# «አርእስት ፡ ስጡልኝ ፤»

## ልብ-ወለድ ፡ ታሪክ ።

ከገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፤

በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡
ዘኢትዮጵያ ፡ በ፴፯ኛው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡

በ፲፱፻፳፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡

በንግድ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

መታሰቢያነቱን ፡ ለኢትዮጵያኖችና ፡ ኢትዮጵያን ፡
ለሚወዱ ፡ ሁሉ ።


የመተርጐሙ ፤ መልሶ ፡ የማሳተሙ ፥ ትያትሩን ፡ የማሳየቱ ፤
መብት ፡ የደራሲው ፡ ብቻ ፡ ነው ።



ደራሲው ፤

አለመማር ፤ የመመራመርን ፤ ችሎታ ፤ ይመጥናል ፤ አለማወቅ ፤ የኑሮን ፤ ደረጃ ፤ አያሻሽልም ፤ በኑሮ ፤ አለመሻሻል ፤ መፈጠርን ፤ አያስመኝም ፡፡

መፈጠርን ፤ መጥላት ፤ የችግር ፤ መፍትሔ ፤ ከማይሆነው ፤ ካንድ ፤ ረቂቅ ፤ ነገር ፤ ጋር ፤ ያሟግታል ፡፡



ደራሲው ፡

አለመማር ፣ የመመራመርን ፡ ችሎታ ፡ ይመጥናል ፤ አለማወቅ ፣ የኑሮን ፡ ደረጃ ፡ አያሻሽልም ፤ በኑሮ ፡ አለመሻሻል ፣ መፈጠርን ፡ አያስመኝም ።

መፈጠርን ፡ መጥላት ፣ የችግር ፡ መፍትሔ ፡ ከማይሆነው ፡ ካንድ ፡ ረቂቅ ፡ ነገር ፡ ጋር ፡ ያሟግታል ።

# ማውጫ ።


| | | ገጽ ፡ |
| --- | --- | --- |
| ፩/ | መግቢያ ፡ ........................... | ፲፩ ፡ |
| ፪/ | መቅድም ፡ ........................... | ፲፭ ፡ |
| ፫/ | ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ የኤፍሬም ፡ መጸነስ ፡ ......... | ፲፱-፳፰ ፡ |
| ፬/ | ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ የኤፍሬም ፡ የልጅነት ፡ ኑሮ ፡ ... | ፳፱-፴፬ ፡ |
| ፭/ | የገደባኖ ፡ አውሎ ፡ ነፋስና ፡ ቃጠሎ ፡ ...... | ፴፭ ፡ |
| ፮/ | የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ........................ | ፴፯ ፡ |
| ፯/ | ወንድ ፡ ይፍራው ፡ ...................... | ፴፯-፴፰ ፡ |
| ፰/ | የወንድይፍራው ፡ ሞት ፡ ................ | ፴፱-፵፩ ፡ |
| ፱/ | በጅሮንድ ፡ አደፍርሰውና ፡ ዋለልኝ ፡ ...... | ፵፩-፵፫ ፡ |
| ፲/ | የኤፍሬም ፡ ትምህርት ፡ .................. | ፵፬-፵፭ ፡ |
| ፲፩/ | የዓይኔ ፡ አበባ ፡ መሞት ፡ ................ | ፵፯-፵፱ ፡ |
| ፲፪/ | ኤፍሬም ፡ በሕልሙ ? ወይስ ፡ በውኑ ? ...... | ፶፩-፶፭ ፡ |
| ፲፫/ | መልክተኞች ፡ .......................... | ፶፯ ፡ |
| ፲፬/ | ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ (አንደኛ ፡ ትይንት) ፡ ......... | ፶፯-፷፯ ፡ |
| | — ኤፍሬም ፡ ............................ | |

— አሳብ ፡ ..............................
— በእውነቱ ፡ ..............................
— ታሪኩ ፡ ..............................
— ይነሱ ፡ ..............................
— መሣይ ፡ ..............................
— ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፡ ..............
፲፭/ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ (ሁለተኛ ፡ ትይንት) ፡ ...... ፸፯-፺፭ ፡
— እንደልቡ ፡ .......................... ፹፯ ፡
፲፮/ ምዕራፍ ፡ ፫ ፡ (ሶስተኛ ፡ ትይንት) ፡ ...... ፺፯ ፡
— የገላጋዮች ፡ ጉባኤ ፡ .................. ፺፯ ፡
— የዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፡ እንዳይሞት ፡
የይግባኝ ፡ አቤቱታ ፡ ............ ፻፫ ፡
— የኤፍሬም ፡ ጭንቅና ፡ ፀፀት ፡ ......... ፺፱-፻፲ ፡
— ፕሮብሌም ፡ .......................... ፻፲-፻፲፩ ፡




# መግቢያ ።

« አርእስት ፡ ስጡልኝ ፡ » ብዬ ፡ ከፊሉን ፡ በትያትር ፡ መልክ ፡ ያቀረብኩት ፡ ድርሰቴ ፡ መነሻው ፡ የአሳብ ፡ ክርክር ፡ ሲሆን ፤ ኤፍሬም ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ ከተጸነሰበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ እናቱ ፡ ላይ ፡ ሊደርስ ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ የገመተውን ፡ ሁሉ ፡ በስሜት ፡ እየገለጸ ፤ ስለራሱ ፡ መጨነቅ ፡ ስለራሱ ፡ ማሰብና ፡ ግራ ፡ እስኪገባው ፡ መበጥበጥ ፡ እስከጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ እናቱ ፡ እሱን ፡ ለማሳደግ ፡ ታደርገው ፡ የነበረውን ፡ ጥረት ፤ ግን ፡ ፍላጐትዋ ፡ በከፊል ፡ እንኳን ፡ አይሞላላት ፡ ስለነበረ ፡ አስባ ፡ ታሳስበው ፤ ተጨንቃ ፡ ታስጨንቀው ፡ እንደነበረ ፡ ከስሜት ፡ ጋር ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

የአባቱ ፡ የጦር ፡ ሜዳ ፡ ሁናቴ ፡ በእናቱ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ኀዘንን ፡ ፈጥሮ ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ፍሬ ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ የኀዘንዋ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆን ፡ ያጽናናት ፡ እንደነበረ ፡ ያስረዳናል ።

ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከገባ ፡ በኋላም ፡ « ቀን ፡ ታወጣ ልኛ ፡ ይሆናል » እያለች ፡ ትመኝ ፡ የነበረችው ፡ እናቱ ፡ አንድም ፡ የደስታ ፡ ጭላንጭል ፡ ሳታይና ፡ በልታ ፡ ሳትጠግብ ፤ ሳይደላት ፡ በሞት ፡ ስትለየው ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡

እስኪጠራጠር ፡ ድረስ ፡ እስከ ፡ ዕብደት ፡ የተቀራረበ ፡ መሆኑን ፡ ያብራራል ።

የአባቱንና ፡ የእናቱን ፡ ሁናቴ ፡ ትዝ ፡ እያለው ፤ ሆዱን ፡ እየለበለበው ፤ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፤ ከመኖርም ፡ መልሶ ፡ ወደ ፡ አለመኖር ፤ « ይህ ፡ ወኃ ፡ ቅዳ ፡ ወኃ ፡ መልሱ ፡ አእምሮዬን ፡ አናውጦታልና ፡ ነገ ፡ መሞቴ ፡ ስለ ማይቀር ፡ እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ ይህንን ፡ ላጥና ፡ ያንን ፡ እያልኩ ፡ አልበጠበጥም ፡ » ብሎ ፡ ትምህርቱን ፡ መተ ዉን ፡ ይገልጻል ።

የሥራ ፡ ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ እሱነቱን ፡ እስኪያ ስጠላው ፡ ድረስ ፡ ተቃርቦ ፡ በተናገሩት ፡ ቁጥር ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየዋለለ ፡ ያባከነውን ፡ ጊዜና ፡ ያለማሰብ ፡ የፈጠረ በትን ፡ የሕሊና ፡ ተውሳክ ፡ በመገንዘብ ፡ ያለፍሬ ፡ ያሳለ ፈውን ፡ ዘመን ፡ እየረገመ ፡ የመመራመርና ፡ የማሰብ ፡ ዕድ ሜው ፡ እንዲሁ ፡ በእንዲሁ ፡ አሳልፎ ፡ ሊደርስበት ፡ በማ ይችል ፡ ጊዜ ፡ ጸጸት ፡ ላይ ፡ መውደቁን ፡ አስተዋዮች ፡ የሰ ውየውን ፡ ሁናቴ ፡ ከጊዜ ፡ ትርጉም ፡ ጋር ፡ ሊያመዛዝኑት ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ።

ሰው ፡ በከንቱ ፡ ያሳለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ሲያስብ ፡ ኀዘን ፡ ይሰማዋል ። የማያዝን ፡ ከሆን ፡ በመወለዱ ፡ ሰው ፡ ይባ ላል ፤ የሚገባውን ፡ ባለመፈጸሙ ፡ የመነቀፍን ፡ ዓምድ ፡ ይከፍታል ። የቀረበው ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንደ



እውነተኛ ፡ ታሪክ ፤ ሌሎችም ፡ እንደ ፡ ልበ ፡ ወለድ ፡ የሚ መለከቱት ፡ አይጠፉም ። የሁለቱ ፡ አስተሳሰብ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ዕምነትን ፡ ፈጥሮአል ፡ ማለት ፡ ነው ። የሁለቱን፡ ክፍል ፡ ዕምነት ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ ዳኝነት ፡ የለም ። በሚታዩ ፡ ነገሮች ፡ ሰውን ፡ ማሳመን ፡ አያስቸግርም ። የማይታዩ ፡ ረቂቅ ፡ ነገሮች ፡ ግን ፡ የያንዳንዱ ፡ ግለ ፡ ሰብ የግል ፡ ትርጉም ፡ ናቸው ።

ከብቶች ፡ የመብላትን ፤ የመንቀሳቀስን ፤ እንደዚ ሁም ፡ ድምፅ ፡ የማሰማትን ፡ ክንውኖች ፡ ይፈጽማሉ ። ይህም ፡ አስቦ ፡ ማከናወን ፡ ሳይሆን ፡ ጊዜአዊ ፡ ፍላጎታ ቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ያላቸው ፡ መገፋፋት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ሰው ፡ በፍላጎት ፡ ብቻ ፡ የሚመራ ፡ ሳይሆን ፡ የሚ መኛቸውን ፡ ጉዳዮች ፡ አስቀድሞ ፡ ያስባል ። በኋላም ፡ ላድርግ ፡ አላድርግ ፡ እያለ ፡ ከአሳቡ ፡ ጋር ፡ ተሟግቶ ፡ ለውሳኔ ፡ ካቃረበ ፡ ወዲያ ፡ ተገቢውን ፡ እርምጃ ፡ ወስዶ ፡ ፍላጎቱን ፡ ይፈጽማል ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የማሰብና ፡ የመመራ መር ፤ የማወቅና ፡ የመራቀቅ ፡ ችሎታው ፡ ተመሳሳይ ፡ አይደለምና ፡ የመልኩን ፡ ያህል ፡ የተለያየ ፡ ግብር ፡ አለው ። የአሳብ ፡ ልዩነትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎችን ፡ ይፈጥ ራል ። የያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ አሳብ ፡ በጉልህ ፡ ባይታይም ፡

ግብሩ ፡ የሱን ፡ ሁናቴ ፡ ይገልጻል ። ስለዚህ ፡ የሰው ፡ ፍጥ ረቱና ፡ ጠቅላላ ፡ ኑሮው ፡ በራሱ ፡ ተያትር ፡ ስለሆነ ፡ በግ ልጽ ፡ የሚታየው ፡ ግዙፉ ፡ ሰውና ፡ የማይዳሰሰው ፡ አሳቡ ፡ ረዳቶቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ሲሟገቱ ፡ ለማሳየት ፡ ከፊሉን ፡ መጽሐፍ ፡ በተያትር ፡ መልክ ፡ አዘጋጅሁት ።

ደራሲው ።



# መቅድም ።

በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ አድናቆትን ፡ ባተረፈው « ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር » ተሰኝቶ ፡ ከክቡር ፡ አቶ ፡ አዲስ ፡ ዓለማየሁ ፡ በተደረሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ደራሴው ፡ ፊደሎችን ፡ በማሳጠር ፡ ረገድ ፡ ለሌሎች ፡ ደራሴዎች ፡ የሰ ጡትን ፡ ምክር ፡ ተከትዬ ፡ አምስቱ ፡ ጕደሎ ፡ የተባሉትን ፡ ፊደሎች ፡ እንዲቀሩ ፡ ለማድረግ ፡ ሞከርኩ ።

የ ፡ « ሀ ፡ ሠ ፡ አ ፡ ጸ ፡ » ጎሳዎችን ፡ በመተው ፡ በያን ዳንዱ ፡ ፊደል ፡ ብቻ ፡ ስጠቀም ፡ ድርሰቴን ፡ አጋመስኩ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ተማሪ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ አንዱ[ን] ፡ ፊደል ፡ ባንደኛው ፡ ሥፍራ ፡ እያስገባሁ ፡ ስጠቀምባቸው ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያስቀሩኝ ፡ የነበሩት ፡ እነ ፡ ሀ ፡ ሐ ፡ ኀ ፡ ኸ ፡ እነ ፡ ሠ ፡ ሰ ፡ እነ ፡ አ ፡ ዐ ፡ እናም ፡ እነ ፡ ጸ ፡ ፀ ፡ አሁንም ፡ አንዱ[ን] ፡ በሌላው ፡ ሥፍራ ፡ ገብቶ ፡ ስመለከተው ፡ መልሶ ፡ ቅር ፡ ሊያሰኘኝ ፡ ቻለ ።

የፈረንጆች ፡ ፊደሎች ፡ በቁጥር ፡ ያነሱ ፡ ሆነው ፡ ወደ ፡ ቃላት ፡ በሚለወጡበት ፡ ጊዜ ፡ በፊደል ፡ ያጠሩትን ፡ ያህል ፡ በቃላት ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ልክ ፡ በርክተውና ፡ የፊ ደሎቹ ፡ አጠራርም ፡ ተለውጦ ፡ ይታያል ። ( neighbour ) የሚለው ፡ ዘጠኝ ፡ ፊደሎችን ፡ የያዘው ፡ ቃል ፡ በአማርኛ ፡ አነባብ ፡ « ኔበር » ተብሎ ፡ በሶስት ፡ ፊደሎች ፡ ይወ

ሰናል ። በአሜሪካኖች ፡ አጠራር ፡ አንዱን ፡ ፊደል ፡ (ሀ)ን ያስቀርና ፡ በዚያው ፡ ዓይነት ፡ ንባብ ፡ ይጠራል ።

አማርኛ ፡ የሚነበበው ፡ በተጻፈው ፡ ዓይነት ፡ ብቻ ነው ። የተደጋገመ ፡ ፊደል ፡ ያላቸው ፡ ፊደሎች ፡ ቢቀሩ ፤ በቃላት ፡ አጠራርም ፡ ሆነ ፡ ቋንቋውን ፡ በመረዳት ፡ ረገድ ፡ ችግር ፡ አይፈጥርም ። ዕድሜአቸው ፡ ለትምህርት ፡ የደረሱት ፡ ኢትዮጵያኖች ፡ ሁሉ ፡ ደራሲው ፡ በሰጡት ፡ አስተያየት ፡ መሠረት ፡ እንዲማሩ ፡ ቢደረግ ፡ በፊደሎቹ ፡ አጠቃቀም ፡ ረገድ ፡ አንባቢዎች ፡ ደራሲዎችን ፡ እንዳይነቅፉ ፡ ሊያደርግ ፡ ይችላል ።

ኀደሎ ፡ ወደተባሉት ፡ ፊደሎች ፡ ስንመለስ ፤ ደራሲው ፡ « ዛሬ ፡ ለማንኛውም ፡ ነገር ፡ አቋራጭ ፡ መንገድና ፡ ቅልጥፍና ፡ በሚፈለግበት ፡ ጊዜ ፡ የፊደሎቻችን ፡ ያለመጠን ፡ መብዛት ፡ . . . » አስቸጋሪነቱን ፡ ገልጸው ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ እነ ፡ ጐ ፡ እነ ፡ ኰ ፡ እነ ፡ ቈ ፡ የመሳሰሉትን ፡ መተው ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲሉ ፡ ምክርን ፡ አበርክተዋል ። እኔም ፡ ይህንኑ ፡ ለመከተል ፡ ምክርኩ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ፊደሎቹን ፡ በተውኩ ፡ ቁጥር ፡ በቃላት ፡ ያሉትን ፡ ፊደሎች ፡ ማብዛት ፡ ግድ ፡ ሆነብኝ ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የአማርኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፎችን ፡ ንባቡ ፡ የተጻፈውን ፡ ፊደል ፡ የሚከተል ፡ ስለሆነ ፡ አነጋገሩ ፡ የተለወጠ ፡ መሰለኝ ። ቋንቋ ፡ ተብሎ ፡ በሦስት ፡ ፊደል ፡ የሚገለጸው ፡ ቃል ፡



« ቁዋንቁዋ» ፡ ስለተሰኘ ፡ አጠራሩ ፡ ያልተለመደ ፡ ከመምሰሉም ፡ በላይ ፡ የፊደሉ ፡ ማጠር ፡ የቃሉን ፡ መርዘም ፡ አስከተለ ።

ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ምሳሌ ፡ ሌላ ፡ ያልተለመደ ፡ አጠራርን ፡ ሊፈጥሩ ፡ የሚችሉት ፡ ቃላት ፡ «አኳኋን ፡ (አሆሁዋን) ፤ አንኳኳ) (አንኩዋኩዋ) ፡ (አጓጓ) አጉዋጉዋ ፡ » የመሳሰሉትን ፡ መጥቀስ ፡ ያሻል ።

ደራሲው ፡ በሰጡት ፡ አስተያየት ፤ ስለተደጋገሙት ፡ ፊደሎች ፡ ተቃራኒ ፡ አሳብ ፡ የለኝም ። ኀደሎ ፡ ያሏቸው ፡ ፊደሎች ፡ ግን ፡ በቃላት ፡ ውስጥ ፡ እየታከሉ ፡ ቃላትን ፡ በማሳጠር ፡ ረገድ ፡ የሚረዱና ፡ የተፈለገውን ፡ አቋራጭ ፡ (አቁዋራጭ) መንገድ ፡ የሚያስገኙ ፡ ስለሆኑ ፡ ፊደሎቹ ፡ « ጉደሎ » ፡ የሚለውን ፡ ስም ፡ ተነስቶላቸው ፡ « አህጽሮተ ፡ ፊደላት ፡ » በሚል ፡ ስም ፡ ቢያጌጡና ፡ እንደቀድሞአቸው ፡ ለጥቅም ፡ ቢውሉ ፡ መካልም ፡ ነው ፡ እላለሁ ።

አባባሌ ፡ አስተያየቴን ፡ ለመግለጽ ፡ እንጂ ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ የደራሲውን ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ለመንቀፍ ፡ አለመሆኑን ፡ አንባቢ ፡ እንዲረዳልኝ ፡ እጠይቃለሁ ።

# የኤፍሬም ፡ መጸነስ ።

የእምዬ ፡ ጤና ፡ ይታወክ ፡ ጀመር ። አትበላም ፤ ድካ
ም ፡ ይሰማታል ። ምግብ ፡ አጠገብዋ ፡ እንዲደርስ ፡ አት
ፈልግም ፤ ምክንያቱን ፡ ግን ፡ አታውቀውም ። ችግሯን ፡
ለወዳጆችዋ ፡ ታዋያለች ። ለእናትዋም ፡ ነግራለች ፤ ግን ፡
እናትዋ ፡ የልጅዋ ፡ ጤና ፡ መታወክ ፡ የእርግዝና ፡ መሆኑን ፡
ጠርጥራ ፡ ልጅዋ ፡ አስተዛዝና ፡ የነገረቻትን ፡ ችግር ፡ ክብ
ደት ፡ አልሰጠችውም ። እምዬ ፡ በዚህ ፡ ቅር ፡ ተሰኝታለች ፤
ውሎ ፡ አደረ ።

ሕመምዋ ፡ እየባሰ ፡ ሲሄድ ፡ መልሳ ፡ ወደ ፡ እናትዋ ፡
ሄዳ ፡ ሆድዋ ፡ የሚያቃጥላትና ፡ እህልም ፡ የማይቀበላት ፡
መሆኑን ፡ አልቅሳ ፡ ነገረቻት ። የእምዬም ፡ እናት ፡ «አይ
ዞሽ ፤ ምንም ፡ በሽታ ፡ የለሽም ፡ ምናልባት ፡ ጽንስ ፡ ይሆና
ልና ፡ አሁን ፡ ይተውሻል ፡ አትስጊ ፡ » ብላ ፡ አጽናናቻት ።
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እናቱ ፡ በደስታ ፡ ተዋጠች ። ፊትዋ ፡ ባንድ ፡
ጊዜ ፡ በራ ፤ ተለወጠ ። እኔ ፡ ልወልድ ፡ ነውና ፡ ሕመሙ ፡
ጨርሶ ፡ እንደተዋት ፡ ይሰማት ፡ ጀመር ። ችግርዋና ፡ ጭን
ቀዋ ፡ በስሜት ፡ ተቃለለ ። ጐረቤቱ ፡ በሙሉ ፡ ማርገዝ
ዋን ፡ አወቀ ።

የሶስት ፡ ወር ፡ ጽንስ ፡ ነኝ ። ከስድስት ፡ ወር ፡ በኋላ ከታሰርኩበት ፤ ከታፈንኩበት ፡ ማየትና ፡ መስማት ፡ ከማልችልበት ፡ ከጠባቡ ፡ ጓዳ ፡ ልወጣ ፡ ነኝ ። ቢርበኝና ፡ ቢጠማኝ ፡ ጩኸቴን ፡ አሰምቼ ፡ ፍላጐቴን ፡ በመጠኑ ፡ ማርካት ፡ ልችል ፡ ነው ። እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ እምዬ ፡ ካልበላችና ፡ ካልጠጣች ፡ እኔ ፡ እችግራለሁ ። ክሳቴ ፡ ሳይታይና ፡ ሳይታወቅ ፡ እታፈንኩበት ፡ እጐላላለሁ ። ጉዳቴ ፡ አይታወቅም ፡ ጩኸቴም ፡ አይሰማም ። ከተወለድኩ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ችግሬን ፡ በሁለት ፡ ዘዴ ፡ ላቃልል ፡ እንደምችል ፡ እረዳለሁ ። በራሴ ፡ መተዳደር ፡ እስክችል ፡ በጩኸት ፤ ጉልበቴ ፡ ሲጠና ፡ ግን ፡ ግራቀኝ ፡ ብዬ ፡ ፍላጐቴን ፡ ማርካት ፡ ስለምችል ፡ እስከወለድ ፡ ያለው ፡ ችግሬ ፡ መፈጠርን ፡ አያስጠላም ። ስለዚህ ፡ መፈጠሬን ፡ ወድጃለሁ ። ችግሩ ፡ በእምዬ ፡ ላይ ፡ ስለሚበረታ ፡ ያበሳጫታል ፤ ሆኖም ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ስለሚወድ ፡ የራሱ ፡ የሆነውንም ፡ ይወዳል ፤ እኔም ፡ ለእምዬ ፡ አካልዋ ፡ ነኝ ። ጣትዋ ፡ ቢቆስልና ፡ ቢገማ ፡ ቊርጣ ፡ አትጥለውም ፤ በመላወስና ፡ በመወራጨት ፡ የምፈጥርባትን ፡ ሁከት ፡ በክፉት ፡ አትተረጉመውም ። ትታገሰኛለች ። ሆኖም ፡ ባላውካት ፡ ባላስጨንቃት ፡ ትወዳለች ፤ አጋጣሚ ፡ እንዲሆንላት ፡ እንጂ ፡ መክራ ፡ እንደማትመልሰኝ ፡ ታውቃለች ። ስትመክረኝ ፡ ብትውል ፡ ብታዝን ፡ ብታጉረመርም ፡ ተጐዳች ፡ ከሳች ፡ ጠቆረች ፡ ብዬ ፡ መወራጨቴን ፡ አልተውኩም ። ምግብ ፡ ባነ



ሳት ፡ ቊጥር ፡ ጉዳት ፡ ይሰማኝ ፡ ነበር ። ብታገኝም ፡ ስለሚያቅራት ፡ አትበላም ። የሀኪም ፡ እርዳታ ፡ ስታገኝ ፡ ትበላ ፡ ስለነበረ ፡ ሰው ፡ ሆኜ ፡ ለመወለድ ፡ ጠቀመኝ ።

ጎጆዬ ፡ እየሰፋ ፤ ሰውነቴ ፡ እየፋፋ ፡ የእምዬም ፡ ሆድ ፡ እየገፋ ፡ ሄዶአል ። ገና ፡ ሰባት ፡ ወሬ ፡ ነው ። እምዬ ፡ ተጎሳቊላለች ፡ ከአንገትዋ ፡ በላይ ፡ በሃይል ፡ ከስታ ፡ እግሮችዋ ፡ አብጠው ፡ አቋዋምዋ ፡ የተንጋደደ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። በጀርባዋ ፡ ያዘለች ፡ ሴት ፡ ወደፊት ፡ የማጐንበስ ፡ ዝንባሌ ፡ እንደምታሳየው ፡ የእምዬም ፡ የሆድዋ ፡ ሸክም ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ አንጋድዶአታል ። መንጋደድዋ ፡ ሚዛንን ፡ ለመጠበቅ ፡ እንጂ ፡ የበሽታ ፡ አይደለም ። መሥራት ፡ ስላለባት ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ትላለች ፤ ወለም ፡ እንዳይላት ፡ እንቅፋት ፡ እንዳይመታት ፡ በሃይል ፡ ትጠነቀቃለች ።

የመወለጃ ፡ ጊዜኤ ፡ ተቃርቦአል ፤ ስምንት ፡ ወር ፡ ሆኖኛል ፤ እምዬ ፡ በጣም ፡ ድካም ፡ ተሰምቶአት ፡ ረፍት ፡ ያስፈልጋታል ። የኔ ፡ ያለአሳብ ፡ መወራጨት ፡ በጣም ፡ ይጎዳታል ። «ድካም ፡ በዝቶብኛልና ፡ እንዴት ፡ አምጬ ፡ እወልድህ ፡ ይሆን ፡ » እያለች ፡ ታማክረኛለች ። መቼም ፡ የኔ ፡ መልስ ፡ ጭጭ ፡ ነው ። « እረ ፡ ጨነቀኝ ፤ አሁንስ ፡ ማርያም ፡ በቀረበችኝና ፡ በተገላገልኩ ፡ » ማለትን ፡ አዘወተረች ። ሆኖም ፡ መታገስ ፡ ይኖርባታል ፡ እንጂ ፡ ያለጊዜው ፡ ልትወልደኝ ፡ አትችልም ። ያለጊዜው ፡ ምጥም ፡

ጭንቅና ፡ አሳር ፡ ነው ። ግን ፡ ዘጠነኛውን ፡ ወር ፡ ይዣለሁ ። እርግጫው ፡ እየባሰ ፡ ሄደ ። እወራጫለሁ ፤ እምዬን ፡ በጣም ፡ አሳቀቅኩአት ፤ የድካምዋ ፡ ውለታ ፤ የጭንቅዋ ፡ ውጤት ፡ ምን ፡ ይሆን ? እስዋስ ፡ ለናትዋ ፡ ምን ፡ አገልግሎት ፡ ሰጥታለች ? ለናትዋ ፡ አገልግሎት ፡ ካልሰጠች ፡ ምናልባት ፡ መውለድ ፡ አመል ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይሆን ? ጭንቅና ፡ ስቃይ ፡ አመልን ፡ ማስታገስ ፡ አይኖርበትምን ?

ዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ሊገባደድ ፡ ተቃርቦአል ። እምዬ ፡ በፍርሃት ፡ ተውጣለች ። ለሊት ፡ እንቅልፍ ፡ አይወስዳትም ፤ « የጅቦች ፡ ጎሽምታ ፡ እንደወትሮ ፡ አይደለም ፤ የሚያለቅሱ ፡ ይመስላሉ ። የተምትሜ ፡ ዶሮም ፡ ያለ ፡ ሰዓቱ ፡ መጮህ ፡ ከጀመረ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ አለፈው ። ውሾቹም ፡ የሚያሰሙት ፡ ጩኸት ፡ ከሌላው ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ነው ፤ አይዘንድሮ ! ምን ፡ ይውጠኝ ፡ ይሆን !» እያለች ፡ ጭንቅ ፡ ጥብብ ፡ ብሎአታል ። ዘወትር ፡ ታየው ፡ የነበረው ፡ ሳር ፡ ቅጠሉ ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ይመስላት ፡ ጀመር ። ጎረቤቶች ፡ ባጽናንዋት ፡ ቁጥር ፡ ችግርዋን ፡ ለመርሳት ፡ ትሞክራለች ።

የገንፎ ፡ እህል ፡ እንዲፈተግላት ፡ የዘመድ ፡ ያለህ ፡ ትላለች ፤ የመውለድ ፡ ወግ ፡ ሊደርሳት ፡ ነውና ። ጊዜ ፡ ባገኘች ፡ ቁጥር ፡ ስወለድ ፡ የምለብሰውን ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ትስፋፋለች ፤ እምዬ ፡ ከኔ ፡ በፊት ፡ ወልዳ ፡ አታውቅምና ፡ እኔ ፡ ብወለድ ፡ የበክር ፡ ልጅዋ ፡ መሆኔ ፡ ነው ።



ስለምጥ ፡ በተነሳ ፡ ቁጥር ፡ ትደነግጣለች ፤ ብዙዎች ፡ ሴቶች ፡ በወሊድ ፡ መሞታቸውን ፡ ሰምታለችና ፤ ሆዳቸው ፡ ተቀዶ ፡ ልጅ ፡ የወጣላቸውም ፡ ሴቶች ፡ ታውቃለችና ፡ እምዬ ፡ ጭንቅ ፡ ይዞአታል ።

ቅዳሜ ፡ ዕለት ፡ ከለሊቱ ፡ በአሥር ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፤ ገና ፡ ጎህ ፡ ሳይቀድ ፤ የወፎቹ ፡ ጭውታ ፡ ሳይሰማ ፤ የኮከቦች ፡ ብርሃን ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ ሀይል ፡ ሳይሸፈን ፡ እምዬ ፡ ምጥ ፡ ጀመራት ። «ወይኔ !» ማለት ፡ መጮህ ፡ ሆነ ። እኔም ፡ ቶሎ ፡ እንድወለድ ፡ ባማጠች ፡ ቁጥር ፡ እርዳታዬን ፡ ከመስጠት ፡ አላቋአረጥኩም ። ግን ፡ የኔ ፡ እርዳታና ፡ እስዋም ፡ በድካም ፡ ላይ ፡ ስለነበረች ፡ ለማማጥ ፡ ያደረገችው ፡ ሙከራ ፡ ሊረዳት ፡ አልቻለም ። የቀድሞ ፡ ፍርሃትም ፡ አለ ። ሐኪም ፡ በአቅራቢያው ፡ የለም ።

አባቴ ፡ እምዬ ፡ አጠገብ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ አይን ፡ ዓይንዋን ፡ እያየ ፡ ከስዋ ፡ ይበልጥ ፡ የሚያምጥ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። ላብ ፡ አስምጦአታል ። «ምነው ፡ ወንድ ፡ ይፍራው ፡ መኪና ፡ ፈልገህ ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውሰደኝ ፡ እንጂ ! እንዴት ፡ ቁጭ ፡ ብለህ ፡ ታየኛለህ ! አልነጋም ፡ እንዴ ! ሞትኩልህ ፡ እኮ » ! እያለች ፡ ስትጮህ ፡ ሰዓቱ ፡ ወደ ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ተቀራርቦ ፡ ስለነበረ ፡ ተነስቶ ፡ መኪና ፡ ፍለጋ ፡ ወደ ፡ መንደር ፡ ሄደ ። የሶስት ፡ የአራት ፡ ቤቶች ፡ መዝጊያዎችን ፡ ደበደበ ። ምንም ፡ የሚሰማው ፡ ሰላጣ ፡

ተጨነቀ ። የእምዬንም ፡ ጩኸት ፡ ከሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ይሰማል ፤ በሀይል ፡ ተርበተበተ ። ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየሮጠ ፡ የአምስተኛውን ፡ ቤት ፡ መዝጊያ ፡ በሃይል ፡ ሲደበድብ ፡ ጎረቤቱ ፡ ሁሉ ፡ ተረበሸ ። የእምዬ ፡ ጩኸት ፡ እየባሰ ፡ ሄደ ። አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ሲሆን ፡ እንድትጠፋ ፡ አምላክ ፡ ባለመወሰኑ ፡ አባቴ ፡ መኪና ፡ አግኝቶ ፡ ይዞ ፡ መጣና ፡ እምዬን ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ይዞአት ፡ በረረ ። ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውስጥም ፡ በአስቸኳይ ፡ የሐኪም ፡ ዕርዳታ ፡ እንዲደረግላት ፡ ዶክተሩን ፡ ለምኖ ፡ እምዬ ፡ ተገቢውን ፡ ዕርዳታ ፡ ልታገኝ ፡ ቻለች ። ቀኑን ፡ በሙሉ ፡ ሳስጨንቃት ፡ ቆይቼ ፡ በአሥራ ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ብቅ ፡ አልኩ ! ተወለድኩ ። ከጠባቡ ፡ ምሽጌ ፤ መጠኑ ፡ ወደሰፋው ፤ ትርጉሙ ፡ ወደ ፡ ከፋው ፤ ብልሃቱ ፡ ወደጠፋው ፡ አለም ፡ መጣሁና ፡ እልልታው ፡ ቀለጠ ።

የእምዬ ፡ ጭንቅ ፡ በደስታ ፡ ተለወጠ ። ክፍልዋ ፡ በሙሉ ፡ በአበባ ፡ ተጌጠ ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ እምዬን ፡ ተወና ፡ እኔን ፡ ለማየት ፡ ወደኔ ፡ ይጠጋ ፡ ጀመር ። « እንዴት ፡ ያለ ፡ ወብ ፡ ልጅ ፡ ነው » የሚለኝ ፡ በረከተ ። አይኖቼን ፡ ገልጬ ፡ ስለነበረ ፡ ተመልካች ፡ ሁሉ ፡ « ካሁኑ ፡ ማየት ፡ ጀመረ» እያለ ፡ ይገረም ፡ ነበር ።



## እንዲያ ፡ ነው !

ባለም ፡ ላይ ፡ ለመኖር ፡ ምንም ፡ ውል ፡ ሳይኖረኝ ፤
ያለ ፡ ፍላጎቴ ፡ አንድ ፡ ሀይል ፡ ፈጠረኝ ።

ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ታስሬ ፡ በሁዋላም ፡ ተወለድኩ ፡
አይኖቼን ፡ ገልጬ ፡ ለማየት ፡ አላመድኩ ።

ያላየሁት ፡ ዓለም ፡ መጠኑ ፡ የሰፋ !
የብስጭት ፡ ስፍራ ፡ ትርጉሙ ፡ የከፋ ።

መሆኑን ፡ አይና !
ላየሩ ፡ መላመድ ፡ ያስነጥሰኝና ፤
ስጮህ ፡ እገኛለሁ ፡ ለመኖር ፡ ነውና ።

ጥቂት ፡ ሲበርድልኝ ፡ በጡት ፡ ተባብዬ ፡
ሳላውቅ ፡ እስቃለሁ ፡ የበቃው ፡ መስዬ ።

ዓይኖቼን ፡ አፍጥጬ ፡ እንደ ፡ ማይ ፡ ይመስል ፤
ነገርን ፡ የሚያውቅ ፡ የሚያሰላስል ፤
መስዬ ፡ እታያለሁ ።
የከፋው ፡ ይመስል ፡ ድንገት ፡ እጮሀለሁ ።

እምዬና ፡ አባዬ ፡ እሽ ፡ ሩ ፡ ሩ ፡ ሲሉኝ ፡
ፊት ፡ ፊቴን ፡ ሲያዩኝ ፤

ወደመታለሉ ፡ ይመልሱኝና ፡
ድዴን ፡ እገልጣለሁ ፡ ውለታ ፡ ነውና ።
ሁዋላም ፡ ቅር ፡ ሲለኝ ፡ ምርር ፡ ብዬ ፡ ሳለቅስ ፡

ጡት ፡ ጡት ፡ ያሰኙኛል ፤
ሆዴ ፡ ሲሞላ ፡ እንጂ ፡ መቼ ፡ ይገባኛል ።

እምዬም ፡ ተቀምጣ ፡ የናትዋን ፡ ውለታ ፡ በኔ ፡
ለመመለስ ፡ አትኩራ ፡ ስታየኝ ፤
አጥብታ ፡ ለማስዳህ ፡ እንካ ፡ ጡት ፡ ስትለኝ ፤

አፌን ፡ እከፍታለሁ ፤
ፊት ፡ ፊትዋን ፡ እያየሁ ፤
ጡቶችዋን ፡ ጨብጬ ፡ ሆዴ ፡ እስኪሞላ ፡ እመገምጋለሁ ።

ለመዳሁ ፡ ስደርስ ፡ ጉልበቴ ፡ ሲጠና ፡
ግራ ፡ ቀኝ ፡ እላለሁ ፡ ፍላጐት ፡ ነውና ፤

የሚጎዳው ፡ ነገር ፡ ምኑንም ፡ ሳላውቀው !
የሚጠቅመኝንም ፡ ፈጽሞ ፡ ሳልለየው ፤

እንደፋደፋለሁ ፤
ሳላውቅ ፡ እደቅአለሁ ።
ጉዳቱን ፡ አላውቀው ፡ ነገር ፡ መቼ ፡ ለየሁ !
ድካም ፡ ሲበዛብኝ ፡ እነጫነጫለሁ ፤
እምዬን ፡ እያየሁ ፡
እምባዬን ፡ በማፍሰስ ፡ አስጨንቃታለሁ ።

«እንካ ፡ ጡት ፡ » እያለች ፡ ታባብለኛለች ፡
የጩኸቴ ፡ ትርጉም ፡ ምግብ ፡ ነው ፡ እያለች ፤
ስቃ ፡ እያሳቀች ፡ በጡት ፡ በማባበል ፡ ታታልለኛለች ፤
ካደጋ ፡ ሰውራ ፡ ልማቴን ፡ ትሻለች ፤
የስጋዋ ፡ ቁራጭ ፡ መሆኔን ፡ ታውቃለች ።

መዳሁን ፡ አልፌ ፡ ገና ፡ ዳዴማ ፡ ስል ! ሆድዋ ፡ ይሸበራል ፡
እፈጠፈጣለሁ ፡ እቃም ፡ ይሰበራል ፤
የማየውን ፡ ሁሉ ፡ መጨበጥ ፡ ያምረኛል ።



“መከልከል ፡ አልወድም ፤
መጥፋቱን ፡ አላውቅም !
ቢሰበር ፡ ቢበላሽ ፡ ከማዘን ፡ በስተቀር ፡ ጠልታኝም ፡
አታውቅም ።”

በዚህ ፡ አይነት ፡ ችግር ፡
ቢኖራት ፡ ከጉአዳ ፡ ባይኖራት ፡ በብድር ፤

«እሽ ፡ ሩ ፡ ሩ ፡ »ስትል ፡ አሳድጋኛለች ፡
የስምዋ ፡ መጠሪያ ፡ መሆኔን ፡ አውቃለች ።

የእምዬ ፡ ውለታ ፡ እስከምን ፡ ይደርሳል ?
በስሜት ፡ ካልሆነ ፡ ተጽፎ ፡ መች ፡ ያልቃል !
ጭንቅዋ ፡ መጠበብዋ ፡ እምን ፡ ላይ ፡ ይውላል !

ሳልሠራ ፡ ሳልደክም ፡ ጡቶችዋን ፡ ስጠባ !
ትን ፡ ሲለኝ ፡ ማልቀስ ፡ ስጮህ ፡ መንገብገብዋ ።

እንደ ፡ ምትጨነቅ ፡ ምንም ፡ ሳልረዳ ፡
በስራ ፡ ላይ ፡ ሁና ፡ አዝላኝ ፡ ወዲህ ፡ ወዳ ፤
ምነው ፡ አልተመከረኩ ፡ እምዬን ፡ ስጐዳ !

እኔን ፡ ሰው ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ ተጣጥራለች ፡
መራመድ ፡ እስክችል ፡ አዝላኝ ፡ ቆይታለች ።

ካንድ ፡ ዓመት ፡ በሁዋላ ፡ ዳዴ ፡ እያለችኝ ፤
እቃን ፡ እያሳየች ፡ እያባበለችኝ ፤

ጉልበቴ ፡ ሊጠና ፡ ሊጠነክር ፡ ቻለ ፤
በፀሐይ ፡ በምግብ ፡ እየተባበለ ።

እየተደሰተች ፡ በምናገረው ፡ ቃል ፤

ምንንም ፡ ሳላውቀው ፡ በድንገት ፡ በመጣል ፤
ትርጉም ፡ ባይኖረውም ፡ እምየን ፡ አስቆአል ።

ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ ተናገር ፡ የሚለኝ ፡
ቁጥሩ ፡ የበዛ ፡ ነው ፡ « ጐሽ ! ጐሽ ! » እያለ ፡ አፋፌን ፡
የሚያየኝ ።

እንደልብ ፡ ስራመድ ፡ ጉልበቴ ፡ ሲጠና ፡
የእምዬ ፡ መሸበር ፡ እሮጣለሁና ።

ብወድቅ ፡ ብሰባበር ፡ ብላላጥ ፡ ብደማ !
አባቴም ፡ እናቴም ፡ ተው ፡ ቢሉኝ ፡ አልሰማ ፤

ወድቄአለሁ ፡ ብዬ ፡ መሩዋሩዋጤን ፡ አልተው ፤
ወድቆ ፡ መላላጡን ፡ ጉዳቱን ፡ አላውቀው ።



ም ዕ ራ ፍ ፡ ፪ ።

# የኤፍሬም ፡ የልጅነት ፡ ኑሮ ፡

## የሁለት ፡ አመት ፡ ልጅ ፡ ነኝ ።

በተወለድኩ ፡ ልክ ፡ በሁለት ፡ ዓመቴ ፡ እምዬ ፡ አቅፋኝ ፡ ቁጭ ፡ እንዳለች ፡ ፊት ፡ ፊቴን ፡ በማየት ፡ ብቻዋን ፡ ትነጋገር ፡ ጀመር ። « ልጄ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ በሆዴ ፡ ተሸክሜሃለሁ ። በዘጠኝ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ የነበረኝ ፡ ጭንቅ ፡ አሁን ፡ በቀላሉ ፡ የሚታወስ ፡ አይደለም ። አንተን ፡ በሆዴ ፡ ተሸክሜ ፡ አሸከሩም ፡ ገረዱም ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ በመሆኔ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስቃይ ፡ ሊደርስብኝ ፡ ቻለ ። ከችግር ፡ የተነሳ ፡ ፊቴ ፡ ካሁን ፡ ይበልጥ ፡ አስቊይሞ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ እንዳልደርስ ፡ እደበቅ ፡ ነበር ። በሁዋላም ፡ ጊዜው ፡ ደርሶ ፡ ስወልድህ ፡ የነበረኝ ፡ ነፍሴ ፡ ውጪ ! ግቢ ! አሁን ፡ እንደተረት ፡ የሚወራ ፡ ሆኖአል ። አባትህም ፡ አብሮኝ ፡ ተቀምጦ፡ ከኔው ፡ ጋር ፡ ሲያምጥ ፡ ገጹ ፡ ላይ ፡ ይታይ ፡ የነበረውን ፡ ኀዘን ፡ ላላየ ፡ ሰው ፡ ማስረዳት ፡ ያዳግታል ። ከተወለድክም ፡ በሁዋላ ፡ ምርር ፡ ብለህ ፡ ታለቅስ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ነካብኝ ፡ ብዬ ፡ እጨነቅ ፡ ስለነበረ ፡ ሆድህን ፡ እየቆረጠህ ፡ እየመሰለኝ ፡ ስንት ፡ ቀን ፡ እንብርትህን ፡ እነፋው ፡ ነበር ። ይህም ፡ የሚፈውስ ፡ ሳይሆን ፡ የመሀይም ፡ አስተሳሰብ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ረድቶህም ፡ ይሆናል ፡ ማን ፡ ያው

ቃል ! አንተን ፣ አዝዬ ፡ ወዲያ ፣ ወዲህ ፣ ከማለቴም ፣ ሌላ ፣ የጡቴ ፡ ወተት ፣ የሚበቃህ ፣ ስላልነበረ ፣ ተጨማሪ ፡ ምግብ ፣ እንዳገኝልህ ፡ አደርገው ፣ የነበረው ፡ ጥረት ፣ ከሌብነት ፣ የማይሻል ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ በድህ ፣ ልጅ ፡ መልክ ፣ ያገኘኸውን ፣ ስለምትቆርጥም ፡ አታሳስበኝም ። ባስብም ፡ ልረዳህ ፣ እንደማልችል ፡ አውቃለሁ ። ቢመችህ ፣ ኖሮ ፣ ምን ፣ የመሰልሽ ፡ ሎጋ ፤ ምን ፡ አይነት ፡ ቆንጆ ፣ የሰው ፡ አፍ ፣ አያድርግብህና ፣ አላፊው ፣ አግዳሚው ፣ አንተን ፡ ሲመለከት ፣ በዋለ ። ብቻ ፣ ምንም ፡ አይደለም ፣ ጤና ፡ ከሰ ጠህና ፣ ካደግህ ፡ በላብህ ፡ በማፍራት ፡ ተደስተህ ፣ ልት ኖርና ፣ መልክህም ፡ ስትወለድ ፣ እንደነበረው ፣ ሊጠራ ፣ ይችላል ። እኔንም ፡ ቀን ፡ ታወጣልኝ ፣ ይሆናል ። አባት ህም ፣ ግራ ፣ ገብቶታልና ፣ ትጦረናልህ ። ግን ፡ ላይሆንም ፣ ይችላል ። የእኔ ፣ እናት ፣ ላንተ ፣ ያደረግሁትን ፡ በሙሉ ፣ አድርጋልኝ ፣ አሁን ፡ ለራሴ ፡ ኑሮና ፡ ላንተ ፣ ለልጇ ፡ ከመ ጨነቅ ፣ በቀር ፣ እናቴን ፣ ዞር ፣ ብዬ ፣ አላያትም ። አንተም ፣ ስታድግ ፣ ደህም ፣ ሆንክ ፣ ሀብታም ፤ ከራስህ ፣ ጣጣ ፡ አት ወጣም ፣ ይሆናል ። ለውለታ ፣ ብዬ ፣ አልወለድኩህምና ፣ ምንም ፣ አይደለም ፤» ብላ ፡ ስታቆም ፡ እምባዋ ፣ አቀረረ ።

አገጭዋን ፣ ይዛ ፣ ለጥቂት ፣ ደቂቃዎች ፣ ጭጭ ፣ ብላ ፣ ተቀመጠች ። በሁዋላም ፡ እኔን ፣ አስቀምጣኝ ፣ ሄዳ ፡ ምና ምን ፣ ትሰራራ ፣ ጀመር ። እኔም ፣ በሀይል ፡ አሳብ ፣ ገባኝ ፤ እምዬ ፣ በጣም ፣ አሳዘነችኝ ። ሳላውቀው ፡ እንባዬ ፣ አቀ



ረረ ። ብድግ ፣ ብዬ ፣ አንዲት ፣ ባርጩማ ፡ አጠገብ ፣ ለመ ቀመጥ ፣ ሄድኩና ፣ « እማዬ ፣ ኮንጆ ! አባዬ ፣ ኮንጆ ! » እያልኩ ፡ እምዬ ፣ እንዳትተከዝ ፡ ለማድረግ ፡ ሞከርሁ ። የልጅነት ፡ ጠባይ ፡ መሰላት ፣ እንጂ ፣ የእኔን ፣ መቀባጀር ፣ ዋጋ ፡ አልሰጠችውም ። ቤት ፡ ውስጥ ፡ ብቻዬን ፡ ትታኝ ፣ ለማገዶ ፡ የሚሆን ፡ እንጨት ፣ ፍለጋ ፡ ጉዋሮ ፣ ሄደች ። እኔም ፡ እንቅልፍ ፣ ወስዶኝ ፡ ባርጩማዋን ፡ ተደግፌ ፣ ለጥ ፣ አልኩ ። እምዬ ፣ ስትመለስም ፣ አንስታ ፣ ሰሌን ፣ ላይ ፣ አስተኝታኝ ፣ እንጀራ ፣ ለመጋገር ፣ ወደ ፣ ጉዋዳ ፣ ገባች ። ሰሌኑ ፡ ስለቆረቆረኝ ፡ ከእንቅልፍ ፣ ነቃሁ ። ግን ፣ እምዬ ፣ መንቃቴን ፣ አላወቀችም ። በሀይል ፣ እርቦኛል ። ለማልቀስም ፡ ቃጣሁና ፣ መልሼ ፡ እስዋን ፡ ማስለቀስ ፡ ይሆንብኛል ፣ ብዬ ፣ ዝም ፣ አልኩ ።

ጡት ፡ አሰጥላኛለች ። እንጀራው ፣ ገና ፡ አልደረሰም ። ከቂጥት ፡ ደቂቃዎች ፡ በሁዋላ ፡ መጀመሪያ ፡ ካወጣቻው ፣ እንጀራ ፣ ቆርሳ ፡ ትኩሱን ፣ አመጣችልኝና ፡ በላሁ ። እስ ዋም ፣ ጋገራዋን ፡ ጨርሳ ፡ ፊትዋ ፡ ሁሉ ፣ ጥላሸት ፡ ለብሶ ፤ ያ ፡ ለኔ ፡ ቆርሳው ፣ የነበረውን ፣ እንጀራ ፣ ይዛ ፡ መጣችና ፡ አብረን ፣ በላን ።

አባቴ ፡ ውጭ ፡ ውሎ ፡ ቀኑ ፡ ሲጨልም ፡ ገባና ፡ ከኔ ፣ ትጫወት ፣ በነበረችው ፡ ባርጩማ ፡ ላይ ፡ አገጩን ፣ ይዞ ፣ ተቀመጠ ። እምዬም ፡ እንጀራ ፡ በሽሮ ፡ አቀረበችለትና ፣

« ብላ ፣ እንጂ ፣» አለችው ። «ምን ፣ ነካህ ፣ ብላ ፣ እንጂ !» «ምኑን ፣ በላሁት ! ዓመቱን ፣ በሙሉ ፣ ስለፋበት ፣ የነበረውን ፣ ሰብል ፣ ውርጭ ፣ ድምጥማጡን ፣ አጥፍቶታል ። ቤተሰቤ ፣ እንዳይራብና ፣ እንዳይታረዝ ፣ የአመቱን ፣ የአፈር ፣ ግብር ፣ ያለችግር ፣ ከፍዬ ፣ እፎይ ፣ እንድል ፣ በማለት ከጠዋት ፣ እስከ ፣ ማታ ፣ ዝናብና ፣ ጸሐይ ፣ ሳልመርጥ ፣ በሬዎቼን ፣ ጠምጄ ፣ ሆ ! ስል ፣ ከረምኩ ። አሁን ፣ የድካሜ ፣ ዋጋ ፣ ለማግኘት ፣ በተስፋ ፣ ስጠባበቅ ፣ ይግረምህ ፣ ብሎ ፣ አምላክ ፣ ጉድ ፣ አደረገኝ ። እንግዲህ ፣ በምን ፣ እንከርማለን ! ምን ፣ ለብሰን ! ግብሩስ ! ምኑስ ! ከየት ፣ ሊመጣ ፣ ነው ? » እያለ ፣ ሀዘኑን ፣ ደረደረላት ፤ እምዬ ፣ እኔን ፣ አቅፋኝ ፣ አገጭዋን ፣ ይዛ ፣ በተቀመጠች ፣ ጊዜ ፣ እንባዋ ፣ እንዳቀረረው ፣ የአባቴም ፣ እንባ ፣ አቀረረ ። « ለመጭው ፣ እግዚአብሔር ፣ ያውቃል ። ነገ ፣ ይርበኛል ፣ ብሎ ፣ ዛሬ ፣ የቀረበውን ፣ መተው ፣ አያስፈልግም ፤ የቀረበውን ፣ እንጀራ ፣ ብላ ። ምናልባትም ፣ እግዚአብሔር ፣ ሳይደግስ ፣ አልተጣላንም ፣ ይሆናል ፣ » እያለች ፣ ባፍዋ ፣ ትደልለው ፣ ጀመር ። ከጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ዝምታ ፣ በሁዋላ ፣ የቀረበውን ፣ እንጀራ ፣ በሉ ። እኔንም ፣ በየተራ ፣ እያጐረሱኝ ፣ ሆዴን ፣ ሞሉልኝ ።

የአባቴ ፣ የአመት ፣ ልፋት ፣ በእናቴ ፣ የአፍ ፣ ድለላና ፣ ባንድ ፣ ቀን ፣ አዘን ፣ የሚወስን ፣ አልነበረም ። ያልበላ ፣



ሆድ ፣ ዘወትር ፣ ሊያስታውሰው ፣ ይችላል ። የበረደው ፣ ጉላም ፣ ራሱ ፣ ይመስክራል ። ሌላም ፣ ችግር ፣ በብዛት ፣ አለ። ውርጭ ፣ የብዙዎቹን ፣ ሰብል ፣ አውድሞአል ። አባቴና ፣ እናቴ ፣ ለኔ ፣ ሲያስቡ ፣ እኔ ፣ ለነሱ ፣ ስጨነቅ ፣ ቆየን ። እኔን፣ በእድሜዬ ፣ መጠን ፣ ይገምቱኝ ፣ ስለነበረ ፣ ለኔ ፣ እንደሚያስቡልኝ ፣ እኔ ፣ ደግሞ ፣ ለነሱ ፣ እጨነቅ ፣ እንደነበረ ፣ ሊያውቁ ፣ አልቻሉም ። ረሃብ ፣ ቢያንገበግበኝም ፣ ዝም ፣ እል ፣ ስለነበረ ፣ ዝምታዬ ፣ የተፈጥሮ ፣ ይመስላቸው ፣ ነበር ። በችግር ፣ እየተቆላን ፣ ዓመቱን ፣ አሳለፍነውና ፣ ለተከታዩ ፣ ዓመት ፣ ሳይደግስ ፣ ያልተጣላው ፣ አምላክ ፣ ረድቶ ፣ በጣም ፣ ጥሩ ፣ ሰብል ፣ ሊገኝ ፣ ተቻለ ። ወፍራም ፣ እንጀራችንን ፣ እየበላን ፣ ልብሳችንንም ፣ ለወጥን ።

ከምላ ፣ ጎደል ፣ ኑሮ ፣ እድሜዬ ፣ ከፍ ፣ እያለ ፣ ሄደ ። አባቴ ፣ ከመጠን ፣ በላይ ፣ ይወደኛል ። የእምዬ ፣ መንገብገብ ፣ ይህ ፣ ነው ፣ አይባልም ። አራት ፣ አመት ፣ አልፎኛል ። ከጨኽቴ ፣ በስተቀር ፣ በአነጋገሬ ፣ ሰውን ፣ ማስቀየም ፣ ገና ፣ አልጀመርኩም ። አባቴ ፣ ወደ ፣ እርሻ ፣ ሲሄድ ፣ ተከትየው ፣ እሄዳለሁ ። በሥራ ፣ ግን ፣ አልረዳውም ፤ አባቴና ፣ እናቴ ፣ « አንድ ፣ ልጅከ ፣ ፋት ፤ ቢሉት ፣ ጭልጥ፣ ነውና ፣ እግዚአብሔር ፣ አንድ ፣ እንኩዋን ፣ ቢጨምርልን ፣ ምነው ፣ » ! እያሉ ፣ ወንድም ፣ ወይም ፣ እህት ፣ እንዲኖረኝ ፣ ይመኙሉ ። ጊዜ ፣ ያልፈጠረው ፣ ሰው ፣ ምኞት ፣ አይፈጥረውምና ፣ ሌላ ፣ አልወለዱም ።

# የገደባኖ ፡ አውሎ ፡ ነፋስና ፡ ቃጠሎ ።

ገና ፡ አምስተኛ ፡ ዓመቴ ፡ አልፎ ፡ ስድስተኛውን ፡ እንደጀመርኩ ፡ ገደባኖ ፡ ከሚባለው ፡ እኛ ፡ ከምንኖርበት፣ መንደር ፡ ሀይለኛ ፡ አውሎ ፡ ነፋስ ፡ ተነስቶ ፡ በተነሳው ፡ ነፋስ ፡ ሣር ፡ ክዳን ፡ ያላቸው ፡ ቤቶች ፡ በሙሉ ፡ ክዳናቸው ከመገነጣጠሉም ፡ በላይ ፡ ካንዱ ፡ ቤት ፡ በተነሳው ፡ የእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የሆኑ ፡ ቤቶች ፡ ወደሙ ። ነበልባሉ ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ንብረት ፡ አለቀ ። የመንደሩም ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ፡ ቁጣ ፡ የአንድ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ምልክት ፡ መሆን ፡ አለበት ፡ እያለ ፡ በፍርሃት ፡ ይርበተበት ፡ ጀመር ። ከሁለት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ ጥፋት ፡ በሁዋላ ፡ የነፋሱ ፡ ሀይል ፡ እየተቀነሰ ፡ ቃጠሎውም ፡ እየበረደ ፡ ሄደ ። ግን ፡ የመንደሩ ፡ ሰው ፡ « ተመልሶ ፡ የሚመጣ ፡ ቁጣ ፡ ነው ፡ » እያለ ፡ ይረበሽ ፡ ነበርና ፡ እንዳይመለስ ፡ በየቤተክርስቲያኑና ፡ በየመስጊዱ ፡ « እግዚኦ ! » ይል ፡ ጀመር ። የቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የመስጊድ ፡ ልምድ ፡ የሌላቸው ፡ ወደ ፡ ጠንቋይ ፡ ይጐርፉ ፡ ነበርና ፡ ከጠንቋይ ፡ ዘንድም ፡ « ደርሶ ፡ የነበረው ፡ ጥፋት ፡ አሁንም ፡ ተመልሶ፣ እንደኖህ ፡ ጊዜ ፡ መንደሩን ፡ በወኃ ፡ ሊያጠፋው ፡ ነው ፡» ሲል ፡ ጠንቋይ ፡ የነገራቸውን ፡ የፈጠራ ፡ ወሬ ፡ ይዘው ፡ ጸሎተኛውን ፡ ሁሉ ፡ አርበተበቱት ። ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ በፍርሃት ፡ ተዋጠ ፤ የወኃው ፡ ጥፋት ፡ በዝናብ ፡ ምክንያት ፡

ይመጣ ፡ እየመሰለው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንጋጥጦ ፡ ይመለከት ፡ ጀመር ። ግን ፡ የጠንቋዮች ፡ ወሬ ፡ ሳይሰምር ፡ ቀርቶ ፡ የነፋሱ ፡ ኃይል ፡ እንደወትሮው ፡ መመለስ ፡ ጀመረ ።

ሰማዩም ፡ እጅግ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ዓይነት ፡ ጠራ ። ጭንቅ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ የመንደሩ ፡ ሕዝብ ፡ የመከራው ፡ ጊዜ ፡ በደስታ ፡ የሚለወጥ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ ተረጎመው ።

ውሎ ፡ ሳያድር ፡ የክፍለ ፡ ሀገሩ ፡ ባላባት ፡ ደጃዝማች ፡ ቁምላቸው ፡ የአካባቢውን ፡ ሕዝብ ፡ ሰብስቦ ፡ « ጠላት ፡ በስተሰሜን ፡ በኩል ፡ አድርጎ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ መጥቶአል ፡ ስለተባለ ፡ በጤንነት ፡ የሚገኝና ፡ እድሜው ፡ ከሀያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያላነሰ ፡ ካርባ ፡ አምስት ፡ ያልበለጠ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በሙሉ ፡ አገሩን ፡ ሊወር ፡ የመጣውን ፡ ጠላት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ማጥፋት ፡ ስላለበት ፡ በአስራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ስንቅና ፡ ትጥቃችሁን ፡ አዘጋጁ ፡ » ሲል ፡ አወጀ ።

በአውሎ ፡ ነፋሱ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ሊገጥመን ፡ ነው ፡ ይል ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ አዋጁን ፡ ሲሰማ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ይተያይ ፡ ጀመር ። አባቴ ፡ ምንም ፡ እንኩዋን ፡ በተፈጥሮው ፡ ጀግናና ፡ ደፋር ፡ ቢሆንም ፡ አዋጁን ፡ ሲሰማ ፡ « ወይ ፡ ልጄን ፡ ሳላሳድግ ፡ » በማለት ፡ ለራሱ ፡ ሳይሆን ፡ ለኔ ፡ ተጨንቀ ፡ « ዛሬ ፡ ባልሞት ፡



ነገ ፡ መሞቴ ፡ ስለማይቀር ፡ ለሞት ፡ አልጨነቅም ፡ » የሚል ፡ አነጋገር ፡ ያሰማ ፡ የነበረው ፡ አባቴ ፡ ከኔ ፡ ካንድ ፡ ልጁ ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ መሄድ ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ አገኘው ። « ባገር ፡ የሚለወጥ ፡ ነገር ፡ ሊኖር ፡ ስለማይችል ፡ ሄጄ ፡ ላገሬ ፡ ልሙት ፤ ልጄ ፡ በእድሉ ፡ ያድጋል ፡ » ብሎ ፡ ስንቅና ፡ ትጥቁን ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀመረ ።

ከእግሬ ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ ራሴ ፡ ድረስ ፡ እየተመለከተኝ ፤

« ያገር ፡ ጉዳይ ፡ ሆነ ፡ በል ፡ ልጄ ፡ ልለይህ ፡
ገና ፡ በልጅነት ፡ ጠግቤ ፡ ሳላይህ ።

ላገሬ ፡ ነጻነት ፡ መሞት ፡ ይገባኛል ፡ ልርሳው ፡ ሁሉም ፡
ይቅር ፡
ነጻነት ፡ ነውና ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ክብር ።

ልጅ ፡ ተወልዶ ፡ ቢያድግ ፡ ነጻነት ፡ ከሌለው ፡
በተወለደበት ፡ ሠርቶ ፡ አቅራቢ ፡ ነው ።

የቀድሞ ፡ ድፍረቴ ፡ በልጅ ፡ አይወሰን ፡ ልዋጋ ፡ ጠንክሬ ፡
በጦር ፡ ሜዳ ፡ ልውደቅ ፡ ልሙት ፡ ለሀገሬ ።

አሳቤ ፡ አትባክን ፡ ምክንያት ፡ አታብዛ ፡
ነጻ ፡ መሆን ፡ የለም ፡ ያለ ፡ ደም ፡ በዋዛ » ብሎ ፡ እምዬንና ፡ እኔን ፡ መላልሶ ፡ ስሞን ፡ ተነሳ ፤ « የአይኔ ፡ አበባ ፡ ልጄን ፡ አደራ ! አደራሽን ፡ ኤፍሬም ፡ እንዳይርበው ፡ እንዳይቸገር ፡ ለምነሽም ፡ ቢሆን ፡ ጠብቂው ፡ ልጃችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከባረከው ፡ የዘለዓለም ፡ ስማችን ፡ ነው ። በመልካም

ይዞታ ፡ ካላደገም ፡ የገሌ ፡ ልጅኮ ፡ ነው ! እየተባለ ፡ የራሱ፡ ሕይወት ፡ የሚበላሽ ፡ ከመሆኑም ፡ ሌላ ፡ እኛንም ፡ የመቃብር ፡ እረፍት ፡ ያሳጣናል ።

እርግጥ ፡ ነው ፡— እኔም ፡ ብመለስ ፡ አንቺን ፡ አደራ ፡ በምልሽ ፡ መልክ ፡ ኤፍሬምን ፡ በሚገባ ፡ ላንከባክበው ፡ እንደማልችል ፡ አቅሜን ፡ አውቀዋለሁ ። ሆኖም ፡ ይራብ ፡ ወይም ፡ ይታረዝ ፡ እንጅ ፡ አሳዳጊ ፡ የበደለው ! ጥጋብ ፡ የሚይዘውን ፡ ያሳጣው ! ርህራሄ ፡ የሌለው ! ልቡ ፡ የተደፈነው ! ከሚባሉትና ፡ መፈጠራቸው ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ከሚጠላው ፡ ወሮ ፡ በሎች ፡ ጋር ፡ ተሳታፊ ፡ እንዳይሆን ፡ ከመሞከር ፡ በቀር ፡ የወደፊት ፡ እድሉን ፡ ልወስን ፡ እንደማልችል ፡ አውቃለሁ ። የዓይኔ ፡ አበባ ! ኤፍሬም ፡ ከኛ ፡ ከድሀ ፡ የተገኘ ፡ ፍጡር ፡ ስለሆነ ፡ እሱን ፡ ሰው ፡ ለማድረግ ፡ መሞከር ፡ እንጂ ፡ ባይሠራም ፡ ይባላል ፤ አጊጦ ፡ ይታይልናል ! እንዳንል ፡ መመጻደቅያ ፡ የለውምና ፡ አደራ፤ ምንም ፡ ቢሆን ፡ ከሶስት ፡ ወር ፡ በላይ ፡ አንቆይም ፡ » ብሎአት ፡ ጦርና ፡ ጋሻውን ፡ ይዞ ፡ « ልጄ ፡ በህይወት ፡ ላግኝህ ፡ ! የአይኔ ፡ አበባዬ ! » ብሎን ፡ ወጣ ።

እንደሚባለው ፡ በሃያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ጉዞ ፡ አድዋ ፡ ደረሰ ። የሰሜን ፡ ሕዝብ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከጠላት ፡ ጋር ፡ ግምባር ፡ ለግምባር ፡ በመግጠም ፡ ጠላትን ፡ እየጨፈጨፈና ፡ እየተጨፈጨፈ ፡ ቆየ ። ጦርነቱ ፡ ባፍላው ፡ ላይ ፡



እያለ ፡ አባቴ ፡ ከሌሎች ፡ ፲፪ ፡ እግረኞች ፡ ጋር ፡ ወደጦር ፡ ሜዳ ፡ ገብቶ ፡ ሲዋጋ ፡ ከሰነበተ ፡ በሁዋላ ፡ አብረው ፡ ከነበሩት ፡ አርበኞች ፡ በጠላት ፡ ሀይልና ፡ አገሩንም ፡ ካለማወቅ ፡ የተነሳ ፡ ተጠፋፉ ። ካባቴ ፡ ጋር ፡ ሰባት ፡ ጉዋደኞች ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ሳይለያዩ ፡ ቆይተው ፡ በ፳፪ኛው ፡ ቀን ፡ ጠላት ፡ በከባድ ፡ መሣሪያ ፡ በመጠቀም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብን ፡ ጨርሶ ፡ አባቴም ፡ ከሁለት ፡ ጉዋደኞቹ ፡ ጋር ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ተመትቶ ፡ ወደቀ ። የጠላት ፡ ሀይል ፡ በጣም ፡ እየከፋ ፡ መሄዱን ፡ እምዬና ፡ እኔ ፡ እንሰማ ፡ ነበርና ፡ ምንም ፡ ፋታ ፡ በሌለው ፡ ጭንቅ ፡ ተያዝን ፤ ጨርስን ፡ ወሬ ፡ አጣን ! ። ካባቴ ፡ ጋር ፡ ከሄዱት ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሰዎችም ፡ ሰማንያ ፡ አምስቱ ፡ ወደ ፡ ክፍለ ፡ ሀገራቸው ፡ ተመልሰዋል ። የቆሰሉም ፡ ነበሩ ። የተረፉት ፡ ግን ፡ ይሙቱ ፡ ወይም ፡ በህይወት ፡ ይኑሩ ፡ አይታወቅም ። እምዬ ፡ አርበኛ ፡ ገባ ፡ በተባለ ፡ ቁጥር ፡ እየሄደች ፡ « ባሌስ!» እያለች ፡ እንባዋን ፡ ታነባለች ። « ጠላት ፡ በታትኖን ፡ ነበርና ፡ መልሰን ፡ ልንገናኝ ፡ አልቻልንም ፡ » ከሚላት ፡ በስተቀር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ አየሁት ፡ የሚላትን ፡ አላገኘችም ። እየዬ ! ብላ ፡ አታለቅስ ፡ መርዶውን ፡ አልሰማችም። ሰውነትዋ ፡ ተጎሳቁሎ ፡ ደምዋ ፡ በአሳብ ፡ ምክንያት ፡ ተመጥጦ ፡ ቢጠሩዋት ፡ የማትሰማ ፤ ጨርሳ ፡ በድን ፡ ሆነች ። አንዳንዴም ፡ ከእንቅልፍ ፡ እንደሚባንን ፡ ሰው ፡ ትደነግጥ ፡ ነበር ። የኔም ፡ የሰዋም ፡ እንባ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ይፈስ ፡ ጀመር ።

ከጥቂት ፡ ቀናት ፡ በሁዋላም ፡ «የጠላት ፡ ኃይል ፡ እየ
ገፋ ፡ መጥቶ ፡ ብዙዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጀግኖች ፡ አልቀ
ዋል ፡ » የሚል ፡ ወሬ ፡ ሰምታ ፡ የባልዋን ፡ ሞት ፡ ሳታረ
ጋግጥ ፡ « ባልሽ ፡ ሞቶ አል ፡ ብለውኛል ፡ » ብላ ፡ ኡኡ
ታዋን ፡ አቀለጠችው ! ። ጎረቤቱም ፡ አስቀድሞ ፡ የአባ
ቴን ፡ ሞት ፡ ቢያውቅም ፡ እምዬን ፡ ለማርዳት ፡ ምቹ ፡
ጊዜን ፡ ይጠብቅ ፡ ስለነበረ ፡ ለቅሶውን ፡ ሲሰማ ፡ «ለካስ፡
ሰምታለች ? ለጊዜው ፡ እንዳትሰማ ፡ ብለን ፡ ነበር ፤ ማን ፡
ይሆን ፡ ያረዳብን ? » እያለ ፡ ተሰብስቦ ፡ ማልቀስና ፡ ማላ
ቀስ ፡ ሆነ ። እምዬም ፡ ሳታረጋግጥ ፡ የጀመረችው ፡ ለቅሶ ፡
እውነተኛ ፡ ለቅሶ ፡ ሆነባት ። « እኔን ፡ አሞራ ፡ ይብላኝ ፡»
እያለች ፡ በእንባ ፡ ትታጠብ ፡ ጀመር ። ጎጆአችን ፡ ፈረሰ ! ።
ምሰሶው ፡ ተሰበረብን ፤ ተስፋችን ፡ ተቆረጠ ፤ መኖራችን ፡
ትርጉም ፡ አጣ ! እምዬ ፡ በሀዘን ፡ ልብስ ፡ ተኮራምታ ፡
ወጭ ፡ ወራጁን ፡ « የባሌን ፡ አምዋምዋት ፡ ንገሩኝ »
በማለት ፡ ሰውን ፡ ግራ ፡ እያገባች ፡ « ይህች ፡ ሴት ፡ አበ
ደች ፡ » እስከመባል ፡ ደረሰች ።

በእግዚአብሔር ፡ ሀይልና ፡ በጀግኖች ፡ ቆራጥነት ፡
ድሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሆነና ፡ ጠላት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡
እየተባረረ ፡ መውጣት ፡ ሲጀምር ፤ ከሞት ፡ ከተፈሩት ፡ አር
በኞች ፡ ሁለቱ ፡ ወደ ፡ ሁዋላ ፡ ተቋርጠው ፡ ቀርተው ፡ ስለ
ነበር ፡ ሞተዋል ፡ ተብሎ ፡ ተለቅሶላቸው ፡ ኀዘኑ ፡ ወደ ፡
መረሳት ፡ ሲል ፡ በተጎናጸፉት ፡ ድል ፡ እየቦረቁ ፡ ከጠ



ላት ፡ የማረኩዋቸውን ፡ ዘመናዊ ፡ መሳሪያቸውን ፡ ይዘው ፡
ወደ ፡ ክፍለ ፡ አገራቸው ፡ ገደባኖ ፡ ከተፍ ፡ አሉ ። እልል
ታው ፡ ቀለጠ ፤ ያለቀሰው ፡ ሳቀ ። ያዘነው ፡ ተደሰተ ።
እምዬም ፡ ስለባልዋ ፡ ሞት ፡ ወደ ፡ መጠራጠሩ ፡ ተመለ
ሰች ። ግን ፡ አርበኞቹ ፡ ሳይውሉ ፡ ሳያድሩ ፡ ወደ ፡ ቤታ
ችን ፡ መጥተው ፡ « የመከራ ፡ ጉዋዴ ! ጀግናው ፡ ወዳጄ »
እያሉ ፡ ልንዘነጋው ፡ የሞከርነውን ፡ ሀዘን ፡ በማልቀስ ፡
መልሰው ፡ አስለቅሰውን ፡ የአባቴ ፡ አሟሟት ፡ እንዴት ፡
እንደነበረ ፡ ይገልጹልን ፡ ጀመር ። « አቶ ፡ ወንድይፍራ
ው ፡ » አለ ፡ በጅሮንድ ፡ አደፍርሰው ፡ « እኛ ፡ ሁለታች
ንና ፡ እንደዚሁም ፡ ምን ፡ እንደበላቸው ፡ ያልታወቀው ፡
እነ ፡ በጅሮንድ ፡ ደጀኔ ፡ እያደፈጥን ፡ ጠላትን ፡ ስናጠቃ ፡
አስራ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ያህል ፡ ሳንለያይ ፡ ቆየን ። በአስራ ፡
አምስተኛው ፡ ቀን ፡ ጠላት ፡ በከባድ ፡ መሣሪያ ፡ እየተጠ
ቀመ ፡ ገፍቶ ፡ መጣብንና ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ዋሻ ፡ ልንገባ ፡
ስንሸሽ ፡ አድፍጦ ፡ ይጠብቀን ፡ የነበረው ፡ ጠላት ፡ እሩ
ምታውን ፡ ለቆብን ፡ ባልሽ ፡ እጭኑ ፡ ላይ ፡ ተመትቶ ፡
ወደቀ ። እኛንም ፡ ለመድገም ፡ ሞክረው ፡ ሳይሆንላቸው ፡
ከመቅረቱም ፡ ሌላ ፡ በጅሮንድ ፡ ደጀኔ ፡ አንዲት ፡ ጉሬ ፡
ውስጥ ፡ አድፍጠው ፡ እኛን ፡ ይከተል ፡ የነበረውን ፡ ጠላት ፡
ካሳለፉት ፡ በሁዋላ ፡ አስቀድመው ፡ ከጠላቶች ፡ በማረኩዋ
ቸው ፡ ሁለት ፡ የእጅ ፡ ቦንቦች ፡ ከሁዋላ ፡ ለቅቀውባቸው ፡
አንዱ ፡ ባንደኛው ፡ ላይ ፡ ሲረባረብ ፡ እኛም ፡ ቶሎ ፡ ደር

ሰን ፡ በጦርና ፡ በጎራዴ ፡ ጨፍጭፈናቸው ፡ የያዙዋቸውን ፡ ጠመንጃዎች ፡ ማርከን ፡ ወደ ፡ አቶ ፡ ወንድይፍራው ፡ ተመለስን ።

አቶ ፡ ወንድይፍራው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አልሞተም ፡ ነበር ። «አይ ፡ ልጄ ፡ ኤፍሬም ! አይ ፡ የአይኔ ፡ አበባ ! » ብሎ ፡ እያቃሰተ ፤ « ልጄስ ፡ በእድሉ ፡ ማደግ ፡ ይችላል ። የዓይኔ ፡ አበባም ፡ ለጊዜው ፡ እንጂ ፡ ከኔ ፡ ከድህ ፡ ኑሮ ፡ ተገላገለች ፡ ማለት ፡ ነው ። በጣም ፡ የሚያሳዝነኝ ፤ አገሬን ፡ ለመውረር ፡ የመጣውን ፡ ጠላት ፡ ድል ፡ ሳልመታ ፡ መቀረቴን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በጉንፋን ፡ ልሞት ፡ የምችለው ፡ ሰው ፡ እዚህ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ መሞት ፡ በጣም ፡ ክብሬ ፡ ነው ። እናንት ፡ ጀግኖች ! በጅሮንድ ፡ አደፍር ሰው ! ዋለልኝ ! ከኔ ፡ የሚፈሰው ፡ ደም ፡ ፍርሃትን ፡ ሳያሳድርባችሁ ፡ በይበልጥ ፡ በቆራጥነት ፡ ተዋግታችሁ ፡ ጠላታችሁን ፡ ባታጠፉ ፡ በባርነት ፡ ቀንበር ፡ ተይዛችሁ ፡ ከመኖራችሁ ፡ ያላመኖራችሁን ፡ የምትመርጡበት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚመጣ ፡ ለነጻነታችሁ ፡ ተዋጉ ። እርስታችን ፡ በሆነው ፡ ሞት ፡ የዛሬውን ፡ ቀን ፡ ለማለፍ ፡ ስትሉ ፡ ለስጋችሁ ፡ አትሳሱ ፡ » ፤ ብሎን ፡ ትንፋሹ ፡ ቀጥ ፡ አለ ፡ » « ወይኔ ፡ ዓይኔ ፡ ይፍሰስ » ! አለችና ፡ « ሬሳውን ፡ ምን ፡ አደረጋችሁት ? » ብላ ፡ ብትጠይቃቸው ፤ « መቼም ፡ ያለደረግነውን ፡ ዛሬ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገናል ፤ በክብር ፡ ቀብረነዋል ! ብንልሽ ፡



ነገ ፡ ሊዋሽበት ፡ በማይቻለው ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ሊወቅሰን ፡ ስለሚችል ፡ እኛ ፡ ትተነው ፡ ከመሄድ ፡ ምንም ፡ ምርጫ ፡ ስላልነበረን ፡ እዚያው ፡ እወደቀበት ፡ ሳር ፡ ነጭተን ፡ እላዩ ፡ ላይ ፡ በመጣል ፡ ወደ ፡ ተግባራችን ፡ ሄድን »፤ ሲሉዋት ፡ « ወይኔ ፡ እኔን ፡ አሞራ ፡ ይብላኝ ! አልቀበራችሁትማ ! ጅብ ፡ በልቶታል ፡ ማለት ፡ ነዋ ! አይ ፡ ጉድ ! አይ ፡ ጭካኔ ! » እያለች ፡ ኡኡታዋን ፡ አቀለጠችው ።

እኔም ፡ « አባዬ ፡ ሆዴ ፡ ምን ፡ አልኩህ ፡ » እያልኩ ፡ እንዳዲስ ፡ ሆነን ፡ ከእምዬ ፡ ጋር ፡ እያለቀስን ፡ አምሽተን ፡ እነ ፡ በጅሮንድ ፡ አደፍርሰው ፡ «አታልቅሱ ፡ በዚህ ፡ ዓለም የሚቀር ፡ የለም ፤ » እያሉ ፡ ያጽናኑን ፡ ጀመር ። እምዬም ፡ « አለቀ ! ተከተተ ! ቁርጡን ፡ አወቅሁት ፤ ባሌ ፡ ወንደይፍራው ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ አሞራ ፡ በልቶታል ! እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ካፈር ፡ ቆንጥሮ ፡ ሲፈጥረው ፡ አፈር ነህና ፡ ወደ ፡ አፈር ፡ ትመለሳለህ ፡ ብሎታል ፡ እያሉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደተጻፈ ፡ ያወራሉ ። ታዲያ ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምን ፡ ቃል ፡ አባይ ፡ ሆነ ? ለምን ፡ ባሌን ፡ አሞራ ፡ እንዲበላው ፡ አደረገ » ? እያለች ፡ የደም ፡ እንባ ፡ ታነባ ፡ ጀመር ። ካባቴ ፡ ሞት ፡ ይልቅ ፡ የእምዬን ፡ መጎሳቆልና ፡ ከሰውነት ፡ ደረጃ ፡ መውጣት ፡ እመለከትና ፡ መፈጠሬን ፡ እስከመጥላት ፡ እደርስ ፡ ነበር ። መፈጠርን ፡ መጥላት ፡ አለመፈጠርን ፡ ሊያስከትል ፡ አይችልምና ፡ ችግሩ ፡ አልተቃለለም ።

እምዬ ፡ ባለቀሰች ፡ ቁጥር ፡ እያጀብኩዋት ፡ ጎጆአ
ችን ፡ የለቅሶ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ።

እምዬ ፡ እኔን ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ ሰጥታኝ ፡ ወደ ፡ ዘመ
ዶችዋ ፡ ከመሄድ ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ዘዴ ፡ ስላልነበራት ፡
ይህንኑ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ታማክረኝ ፡ ጀመር ። እኔ ፡
ግን ፡ ከስዋ ፡ የመለየቱን ፡ አሳብ ፡ ጨርሼ ፡ አልወደድኩ
ምና ፡ «ለማን ፡ ልትሰጭኝ ? ማን ፡ ሊቀበልሽ » ? ብዬ ፡
መላልሼ ፡ ጠየቅሁዋት ። መልስ ፡ ሳትሰጠኝም ፡ ጭጭ ፡
ብላ ፡ ዓይን ፡ ዓይኔን ፡ ትመለከተኝ ፡ ጀመር ። እንባዋ ፡
ይፈስሳል ።

በዚሁ ፡ አሳብ ፡ ስንተራመስ ፡ እያለን ፡ መንግሥት ፡
በጦር ፡ ሜዳ ፡ የሞቱትን ፡ ጀግኖች ፡ ልጆች ፡ ባዳሪነት ፡
ተቀብሎ ፡ ያስተምራል ፡ ሲባል ፡ ሰማች ፤ በጣም ፡ ተደሰ
ተች ። ውላ ፡ ሳታድር ፡ ላባላባቱ ፡ አመልክታ ፡ ባላባቱም ፡
እምዬን ፡ ለመርዳት ፡ ባስቸኳይ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡
ተጻጽፎ ፡ በአስራ ፡ አንድ ፡ ዓመቴ ፡ ባዳሪነት ፡ ት/ ቤት ፡
ልገባ ፡ ቻልኩ ። እምዬም ፡ ወደ ፡ ዘመዶችዋ ፡ ሄዳ ፡ ከሰነ
በተች ፡ በሁዋላ ፡ ጎጆአችን ፡ እንዳይፈርስና ፡ ንብረታችን፣
እንዳይነጠቅ ፡ የወንድሙዋን ፡ ልጅ ፡ ይዛ ፡ ተመልሳ ፡ ከስ
ድስት ፡ አመት ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ የብቸኝነት ፡ ኑሮዋን ፡ ጀመ
ረች ። ትምህርቴን ፡ ቀጠልኩ ። አንድም ፡ ቀን ፡ እንድለ
ያት ፡ የማትፈልገው ፡ እናቴ ፡ ሳላያት ፡ አራት ፡ አመት ፡
ቆየሁ ። በአስራ ፡ አምስት ፡ አመቴ ፡ ገና ፡ አራተኛ ፡ ክፍል፡



ሆኜ ፡ እምዬ ፡ በጠና ፡ ታምማ ፡ « ልጄን ፡ ሳላይ ፡ መሞቴ፡
ነው ፡ » እያለች ፡ በማልቀስ ፡ ጎረቤቱን ፡ ሁሉ ፡ አስቸገረ
ችና ፡ በበጅሮንድ ፡ አደፍርሰው ፡ አማካይነት ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ ተላከብኝ ። ሲነገረኝ ፡ እንዳልደነግጥ ፡ ብዙ ፡ ጥን
ቃቄ ፡ እንዲደረግ ፡ አደራ፡አለች ። መልክተኛው ፡ አራት ፡
ቀን ፡ በሙሉ ፡ በበቁሎ ፡ ተጉዞ ፡ እኔ ፡ ዘንድ ፡ ደረሰ ። ገና ፡
ሳየው ፡ ተሸበርኩ ። የምናገረውን ፡ እስከማጣት ፡ ተርበት
ብቼ ፡ ሲያየኝ ፡ እሱም ፡ ደነገጠ ። « ምን ፡ ነካህ ፡ ? ለምን ፡
ደነገጥህ ? አለኝ ። » እኔም ፡ « እኔ ፡ እንጃ ! ብቻ ፡ ገና ፡
ሳይህ ፡ ላብ ፡ አሰመጠኝ ፤ ለመሆኑ ፡ እምዬ ፡ ደህና ፡ ነች ?»
ስል ፡ ጠየቅሁት ። « በጣም ፡ ደህና ፡ ነች ፡ ግን ፡ ናፍቆኛ
ልና ፡ ካላየሁት ፡ ብላ ፡ ጎረቤቱን ፡ ሁሉ ፡ ግራ ፡ አጋባችው ፤
ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃድ ፡ ጠይቀህ ፡ ብትሄድና ፡ ብታ
ይህ ፡ » ሲል ፡ መለሰልኝ ። ከፊተኛው ፡ ይበልጥ ፡ በመደን
ገጥ ፡ « ምን ፡ ልታሰማኝ ፡ ፈልገህ ፡ ነው ? » በማለት ፡ ወደ
ሱ ፡ ስመለከት ፡ እንባዬ ፡ ሳላውቀው ፡ ይወርድ ፡ ጀመር ።
እንዴ ! ምን ፡ ነካህ ? እኔ ፡ እንደሆን ፡ የቀን ፡ ስራን ፡ ለመ
ፈለግ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስመጣ ፡ እግረ ፡ መንገዴን ፡ ልካኝ ፡
ነው ፡ እንጂ ፡ ለዚህ ፡ ብዬ ፡ አለመጣሁም ፡ ምነው ፡ ተማሪ፡
አይደለህም ፡ እንዴ ? እንዴት ፡ ሆድ ፡ ይብስሃል ? » ብሎ ፡
ድርቅ ፡ አለብኝ ። ልቤ ፡ ተከፈለ ። መልሼ ፡ « የእምዬ ፡
ጤና ፡ እንዴት ፡ ነው ? እኔ ፡ እንደሆነ ፡ አሁን ፡ ትምህር
ቴን ፡ ትቼ ፡ አልሄድም ፡ » ስል ፡ አግባባሁት ፡ « አይ ፡

ጤናዋስ ፣ ደህና ፣ ነው ፣ ግን ፣ በሰሞኑ ፣ እንደጉንፋን ፣ አድርጎ ፣ አመመኝ ፣ ብላ ፣ ተኝታ ፣ ሰነበተች ። አሁን ፣ ግን ፣ ደህና ፣ ነች » አለኝ ፣ በረድ ፣ አድርጎ ፤ ተመልሶ ፣ የነበረው ፣ መንፈሴ ፣ እንደገና ፣ ተናወጠ ። ከቆምኩበት ፣ ስፍራ ፣ ሳላውቀው ፣ ወደቅሁ ። ሞታ ፣ የሚያረዳኝ ፣ እንጂ ፣ እውነትም ፣ በሕይወት ፣ ያለች ፣ አልመሰለኝም ። ቀስ ፣ ብሎ ፣ አጠገቤ ፣ ለነበረው ፣ ጉዋደኛ ዬም ፣ « ታማለች ፣ » ብሎ ፣ ሹክ ፣ ሲለው ፣ ጆሮኤ ፣ ውስጥ ፣ ጥልቅ ፣ አለ ። እሪ ፣ አልኳ ! ። የሚሉኝን ፣ መስማት ፣ አልቻልኩም ! ጓደኞቼ ፣ ከግራና ፣ ከቀኝ ፣ ከበውኝ ፣ « ምን ፣ ነካህ ! እናትህ ፣ ጉንፋን ፣ ያዛቸው ፣ ስትባል ፣ እንደዚህ ፣ የተርበተበትከው ፣ ቢሞቱ ምን ፣ ልትሆን ፣ ነው » ? እያሉ ፣ ከበድ ፣ ያሉትን ፣ ቃላት ፣ ይጥሉብኝ ፣ ጀመር ። አዬ ፣ ፍርጃ ! እርር ፣ ድብን ፣ አልኩ ! ጓደኞቼ ፣ ወቀሳ ፣ ሲበያዙብኝ ፣ አንዴ ፣ የሆነው ፣ ሆነ ፤ ቁርጡን ፣ ልወቀው ፣ በማለት ፣ ወደናቴ ፣ ለመሄድ ፣ ፈቃድ ፣ ተቀበልኩ ። የስምንት ፣ ቀን ፣ ፈቃድ ፣ አገኘሁና ፣ መልክቱን ፣ ያደረሰልኝ ፣ ሰውዬ ፣ እዚያው ፣ ትቼው ፣ በመጣደፍ ፣ ጉዞኤን ፣ ቀጠልኩ ።

ከ፫፻ ፣ ኪሎ ፣ ሜትር ፣ የመኪና ፣ መንገድ ፣ ሌላ ፣ የ፲ ፣ ኪሎ ፣ ሜትር ፣ የእግር ፣ መንገድ ፣ አለው ። በእቃ ፣ መጫኛ ፣ ከባድ ፣ መኪና ፣ ተሳፍሬ ፣ በሁለት ፣ ቀኔ ፣ ወደ ፣ እናቴ ልደርስ ፣ ቻልኩ ። ከመግባቴም ፣ በፊት ፣ ይለቀስ ፣ እንደ



ሆነ ፣ ለማዳመጥ ፣ በጣም ፣ ዝግ ፣ እያልኩ ፣ እራመድ ፣ ጀመር ። ምንም ፣ ለቅሶ ፣ የለም ። መራመድ ፣ በፍጹም ፣ አቅቶኝ ! ስወላገድ ፣ ገብቼ ፣ እምዬን ፣ በሕይወት ፣ አገኘሁዋት ! ። ግን ፣ በጠና ፣ ታማለች ! እያለቀስኩ ፣ አጠገብዋ ፣ ሄጄ ፣ ተቀመጥኩ ። « ምነው ፣ ለምን ፣ ታለቅሳለህ ? በጣም ፣ ተሽሎኛልኮ » አለችኝ ፣ በጣም ፣ በደከመ ፣ ቃል ። ግን ፣ አይን ፣ አይኔን ፣ እያየች ፣ እንባዋን ፣ ታፈስ ፣ ጀመር። ምን ፣ ልሁን ! እምን ፣ ውስጥ ፣ ልግባ ! በጣም ፣ ተዳከመች ፤ አያቴና ፣ ጎረቤቶቹ ፣ ቁጭ ፣ ብለው ፣ ያስታምሙዋታል ። የሰነበተችበትን ፣ ሁናቴ ፣ ብጠይቃቸው ፣ እየተዳከመች ፣ መሄድዋን ፣ ገለጡልኝ ። ከጀመራት ፣ ጊዜ ፣ አንስቶ ፣ አንድም ፣ ቀን ፣ እንቅልፍ ፣ ያልተኛችና ፣ አስታማሚዎቹም ፣ ካሰር ፣ ለሊት ፣ የበለጠ ፣ ቁጭ ፣ ብለው ፣ ይጠብቁዋት ፣ ስለነበረ ፣ ባለመተኛታቸው ፣ ከስዋ ፣ ያላነሰ ፣ እነሱ ፣ በእንጥልፍ ፣ በሽታ ፣ የተሰቃዩ ፣ መሆናቸውን አስረዱኝ ። እምዬ ፣ የመዳን ፣ ተስፋ ፣ ስላልነበራት ፣ ቶሎ ፣ ብትገላገል ፣ እያሉ ፣ ሞትዋን ፣ ይመኙ ፣ ጀመር ። ቀኑ ፣ አለቀና ፣ የምሽቱ ፣ ሰዓት ፣ ተተካ ። ለሊቱን ፣ በሙሉ ፣ በጭንቅና ፣ በመከራ ፣ ወዲህ ፣ ስናገላብጥ ፣ ወዲያ ፣ ስንል ፣ ቁጭ ፣ ብለን ፣ አደርን ። ጠዋት ፣ አጠገብዋ ፣ እንደተቀመጥኩ ፣ ሳለቅስ ፣ አይታ ፣ « ኤፍሬም ! ኤፍሬም ! » ብላ ፣ ጠራችኝ ። « ምነው ፣ እማዬ ! » አልኩዋት ፤ « ማልቀስ ፣ አያስፈልግም ፤ ከሞት ፣ የሚድን ፣ የለም ። ይህን ፣

ያህል ፡ በመከራ ፡ እንዳሳልፈው ፡ ሲፈጥረኝ ፡ ለኔ ፡ ማልቀስ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ አረፍኩት ፡ ማለት ፡ ነው ። ምንም ፡ እዳ ፡ የለብኝም ፤ እናትህ ፡ ንጹህ ፡ ደሀ ፡ ነኝ ።

እርግጥ ፡ ነው ፤ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዋጋ ፡ በሌለው ፡ አሳብ ፡ ስታመስ ፡ ኖርኩ ። አንተ ፡ ተምረህ ፡ ቀን ፡ ታወጣልኝአለህ ፡ እያልኩ ፡ በመጉዋጉዋትና ፡ ሰውነቴን ፡ በማታለል ፡ ላይ ፡ እያለሁ ፡ ይኸውና ፡ ቀኔ ፡ ደርሶ ፡ ይተናነቀኛል ። አስብ ፤ እጨነቅም ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከመክሳት ፡ ኮሳሳ ፡ ሆኜ ፡ ከመታየት ፡ በቀር ፡ አስቤ ፡ ያተረፍኩት ፡ ጥቅም ፡ የለም ። አትዘን ፡ አታስብ ፤ መጨነቅ ፡ አያስፈልግም ። ምናልባት ፡ ጽድቅ ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ ለሀገሩ ፡ የሞተውን ፡ ባሌን ፤ አሳቢዬ ፡ ሕይወቴን ፡ አግኝቼ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ስፍራ ፡ ይኖረን ፡ ይሆናል ። ይህም ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ የፈጠረው ፡ ምኞት ፡ ነው ። ልጄ ! ለአሳብ ፡ ዋጋ ፡ አትስጠው ፤ በማሰብ ፡ ሰውነትህን ፡ አታስጨንቅ ። ትምህርትህን ፡ ቀጥለህ ፡ በተቻለህ ፡ መጠን ፡ ጊዜው ን ፡ ምሰል ፡ » ብላኝ ፡ ንግግርዋን ፡ አቋረጠች ።

ሰውነትዋ ፡ እየቀዘቀዘ ፡ የመተንፈስ ፡ ሀይልዋ ፡ እየደከመ ፡ ይሄድ ፡ ጀመር ። እኔም ፡ ዘመድ ፡ አዝማዱም ፡ ተስፋ ፡ ቆረጥን ። ሀሙስ ፡ ጠዋት ፡ ልክ ፡ በአራት ፡ ሰአት ፡ በተወለደች ፡ በ፵፫ ፡ አመትዋ ፡ ሕይወትዋ ፡ አለፈ ። ቁር



ጡን ፡ አወቅሁት ! ከዚያ ፡ ወዲያማ ፡ ምኑ ፡ ቅጡ ! ተቃጠልኩ ! ። አያቴና ፡ እኔ ፡ ፈጽሞ ፡ ግራ ፡ ገብቶን ! እንተያይ ፡ ጀመር ። እዬዬው ፡ ቀለጠ ! እኔ ፡ ለናቴ ፡ አንድ ፡ እምዬም ፡ ላያቴ ፡ አንድ ፡ ስለነበረች ፡ « አያቴ ፡ መተኪያ ፡ የሌለሽ ፡ ልጄ » እያለች ፡ ስታለቅስ ፡ እምዬ ፡ ለኔም ፡ መተኪያ ፡ የሌላት ፡ አለኝታዬ ፡ ነበረች ።

እምዬን ፡ በማስታመም ፡ ለብዙ ፡ ቀናት ፡ በእንቅልፍ በሽታ ፡ የተቸገረው ፡ ጎረቤት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳይወስዱ ፡ መቃብር ዋን ፡ በቶሎ ፡ አፋጥነው ፡ ወስደን ፡ ቀበርን ። የእምዬ ፡ ነገር ፡ አለቀ ! ተከተተ ! አልቅሼ ፡ ምንም ፡ እንደማላገኝ ፡ ተረዳሁ ። ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ በድን ፡ ሆነ ፤ ቢጠሩኝ ፡ የማልሰማ ፡ ዓይኖቼ ፡ እያዩ ፡ የማላስተውል ፡ ሆንኩ ። « አታስብ ፡ አትጨነቅ ፡ » ትለኝ ፡ የነበረውን ፡ ትዝ ፡ ይለኛል ። የነበረችበትን ፡ ችግርና ፡ ጭንቅ ፡ ሳስብ ፡ ያንገበግበኛል ። ጠግቤ ፡ ያላየሁዋቸው ፡ ጠግበው ፡ ያላዩኝ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ በሞት ፡ ተለይተውኝ ፡ ብቻዬን ፡ ቀረሁ ።

ልብሴ ፡ ሁሉ ፡ በእንባ ፡ እየታጠበ ፡ ከአያቴ ፡ ጋር ፡ እስከ ፡ አምስ ፡ ቀን ፡ ሰነበትኩና ፡ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ አያቴን ፡ ተሰናብቼ ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤቴ ፡ ጉዞዬን ፡ ቀጠልኩ ።

የሁለት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ የድካም ፡ ጉዞ ፡ ተጉዤ ፡ አደራውን ፡ እንደጣለ ፡ ሰው ! የያዘውን ፡ እቃ ፡ እንዳ

ጠፋ ፣ ሰው ፣ ተጨንቄ ! ቅስሜ ፣ ተሰብሮ ፤ ፈቃድ ፣ ተቀብዬ ፣ በወጣሁ ፣ በዘጠነኛው ፣ ቀኔ ፣ ወደ ፣ ትምህርት ፣ ቤቴ ፣ ደረስኩ ። ጉዋደኞቼን ፣ ሳይ ፣ የባሰውን ፣ እሪ ፣ አልኩ ። ሁሉም ፣ በየተራ ፣ እየመጣ ፤ እናቱ ፣ ያልሞተችበትም ፣ ጭምር ፣ « ምነው ፣ ታገስ ፣ እንጂ ! ሰንቶቻችን ፣ እናቶቻችንን ፣ ቀብረን ፣ ተቀምጠናል ፤ ሞት ፣ እንደሆነ ፣ የማይቀር ፣ የዘላለም ፣ እርስት ፣ ነው ። አዲስ ፣ ነገር ፣ እንዲሆንብህ ፣ አያሻምና ፣ ማንኛውም ፣ ነገር ፣ እንደመልኩ ፣ መያዝ ፣ ነው ፣ » እያሉ ፣ ለማጥናናት ፣ ሞከሩ ። ሌላውስ ፣ ይቅር ! « ቀን ፣ ታወጣልኝ ፣ ይሆናል ፣ » እያለች ፣ ተሻሽላ ፣ ለመኖር ፣ ተስፋ ፣ በማድረግ ፣ ላይ ፣ የነበረችው ፣ እምዬ ! ምንም ፣ ቀን ፣ ሳይወጣላት ! አፈር ፣ ሆና ፣ ስትቀር ፣ ዴት ፣ ልርሳት ?

በይበልጥ ፣ ያንገበግበኝ ፣ የነበረው ፣ በሕጻንነቱ ፣ አቅፋኝ ፣ ቁጭ ፣ ብላ ፣ የኔን ፣ ፍሬ ፣ ሳታይ ፣ እንደምትሞት ፣ ተገልጾላት ፣ « ለኔም ፣ ቀን ፣ ታወጣልኛለህ ፣ አባትህም ፣ ግራ ፣ ገብቶታልና ፣ ትጠረናለህ ፤ ግን ፣ ላይሆንም ፣ ይችላል » ያለችኝን ፣ ሳስታውስ ፣ ነው ። ገና ፣ ተማሪ ፣ ሆኜ ፣ በአሳብ ፣ ብቻ ፣ ትምህርቴን ፣ በመጨረስ ፣ እምዬን ፣ እያጌጥኩ ፣ እደሰት ፣ ነበር ። አሁን ፣ ግን ፣ ለእኔም ፣ ቀን ፣ ማውጣቴ ፣ ያጠራጥራል ። ሁሉም ፣ ነገር ፣ ነገ ፣ አገኛዋለሁ ! ነገ ፣ እጨብጠዋለሁ ፣ ሲባል ፣ ነው ፣ የሚያመልጠው ፤ ስለዚህ ፣ በመነመነ ፣ ተስፋ ፣ ሕይወቴን ፣ እገፋው ፣ ጀመር ።



እምዬ ፣ በሞተች ፣ በሰልሳ ፣ ሁለተኛው ፣ ቀን ፣ ለሊት፣ ተኝቼ ፣ በህልም ፣ ታየችኝ ። ትምህርቴን ፣ ጨርሼ ፣ በሥራ ላይ ፣ ያለሁ ፣ ይመስለኛል ። በጣም ፣ ግሩም ፣ የሆነ ፣ ቤት ፣ ተከራይቼ ፣ በደንበኛ ፣ የቤት ፣ እቃ ፣ ተሽቆጥቁጦአል ። በሰአት ፣ ከስራ ፣ እንደገባሁ ፣ እምዬ ፣ አደፍ ፣ ያለ ፣ የአገር፣ ልብስ ፣ ለብሳ ፣ ብቅ ፣ አለች ። በሀይል ፣ ደነገጥኩና ፣ ትኩር ፣ ብዬ ፣ አየሁዋት ። « እምዬ ! ለካስ ፣ ሞታለች ፣ እያልኩ ፣ አለቅስ ፣ የነበረው ፣ በህልሜ ፣ ነበር ? ምን ፣ ልሁንልሽ ! እንኳን ፣ በደህና ፣ መጣሽልኝ ፣ ጉዋደኞቼን ፣ በሙሉ ፣ አልቅሼ ፣ ሳስለቅሳቸው ፣ ነበርኩ ፣ » ብያት ፣ አቅፌ ፣ ሳምኩዋትና ፣ « ይኸውልሽ ! ድሮ ፣ ቀን ፣ ታወጣልኝ ፣ ይሆናል ፣ እያልሽ ፣ ተስፋ ፣ ታደርጊ ፣ እንደነበረው ፣ ከአሁን ፣ ጀምሮ ፣ ችግር ፣ የለም ። የወር ፣ ደመወዜ ፣ ሶስት፣ መቶ ፣ አምሳ ፣ ብር ፣ ስለሆነ ፣ ላንቺ ፣ በየወሩ ፣ አንዳንድ ፣ መቶ ፣ ብር ፣ ይዤልሽ ፣ እመጣለሁ ፤ ወይም ፣ እልክልሻለሁ ። እስኪ ፣ አሁን ፣ ምሳ ፣ በልተን ፣ ወደ ፣ ገበያ ፣ እንሂድና ፣ የከተማ ፣ ልብስ ፣ ልግዛልሽ ፣ » እላት ፣ ጀመር ። ይህን ፣ ሁሉ ፣ ስለፈልፍ ፣ አንድም ፣ መልስ ፣ አልሰጥ ፣ አለችኝ ፤ ለምን ፣ ቅር ፣ ተሰኘችብኝ ፣ ብዬ ፣ ላባብላት ፣ ተነሳሁ ፤ ምንም ፣ ለውጥ ፣ አላሳየችኝም ። ዱሮ ፣ ሳኮርፍ ፣ ታባብለኝ ፣ ስለነበረ ፣ አሁንም ፣ ብታባብለኝ ፣ ብዬ ፣ መነጋገሩን ፣ ተውኩ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ፊትዋን ፣ አዙራ ፣ የአባቴን ፣ ስም ፣ እየጠራች ፣ ታለቅስ ፣ ጀመር ። ሲጨንቀኝ ፣ ጊዜ ፣

መልሼ ፡ ላባብላት ፡ ወደ ፡ እስዋ ፡ ተጠጋሁና ፡ « ምነው ፡ እምዬ ! አባቴ ፡ የኔን ፡ ማዕረግ ፡ ሳያይ ፡ በመሞቱ ፡ አዝነሽ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ምን ፡ የበደልኩሽ ፡ ነገር ፡ አለና ፡ ነው ፡ የምታለቅሽው ? አባባ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ ተጠራበት ፡ ሄደ ። የሰማዩ ፡ ጌታ ፡ ነፍሱን ፡ ይማረው ፡ እያልን፡ በዚህ ፡ አለም ፡ ለመኖር ፡ እስከተፈቀደልን ፡ ጊዜ ፡ ድረስ፡ ለራሳችን ፡ ኑሮ ፡ እናስብ ። እኛስ ፡ እንሞት ፡ የለምን ? » በማለት ፡ ላይ ፡ እያለሁ ፡ አባቴ ፡ መልኩ ፡ ፈጽሞ ፡ ተለውጦ ፡ ወዙ ፡ ጨርሶ ፡ ጠፍቶ ፡ ከስቶና ፡ ገርጥቶ ፡ ብቅ ፡ አለ ! ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መናገር ፡ አቃተኝ ፤ ተርበተበትኩ ። እኔን ፡ አላናግር ፡ ብላኝ ፡ የነበረችው ፡ እምዬ ! አባቴን ፡ ስማ ፡ ተቀበለችውና ፡ እጁን ፡ ይዛ ፡ ተቀመጠች ። ፈጽሞ ፡ የምለውን ፡ አጣሁ ፡ ግራ ፡ ገባኝ ። እነሱን ፡ እመለከትና ፡ መልሼ ፡ የገዛ ፡ ሰውነቴን ፡ እመለከት ፡ ጀመር ። ቆይቶም ፡ ለካስ ፡ አባትና ፡ እናቴ ፡ በሕይወታቸው ፡ እያሉ ፡ ሞታቸውን ፡ እመኝ ፡ ነበር ? አላናግር ፡ የሚሉኝም ፡ ለዚህኮ ፡ ነው ! እያልኩ ፡ ራሴን ፡ ወቀስኩ ። አባቴም ፡ እንደናቴ ፡ እኔን ፡ ዝም ፡ ብሎኝ ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይነጋገራሉ። ሆኖም ፡ ከንፈሮቻቸው ፡ ሲንቃነቁ ፡ እንጂ ፡ የሚሉትን ፡ መስማት ፡ አልቻልኩም ። ወደነሱ ፡ ተጠጋሁ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ድምፅ ፡ የለም ። በእሩቅ ፡ ለሚመለከት ፡ ሰው ፡ በሀይል ፡ ተጨንቀው ፡ የሚያወሩ ፤ ስለኔም ፡ የሚናገሩ ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ። ጨርሶ ፡ ግራ ፡ ሲገባኝ ፡ « አባባ ! እማዬ !



እኔ ፡ ለዚህ ፡ ደረጃ ፡ ደርሼላችሁ ፡ ስታዩኝ ፡ ሰርጋችሁ ፡ ዛሬ ፡ እንደሆነ ፡ ቆጥራችሁት ፡ በመደሰት ፡ ፋንታ ፡ በጣም፡ የመተከዝ ፡ መልክ ፡ የሚታይባችሁ ፡ ለምንድር ፡ ነው ? አላናግር ፡ አላችሁኝ ፤ የበደልኩአችሁ ፡ ነገር ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ። ገና ፡ አሁን ፡ ሥራ ፡ ጀመርኩ ፡ እንጂ ፡ ደመወዝ ፡ አልበላሁ ። ተነገ ፡ ወዲያ ፡ ደመወዜን ፡ እቀበልና ፡ ለናንተው ፡ አስረክባችሁአለሁና ፡ አትቀየሙኝ ! እንዲያውም ፡ በሀይል ፡ እናንተን ፡ ከመናፈቅ ፡ የተነሳ ፡ አንተ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ አንቺ ፡ እማዬ ፡ በበሽታ ፡ የሞታችሁ ፡ መስሎኝ ፡ ሳለቅስና ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ጉዋደኞቼን ፡ ሁሉ ፡ ሳስለቅስ ፡ ይኸውና ፡ ሰውነቴ ፡ አልቆአል ።

ድሮ ፡ ለምን ፡ ችግር ፡ ነበረብን ፡ አትበሉ ። ችግርና ፡ ደስታ ፡ ካልተፈራረቁ ፡ የደስታ ፡ ዋጋ ፡ አይታወቅም ። ለወደፊቱ ፡ ትደሰታላችሁ ። ላለፈው ፡ አትዘኑ ፡ » እያልኩ ፡ ላባብላቸው ፡ ወደነሱ ፡ ስጠጋ ፡ ከእንቅልፍ ፡ ባነንኩ ። አዬ ! አዬ ! ጭንቄን ፡ በምን ፡ አባባል ፡ ልግለጠው ! « በስመ ፡ አብ » ብል ! በጭለማ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ብመለከት ! ምኑ ፡ ቅጡ !

ራሴን ፡ ተጠራጠርኩት ። በህልም ፡ የማየውን ፡ በውኔ ፡ ሲመስለኝ ፤ በውኔ ፡ ያየሁት ፡ ደግሞ ፡ በህልም ፡ እየመሰለኝ ፡ ስጨነቅና ፡ ፈጽሞ ፡ ግራ ፡ ሲገባኝ ፤ የቱን ፡ ልመን ? ከዚያ ፡ ወዲያማ ፡ ቀን ፡ የማየውን ፡ ሁሉ ፡ በህልም ፡ ይሆናል ፡ እያልኩ ፡ እጠራጠር ፡ ጀመር ። መጠራጠሬ ፡

ለሥራ ፡ ፈትነት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ሆነኝ ፤ እምዬ ፡ «አታ ስብ ፡ አትጨነቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያላሳካው ፡ ነገር ፡ በአ ሳብ ፡ አይገነባም ፡ » ትለኝ ፡ የነበረውን ፡ ባስታውስም ፡ የምይዘውን ፡ ያሳጣኝ ፡ ጀመር ። ትምህርቴ ፡ ሁሉ ፡ በህ ልሜ ፡ ይሆናል ፡ እያልኩ ፡ መጠራጠር ፡ ውስጥ ፡ ገባሁ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የምማረው ፡ አልጥም ፡ አለኝ ። ስጠራ ፡ እንኳን ፡ ጆሮኤ ፡ እየሰማ ፡ በህልሜ ፡ ይሆናል ፡ እያልኩ ፡ ለጥሪው ፡ መልስ ፡ የማልሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ነበርና፡ እወቀስ ፡ ነበር ። ወቀሳው ፡ ራሱ ፡ ምናልባት ፡ በህልሜ ፡ ይሆናል ፡ እያልኩ ፡ ለማናቸውም ፡ ጭቅጭቅ ፡ ዋጋ ፡ መስ ጠቱን ፡ ተውኩ ። እንቅፋት ፡ ቢመታኝ ፡ በህልሜ ! ቢር በኝ ፡ በህልሜ ! ምኑ ፡ ቅጡ ! ስለዚህ ፡ ትምህርቴን ፡ አቋ ዋርጬ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እንከራተት ፡ ጀመር ፡ « ብማር ፡ ምን ፡ ይሠራልኛል ! ነገ ፡ መሞቴ ፡ አይቀርም ፤ አባትና ፡ እናቴ ፡ ካለመኖር ፡ ወደ ፡ መኖር ፡ ከመኖርም ፡ ወደ ፡ አለ መኖር ፡ ሲለዋወጡ ፡ ወሀ ፡ ቅዳ ፡ ወሀ ፡ መልሱ ፡ ለኔም ፡ የሚተርፍ ፡ ነው ። ቢያዝኑ ! ቢደሰቱ ! ቢራቡ ! ቢራቆቱ ፡ ቢለብሱ ፤ ቢያጌጡ ፤ ሞት ፡ እንደሆን ፡ የማይቀር ፡ ነው ። ከሆን ፡ ታዲያ ፤ ለዚህ ፡ ዋስትና ፡ ለሌለው ፡ እድሜ ፤ ይህ ንን ፡ ላጥና ! ያንን ፡ እያልኩ ፡ የምበጠብጠው ፡ ለምንድነው ? በአሳብ ፡ መሰቃየት ፡ አልፈልግም ። እስከ ፡ እለተ ፡ ሞቴ ፡ የትም ፡ ዞሬና ፡ ዘመዶቼን ፡ ተጠግቼ ፡ የእለት ፡ ጉርሴን ፡ አላጣም ። ነገ ፡ ለመመላለጥ ፡ ጌጥ ፡ አያምረኝም ። ክብርን፡



አልፈልግም ። የምን ፡ መማር ! » ብዬ ፡ ትምህርቴን ፡ ተው ኩና ፡ ወደተመኘሁት ፡ መንከራተት ፡ ገባሁ ። የልመና ፡ ጉርስ ፡ ቀለብ ፡ ሊሆነኝ ፡ አልቻለም ። እምዬ ፡ « ቀን ፡ ቢወጣልህ ፡ መልክህ ፡ የሚደንቅ ፡ ይሆናል ፡ » ትለኝ ፡ የነበረው ፡ እውነትነቱ ፡ እስከ ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ለማረጋ ገጥ ፡ አልተቻለም ። የምለብሰው ፡ የለኝ ። የሰውን ፡ እጅ ፡ አይቼ ፡ የምበላው ፡ ሰውነቴ ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ አይል ፡ ስለነ በረ ፡ መልኬ ፡ ሁሉ ፡ ልውጥውጥ ፡ አለ ። ዘመዶቼ ፡ ሁሉ ፡ ይርቁኝ ፡ ጀመር ። ኑሮኤም ፡ እንደ ፡ ቅዠት ፡ ሆኖ ፡ ይሰ ማኝ ፡ ጀመር ። በመጠኑ ፡ እንኩዋን ፡ ኑሮኤን ፡ የማስተካ ከል ፡ አሳብ ፡ ፈጽሞ ፡ ከአእምሮኤ ፡ ተሰወረ ። ማን ፡ መ መክሮ ፡ ይመልሰኝ ! ላለማሰብ ፡ ወስኜ ፡ መልክቴን ፡ በቶ ያትር ፡ መልክ ፡ በመሞገት ፡ ለአንባቢዎቼ ፡ አቅርቤአለሁ ።

# የመልክተኞች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ።

ኤፍሬም ፤

አሳብ ፤

በእውነቱ ፤

ታሪኩ ፤

ይነሱ ፤

መሣይ ፤

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ አለም ፤

እንደልቡ ፤



## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ።

### ኤፍሬም ፤

ኤፍሬም ! ተብያለሁ ፡ ስም ፡ አይከለከልም ፡
ጥቅም ፡ ግን ፡ የለውም !
በስም ፡ ስላጌጡ ፡ ኑሮ ፡ አይደለልም ።

በጣም ፡ ተበጠበጥኩ ፡ ጉዳቴን ፡ እዩልኝ ፡
ጤናዬ ፡ ታወከ ፡ ምነው ፡ ተረዱልኝ ።

ቀንም ፡ ሆነ ፡ ለሊት ፡ ከሰው ፡ የማይለይ ፡
በጅ ፡ የማይጨበጥ ፡ መከራን ፡ የሚያሳይ ፤

አንድ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ እኔን ፡ ያሰቀቀኝ ፡
ይህ ፡ ነው ፡ የማልለው ፡ በጣም ፡ ያስጨነቀኝ።

አጊጦ ፡ ይመጣል ፡ ሁሉንም ፡ ያሳያል ፤
ሳይሠሩ ፡ ያደክማል ፤
በምኞት ፡ ያሰክራል !
በኔማ ፡ ቀልዶአል ፡ በነፍሴ ፡ ተጫውቶአል ።

መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከኔ ፡ አይለይም !
በምኞቴ ፡ መጠን ፡ የሚሰጠኝ ፡ ነገር ፡ ከኔ ፡
ጋር ፡ አይቆይም !
ስቃይ ፡ ያሳየኛል ፡ እንቅልፍ ፡ አላገኝም ።

ሳልተኛ ፡ በውኔ ፡ እቀሰቀሳለሁ !
እበጠበጣለሁ ! ብክንክን ፡ እላለሁ !

ዓይኖቼን ፡ ገልጬ ፡ ሁሉንም ፡ አያለሁ ፤
ከሰው ፡ ጋር ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ወሬ ፡ አወራለሁ ፤
ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ እዚያው ፡ ይሁን ? አይሁን ?
እንጃ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ ፡ !
ሁከት ፡ ሲበዛብኝ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እያየሁ ፡
አምላኬን ፡ እላለሁ ።
ስለጤንነቴም ፡ በጣም ፡ እሰጋለሁ ፤
እጠራጠራለሁ ፡
ጎበዝ ፡ ምን ፡ ይሻላል ? ብክንክን ፡ ብያለሁ ።

በህልም ፡ የማየውን ፡ በውኔ ፡ ሲመስለኝ ፡
በውኔ ፡ ያየሁት ፡ በህልሜ ፡ ሲታየኝ ፡
የመኖሬ ፡ ትርጉም ፡ የጥርጥር ፡ ሆነ ፡
መንፈሴ ፡ ታወከ ፡ አሳቤ ፡ ባከነ ።

ችላ ፡ ልለው ፡ አልችል ፡ ይጐተጉተኛል ፡
አልጨብጠው ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ ይታየኛል ፤

በውኔ ፡ እቃዣለሁ ፡ ብክንክን ፡ እላለሁ ፡
በምንም ፡ አላምንም ፡ እጠራጠራለሁ ።

እስከየት ፡ ያያሉ ፡ ሰዎች ፡ ዓይኖቻችሁ !
እንደኔው ፡ ከሆኑ ፡ አውጉኝ ፡ እባካችሁ ፤

የኔማ ፡ ይደንቃል ፡ አይኖቼን ፡ አጅቦ ፡ ሰው
ነቴም ፡ ያያል ፤
መንሳት ፡ ሳያሻኝ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ይጓዛል ።

ምን ፡ ቀረኝ ! ምን ፡ ቀረኝ !

ተከፋፍሎ ፡ አልቆአል ፡ ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡
በየመስመራችው ፡ ብዙ ፡ ይጓዛሉ ፡



አይከለከሉም ፡ የትም ፡ ይደርሳሉ ፤
ድንጋጤንና ፡ ፍርሃትን ፡ ይዘው ፡ ደግሞም ፡
ይመጣሉ ።

እንደዚህ ፡ የሚያደርግ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ልረ
ዳው ፡ ሳለሁ ፡ በሕይወቴ ፡
ባላንጣ ፡ ሆነብኝ ፡ የገዛ ፡ አከላቴ ።

እስኪ ፡ አረፍ ፡ ልበል ፡ ጭፍሮቼም ፡ ይድረሱ
ሳይሰሩ ፡ ይሻሙኝ ፡ አንዳንዴ ፡ ይጐረሱ ።
(ይተኛል )

ጨልሞአል ፡ ብዬ ፡ ለማረፍ ፡ ስቃጣ ፤
ገና ፡ ጋደም ፡ ስል ፡ ጭኖ ፡ እየመጣ ፤
ይተናነቀኛል ፡ አቤት ፡ የኔ ፡ ጣጣ ።

ለምን ፡ ልንከራተት ፡ አልፈልግም ፡ ጥፋ ፡
የደሀ ፡ ቀለቤ ፡ አንተ ፡ ከንቱ ፡ ተስፋ ፡
ገለል ፡ በልልኝ ፡ አንዴ ፡ ላንቀላፋ ።

ስታንከራትተኝ ፡ በህልሜም ፡ በውኔ ፡
ወይ ፡ የምድር ፡ ደስታ ፡ ጽድቅ ፡ አይሆን ፡
ኩነኔ ፡

የመፈጠር ፡ ውጤት ፡ የመኖር ፡ ትርጉሙ ፡
እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡
አንጥፎ ፡ ሳይተኛ ፡ በቁም ፡ ካባነነ ።

መፈጠርን ፡ መጥላት ፡ ያስከትል ፡ የለምወይ ?
መጥላትስ ፡ መውደድስ ፡ መፍትሔው ፡ ይሆ
ናል ፡ ወይ ?

መላ ፡ ቅጡ ፡ ጠፋኝ ፡ ተወሳሰበብኝ !
ነገሬን ፡ ለመርሳት ፡ ብሞክር ፡ ባሰብኝ ።
ሳልሰራ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ላብ ፡ እያስመጠኝ ፤
የምሰራ ፡ ብሆን ፡ እንዴት ፡ በጨነቀኝ !

(ይነቃል)

አቤት ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ ለካስ ፡ ቅዠት ፡ ኖሮአል!
እየከፋ ፡ ሄደ ፡ ጨርሶ ፡ ብሶአል ፡
ይህ ፡ መጥፎ ፡ በሽታ ፡ እረ ፡ ምን ፡ ይሻላል ?

በህልሜም ፡ በውኔ ፡ ድቅን ፡ እያለብኝ ፡
እዩኝ ፡ ሰው ፡ አልሆንም ፡ በሽታ ፡ ላይ ፡ ጣለኝ
ምነው ፡ ምን አደረግሁ ፡ አቤቱ ፡ ገላግለኝ ።

አሳብ ፤

አይ ፡ ጉድ ! አይ ፡ ጉድ ! እጅን ፡ አለስልሶ ፡ አነጋገርን ፡ በማሳመር ፡ የማስተዛዘኛ ፡ ቃላትን ፡ ቢያዘንቡ ፡ ወይም ፡ ምላስን ፡ አሹሎ ፡ አቃቂርን ፡ ቢያወጡ ፡ ኑሮኮ ፡ መፍትሄ ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። ኑሮኮ ፡ በሥራ ፡ እንጂ ፡ በጨዋታ ፡ አይደለለም ! አታስብ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ያለመስመሩ ፡ አትጨነቅ ፡ ማለትን ፡ እንጂ ፡ አቅድ ፡ ይነስህ ፡ ፕሮግራም ፡ አይኑርህ ፡ እጅህን ፡ አለስልሰህ ፡ ተቀመጥ ፡ ስራህ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ በልማድ ፡ ይሁን፡ ማለት ፡ አይደለም ። አስብ ፡ ማለትም ፡ አንተ ፡



እንደምትለው ፡ መጨነቅና ፡ መጠበብ ፤ ሊሆን ፡ የማይችለውን ፡ ሁሉ ፡ በይሆናል ፡ መመኘትና ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ ፍሬ ፡ ከርስኪ፡የአእምሮ ፡ ተውሳክ ፡ እን ዲፈጠር ፡ ማድረግ ፡ አይደለም ።

ኤፍሬም ፤

እምዬ ፡ ገና ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሆኜ ፡ አቅፋኝ ፡ አገጭዋን ፡ ይዛ ፡ እንደተቀመጠች ፡ «ልጄ ፡ ወደፊት ፡ ቀን ፡ ታወጣልኝ ፡ ይሆናል ፤ ይህም ፡ በራሱ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ » ያለችውኮ ፡ አሳብ ፡ ዋጋ ፡ የለውምና ፡ ዋጋ ፡ በሌለው ፡ ነገር ፡ አትታመስ ፡ ስትለኝ ፡ ነበር ። እንዳለቸውም ፡ አሳብዋ ፡ ዋጋ ፡ አጥቶ ፡ ሲቀርያ ፡ ከንቱ ፡ አሳብ ፡ በተራው ፡ እኔን ፡ ሲያውክ ፡ ይገኛል ።

በእውነቱ ፤

እናትህ ፡ የሞተችው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፤ ግን ፡ ባትሞት ፡ ኖሮ ፤ አንተም ፡ ሥራ ፡ ቢኖህር ፡ እንዳለችው ፡ ቀን፡ አታወጣላትም ፡ ነበር ?

ኤፍሬም ፤

ይህስ ፡ ራሱ ፡ አሳብ ፡ የፈጠረው ፡ የይሆናል ፡ ተስፋ ፡ አይደለምን ?

በእውነቱ ፤

አይደለም ! የናትህ ፡ ዕድሜ ፡ ሊረዝም ፡ ይችል ፡ ነበር ። በ፵፫ ፡ ዓመት ፡ የመሞት ፡ ውል ፡ ኖሮአት ፡ አይደለም ። አንተም ፡ ሥራን ፡ ላለመያዝ ፡ ያደረግኸው ፡ ውል ፡ የለም ፤ ሥራ ፡ ይዘህ ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ የምትችል ፡ ስለሆነ ፡ በውንም ፡ ሆነ ፡ በህ ልም ፡ እንደዚህ ፡ በሆነልኝ ፤ እንዲህ ፡ በፈጠ ርኩ ፤ ሳልሰራ ፡ ቁጭ ፡ ብየ ፡ በበለጸግሁ ፡ ዓለ ምን ፡ በእጄ ፡ በጨበጥኩ ፡ ከሚለው ፡ ከንቱ ፡ ምኞት ፡ ጋር ፡ የሚመዛዘን ፡ አይደለም ። ቢታ ሰብ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ አለ ፤ ጨርሶ ፡ ሊሆን ፡ የማይችል ፡ ነገር ፡ እንዳለም ፡ ታው ቃለህ ፤ ወይም ፡ ማወቅ ፡ አለብህ ።

ኤፍሬም ፤

እረ ፡ ወዲያ ! መልሶ ፡ እንድጨነቅ ፡ እንድ በጠበጥ ፤ በእንቅልፍ ፡ በሽታ ፡ እንድሞት ፤ አታድርገኝ ! ውትወታው ፡ ይቆይልኝ !


ይኸው ! ይኸው !

እዩት ፡ ድቅን ፡ አለ ! አሁንስ ፡ ሰው ፡ መሰሎ፡

ይኸው ፡ ይታየኛል !

ምን ፡ አይነት ፡ ፍርጃ ፡ ነው ! መጣ ፡ ይጠጋኛል !





አይዞህ ! አይዞህ !

አትጫወትብኝ ፡ እባክህን ፡ ተወኝ ፡
ተውሳኩ ፡ በዛብኝ ፡ አቤቱ ፡ ገላግለኝ ።
ተው ! ተው !

አሳብ ፤

በመልኩ ፡ ብትይዘው ፡ ይሻልህ ፡ ነበረ ፤
ግን ፡ አይመለስም ፡ ሞኝ ፡ ካመረረ ፤
ነገርህ ፡ ያሰጋል ፡ ከፉኛ ፡ ከረረ ።

አንገትህን ፡ አንጋጥጠህ ፡ እጅህን ፡ አጣምረህ ፤
ሳትሰራ ፡ ቁጭ ፡ ብለህ ፡ በሆነ ፡ ትላለህ ።

ማማረር ፡ ሰርቶ ፡ ነው ፡ ሳይሳካ ፡ ሲቀር ፡
በልቶ ፡ ማደር ፡ የለም ፡ እጅን ፡ በማጣመር ፤

ኤፍሬም ፤

በይሆናል ፡ ምኞት ፡ እንቅልፍ ፡ ከማጣት !
ዘወትር ፡ ከመስጋት ፡ ከንቱ ፡ ከመርበትበት !
ሊጠቅመኝ ፡ አልቻለም ፡ በሃሳብ ፡ ያየሁት ።
ግን ፡ ምን ፡ አለ ?
ሁሉም ፡ በየተራው ፡ ይመከራል ፡ ይተቻል፤
ዝቅ ፡ ብሎ ፡ መገኘት ፡ ለስድብ ፡ ያመቻል ።
በልዩ ፡ አስተሳሰብ ፡ በየተራው ፡ ተቸኝ ፡
አሳቤን ፡ ሰብስቤ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚበጀኝ ፤
የምል ፡ አይደለሁም ፡
ለዚህ ፡ አልበቃሁም ፤
የሚጠቅመኝ ፡ ምክር ፡ ሆኖም ፡ አልሰማሁም ።
አስብ ፡ የሚሉኝም ፡ ከንቱ ፡ አስጨነቁኝ ፤
አታስብ ፡ የሚሉም ፡ ለጥቅም ፡ ፈለጉኝ ።



እየተንከራተትኩ ፡ በሁለት ፡ ሀይል ፡ መሀል ፤
ብክንክን ፡ ብያለሁ ፡ እምን ፡ ሥራ ፡ ልዋል ?

አባትና ፡ እናቴ ፡ በህልም ፡ አግኝቻቸው ፤
ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ቀን ፡ ላወጣላቸው ፤
ችግር ፡ የለምና ፡ አይዞአችሁ ፡ አልኩአቸው ።

ኋላም ፡ ብንን ፡ ብዬ ፡ አኳኋኔን ፡ አየሁ ፡
ህልም ፡ እንደነበረም ፡ አሳምሬ ፡ ለየሁ ።

በህልሜ ፡ አየሁት !
በወሬም ፡ ሰማሁት !
ታከተኝ ፡ ደከመኝ ፡ ውጤቱን ፡ አጣሁት ።

« የዚህ ፡ አለም ፡ ነገር ፡ ወጥመዱ ፡ ብዙ ፡ ነው
ጥበብ ፡ አይነስህ ፡ በዘዴ ፡ ታገለው » ፤
እያለች ፡ ስትመክረኝ ፡ አሳዛኝዋ ፡ እናቴ ፤
ገና ፡ በልጅነት ፡ ሳይጠና ፡ ጉልበቴ ፤
ጊዜው ፡ ደረሰና ፡ ትዝ ፡ ይለኝ ፡ ጀመረ
ዘዴውማ ፡ ከኔ ፡ ተሰውሮ ፡ ቀረ ።
የእሳት ፡ ራት ፡ ልሁን ፡ አላስብም ፡ በቃኝ ፤
እንዲያው ፡ ላይሞላልኝ ፡ ተውሳኩ ፡ አጠቃኝ ።

በእውነቱ ፤

የስንፍና ፡ ኑሮ ፡ ይበጠብጥሃል ፡
በጤናህ ፡ አይደለም ፡ ዕብደት ፡ ጀምሮሃል ።

አሳብማ ፡ ካንተ ፡ ሊለይ ፡ የሚችለው ፡
ነፍስህ ፡ ተለይታህ ፡ መሬት ፡ ስትገባ ፡ ነው ።

እንደከብት ፡ በልማድ ፡ መኖር ፡ አይቻልም ፤
ኑሮም ፡ ያለአሳብ ፡ አይስተካከልም ።

ክፉን ፡ እየሠሩ ፡ አምላክ ፡ ዓምላክ ፡ ቢሉት ፡
ያንን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ቁርጥ ፡ አርገው ፡ ካልተውት ፡

አምላክን ፡ መሸንገል ፡ ድለላ ፡ ይሆናል ፡
መልካም ፡ ተግባር ፡ እንጂ ፡ መላስ ፡ መች ፡
ያድናል ?

እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ እጅን ፡ አለስልሶ ፡
ከንቱ ፡ ቢጎለቱ ፡ በልቶ ፡ ማደር ፡ የለም ፤
ኑሮ ፡ ካልተሟላ ፡ ሰላም ፡ አይገኝም ።

የመንፈስ ፡ ጸጥታ ፡ ሊገኝ ፡ የሚችለው ፡
ጊዜውን ፡ በመምሰል ፡ ሠርተው ፡ ሲገኙ ፡ ነው ።

ሠርቶ ፡ እንደመሻሻል ፡
ሰነፍ ፡ ተጐልቶ ፡ ይመሻል ፡ ይነጋል ።

ታሪኩ ፤

ኑሮ ፡ ልማድ ፡ እንጂ ፡ ቢታገሉት ፡ አይሆን ፤
ይልቅስ ፡ ካምላክ ፡ ጋር ፡ መጣላት ፡ እንዳይሆን ፤
በሱ ፡ ስራ ፡ ገብተን ፡ መፈትፈት ፡ ይቅርብን ።

እግዜር ፡ እርዳኝ ፡ ብሎ ፡ መለመን ፡ እያለ !
ተጨነቁ ፡ የሚል ፡ ባይበዛ ፡ ምን ፡ አለ ?

ላብ ፡ ካላሰመጠህ ፡ ገርጥተህ ፡ ካላዩህ !
ቅር ፡ ከተሰኙ ፡ እንደዚህ ፡ ከጠሉህ ፤

እጅህን ፡ ስጥና ፡ ውጤቱን ፡ ተመልከት ፡
ተቀምጠህ ፡ እያለህ ፡ በአሳብ ፡ ተንከራተት ።



ኤፍሬም ፤

እረ ፡ ወዲያ ፡ ይቅር ፡ ምኑ ፡ ይታተታል !
በኔ ፡ ላይ ፡ ከሆነ ፡ ሁሉም ፡ ይበረታል ።

አሁን ፡ በኔ ፡ ገላ ፡ ስትከራከሩ ፡
የባጡን ፡ የቆጡን ፡ ብዙ ፡ ስታወሩ ፡
ለኔማ ፡ አታስቡም ! ዝቅ ፡ ብሎ ፡ መታየት ፡
ይኸው ፡ ነው ፡ ችግሩ ።

ይነሱ ፤

ጥሩ ፡ ይዘህ ፡ ነበር ፡ አሁንም ፡ አትልቀቅ ፡
ሰው ፡ መሆን ፡ ከፈለግህ ፡ ከሀሳብ ፡ ተላቀቅ ።

እንዲያው ፡ ላይሞላልህ ፤
አንስቶ ፡ አይጣልህ !
ስለራስህ ፡ ማወቅ ፡ አንተም ፡ አያቅትህ ።

መሣይ ፤

ኑሮ ፡ ብልሀት ፡ እንጂ ፡ በትግል ፡ አይሆንም ፡
ጉልበት ፡ ያለብልሃት ፡ ፍሬን ፡ አያስገኝም ።
ምንም ፡ አትጨነቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል
ቀኑ ፡ ካልደረሰ ፡ በምኞት ፡ መች ፡ ያልቃል ፡

አሳብ ፤

አንተ ፡ ከብት ፡ አይደለህ ፡ አእምሮ ፡ ያለህ ፡
ሰው !
በልተህ ፡ ለጥ ፡ እንድትል ፡ የምትመከረው ፤
የምትበላውስ ፡ ማን ፡ የሠራውን ፡ ነው ?
ስላልተግባባን ፡ ነው ፡ እኔን ፡ የጠላኸው ፤

የነመሣይ ፡ ምክር ፡ የሚያጠፋህ ፡ ነው ፤
ተገላገል ፡ አሉህ ፡ ሊበሉህ ፡ ፈልገው ፤
አሳብ ፡ የሚባለው ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሞረድ ፡ ነው ።
ከብቶቹን ፡ እያቸው ፡ በመኽርገር ፡ ተከበው !
ስለማያስቡ ፡ ያልቃሉ ፡ ተበልተው ፡
ተግጠው ፡ ተግጠው ።

ኤፍሬም ፤

ይህስ ፡ እውነትህ ፡ ነው ፡ ከከብት ፡ እሻላለሁ ፡
ለጥ ፡ ብዬ ፡ አልተኛም ፡ ጥቂት ፡ አስባላለሁ

መሣይ ፤

ብቻ ፡ ሳትጠጣ ፡ ከንቱ ፡ ትሰክራለህ ፡
በህልምህ ፡ ስትበላ ፡ በምራቅህ ፡ ብቻ ፡
ሆድክን ፡ ትሞላለህ ፡
ወፍረህ ፡ አትታይ ፡ በውንህ ፡ አልበላህ ።

አሳብ ፤

እንዴት ፡ ይወፍራል ፡ ካልሰራ ፡ ካልበላ ?
በልቶ ፡ ማደር ፡ የትአል ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በመላ !
ደክሞ ፡ መሥራት ፡ አለ ፡ ኑሮን ፡ ለማሻሻል ፤
እሱ ፡ ግን ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ይመሻል ፡ ይነጋል ፤
ተኀልቶ ፡ መላ ፡ መች ፡ ያኀለምሳል ?

ይነሱ ፤

የማትጨበጠው ፡ ግፈኛው ፡ አንተ ፡ ነህ !
ያለተኙትን ፡ በቁም ፡ በድን ፡ ታደርጋለህ !
ላልሰራም ፡ በሀሳብ ፡ ደሞዝ ፡ ትሰጣለህ ።



ምነው ፡ አትተው ፡ አሁን ፡ ይህን ፡ ደሀ !
ጭንቅ ፡ ውስጥ ፡ እየጣልክ ፡ ከሚጠማው ፡
ውሀ !

ቢሆን ፡ ብቻ ፡ ሆኖ ፡ ያንተ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡
ሲጨነቅ ፡ ይታያል ፡ ሁሉም ፡ በበኩሉ ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ አለም ፡ !

(ተከናንቦ ፡ ተቀምጦል ፡ )

መ ! ! ! ጭ ፡ ! ! !
ጭ ፡ ! ! ! ል ! ! ጥ

በእውነቱ ፤

መግባባት ፡ ይኑረን ፡ አቃቂር ፡ አይውጣ ፤
ሠርተው ፡ ያላፈሩት ፡ ከየትም ፡ አይመጣ ።

መተቻቸት ፡ ይቅር ፡ ጊዜ ፡ አይጥፋብን ፡
ለአለፈው ፡ ስናዝን ፡ መጭው ፡ አይባስብን ።

አምላክ ፡ ባይቆጣ ፡ ድንጋይ ፡ ዳቦ ፡ ነበር !
በበቅሎ ፡ እርግጫ ፡ ሰማይ ፡ ባይባረር ፤

ከማለት ፡ እንራቅ ፡ ከጥንቱ ፡ እንቆቅልሽ ፡
አቅዶ ፡ የሠራው ፤ ሠርቶ ፡ ያመለጠው ፤ ሳይለን ፡
ምን ፡ አውቅልሽ ?

መጠንቀቅ ፡ ያሻናል ፡ ሠርተን ፡ መስተካከል ፡
የገነተረውን ፡ በጥበብ ፡ በማብሰል ።
ሰው ፡ በሠራው ፡ ጥበብ ፡ ባየር ፡ ሲንፈላሰስ ፡
አንጋጦ ፡ ያየዋል ፡

እግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ ሚስጢር ፡ ይመ
ስለዋል ።

እረ ፡ ለመሆኑ ! ሁሉም ፡ በየፊናው ፡ እኩል ፡
ነኝ ፡ የሚለው ፤
ክብሬ ፡ አይነካ ፡ ብሎ ፡ የሚጮኸው ፤
ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ተረግዞ ፡
የሰውን ፡ ቅርጽ ፡ ይዞ ፡ በመወለዱ ፡ ነው ?
ካባታችን ፡ አዳም ፡ በውርስ ፡ የመጣ ፡ ነው ?
ወይስ ፡ ያልታወቀ ፡ ሌላ ፡ ሚስጢር ፡ አለው?
የወል ፡ ስም ፡ መውጣቱ ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድ
ነው ?

አዎ !

በሥነ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ሰው ፡ ነው ፤
ልዩነት ፡ ያመጣው ፡ የሀሳብ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

ታሪኩ ፤

ብዙ ፡ ዘዴ ፡ አለህ ፡ ሰውን ፡ ማታለያ ፡
በጅ ፡ የማይዳሰስ ፡ ከንቱ ፡ መደለያ ።

ምነው ፡ ብትተወው ፡ ንትርክ ፡ ባይበዛ !
ኑሮ ፡ አይደለል ፡ እንዲሁ ፡ በንዝነዛ ።

ኤፍሬም ፤

በኔ ፡ ላይ ፡ ተጫውቶአል ፡ እሰት ፡ አይባልም
ይበጠብጠኛል ፡ እረፍት ፡ አላገኝም ።

እመንገድም ፡ ስሄድ ፡ አንጎሌን ፡ አዙሮ ፡
ልቤን ፡ ጥፍት ፡ አርጎ ፡ በሙሉ ፡ ሰውሮ ።



እንካ ፡ ቅመስ ፡ ሲለኝ ፡ እንቅፋቱ ፡ ሁሉ ፡
ተሰወርኩኝ ፡ እንጂ ፡ ዓይኖቼ ፡ ያያሉ ።

እውር ፡ አልባልም ፡ አፍጥጬ ፡ አያለሁ ፡
ምን ፡ ጎደለኝ ፡ ብዬ ፡ እርዳታ ፡ አገኛለሁ ።

(ዘግየት ፡ ብሎ) ፤

አቤት ! አሻንጉሊት ፡ የልጅ ፡ መጫወቻ ፤
እንደዘመኑ ፡ ዳንስ ፡ ማርንጌ ፡ ቻ ! ቻ ! ቻ !
የሰነፍ ፡ ተፈጥሮ ፡ እንዲያው ፡ ምኞት ፡ ብቻ ፡

ዓይን ፡ አንዱጋ ፡ ሲያይ ፡ ሰውነት ፡ ሌላ ፡ ዘንድ ፡
ጠዋት ፡ ሆነ ፡ ማታ ፤
በሃሳብ ፡ መነከር ፡ ትርፉ ፡ ለበሽታ ፤

ጉድ ፡ ነው !

በገዛ ፡ ሥራዬ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ መገረም ፡
አይ ፡ አለመሻሻል ፡ አይ ፡ አለመታረም !

ለነገሩ ፡ ያህል ፡ ሁለት ፡ ዓይንን ፡ ይዘን ፡
ለሊት ፡ ተኝተን ም ፡ ብዙ ፡ እናያለን ።

የባጡን ፡ የቆጡን ፡ አንዱንም ፡ ላንይዘው ፤
የጭለማ ፡ ጉዞ ፡ ምንም ፡ ሳያግደው ፡
ሲመላለስ ፡ ያድራል ፡ እንቅፋትም ፡ የለው ፤
አሳብ ፡ የሚባለው ፡ የደሀ ፡ ቀለብ ፡ ነው ።

<u>ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፤</u>

መ ! ! ! ! ጭ ፡ ! ! ጭ ፡ ! !

ታሪኩ ፤

ቢጨነቁ ፡ ላይሆን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡
በምኞት ፡ ላይገኝ ፡ ሥር ፡ ቢግተረተር ፡
ቀኑ ፡ ካልደረሰ ፡ ካልበሰለ ፡ በቀር ።

ካላበጠ ፡ አይበስልም !
ካልበሰለ ፡ አይፈርጥም !
ሰዉ ፡ ቢጨነቅም ፤
ጨጓራው ፡ ቢላጥም ።

ወዲህ ፡ ቢሉት ፡ ያው ፡ ነው ፡ ወዲያ ፡ ቢሉ
ትም ፡ ያው !
የምኞት ፡ እንጀራ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ጣጣው ።

በሀሳብ ፡ ያርስና ፡ ደግሞም ፡ ይዘራና ፤
መሬቱ ፡ ለስልሶ ፡ ጥሩ ፡ ያበቅልና ፤
አርሞ ፡ ኮትኩቶ ፡ አጭዶ ፡ ይወቃና ፤
ፍሬውን ፡ አይቀምስም ፡ ያልበው ፡ የነበር ፡
በሀሳብ ፡ ነውና ።

ፍሬ ፡ ሲያጣበት ፡ መልሶ ፡ ይጠምዳል ፡
በምኞት ፡ ለማረስ ፤
ለመዝራት ፡ ለማብቀል ፤ ለማጨድ ፡ ለመው
ቃት ፡ ለማምረት ፡ ለማፈስ ፤
ሠርተው ፡ ከሚያገኙት ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ።

ዳሩ ፡ ግን ፡ አይሆንም ፡ ያው ፡ አሳብ ፡ ነውና ፡
በዕውነት ፡ ካላረሱ ፡ አይገኝምና ።

ጉበዝ ፡ ተው ፡ በሉልኝ ፡ ይኸ ፡ ሰው ፡ አይባክን ፡
በአሳብ ፡ አይጨነቅ ፡ ይለምን ፡ አምላክን ።



ኤፍሬም ፤

ችግሬ ፡ ይኸው ፡ ነው !
መፍትሄ ፡ የሌለው !
በራሴ ፡ መመራት ፡ ከቶውም ፡ አላውቀው ።

አንዱ ፡ ግራ ፡ ሲለኝ ፡ አንደኛው ፡ ወደቀኝ !
በዚህ ፡ በዚያ ፡ እያለ ፡ ሁሉም ፡ ሲጎትተኝ ፤

የምለውን ፡ አጣሁ ፡ ሁሉን ፡ እየሰማሁ ፡
መምረጥ ፡ ስላቃተኝ ፡ በመሀል ፡ ተጐዳሁ ፡
ማንንም ፡ አልወቅስም ፡ ስንፍናው ፡ የራሴ ፡
መሆኑን ፡ ተረዳሁ ።

አሳብ ፤

ዕውነትም ፡ ከብት ፡ ነህ ፡ የትም ፡ ትነዳለህ !
በተወራ ፡ ቁጥር ፡ ትለዋወጣለህ ።

መልክህ ፡ እንደሰው ፡ ነው ፡ ጠባይህ ፡ ግን ፡
እሰስት ፤
ሊገባህ ፡ አይችልም ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ማተት !
ሜዳ ፡ ተሰማራ ፡ ሣር ፡ ብላ ፡ እንደከብት ።
ምነው ፡ ብታስተውል ፡ የከብቶችን ፡ ፍጥረት ፡

ትልቁም ፡ ትንሹ !
ምንም ፡ ሳያስቡ ፡ ምግብን ፡ ብቻ ፡ ሲሹ ።
የአሳማው ፡ መደሰት ፡ ለምን ፡ ይመስልሃል ?
አወፋፈሩሳ !

እየለቃቀመ ፡ ይኖራል ፡ ሳይከሳ ፡
ብዙ ፡ ሳያደክም ፡ ገንዘብ ፡ መሆኑሳ !

ኤፍሬም ፤

እኮ! ሰውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ካላሰበ ፡ አይከሣ!

አሳብ ፤

ካልሠራ ፡ በስተቀር ፡ ለቅሞ ፡ የማይበላ ፡ መሆ
ኑን ፡ አትርሳ !

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ መ ! ! ! ጭ ፡ ! ! ! !
እ ! ! ! ል ! ! ! ም ! !
ለካስ ፡ ሞትም ፡ አለ ?

አሳብ ፤

ባንድ ፡ በኩል ፡ ውሻ ፡ ጌታውን ፡ የሚወድ ፤
ቢበድለው ፡ አያውቅ ፡ ሂድ ፡ ቢለው ፡ የማይ
ሄድ ፤
በራሱ ፡ አስቦ ፡ መኖር ፡ ስለማይችል ፣
እየለቃቀመ ፡ የትም ፡ ሲዞር ፡ ቢውል !
ማታ ፡ ተመልሶ ፡ ዘበኝነት ፡ ያድራል ።

ልብ ፡ ብለህ ፡ እየው ፡ እስኪ ፡ ተመልከተው ፣
ቢበላ ፡ ባይበላ ፡ ለጌታው ፡ ታማኝ ፡ ነው ፤
ይህኮ ፡ የሆነው ፡ ስለ ፡ ማያስብ ፡ ነው ።
እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ፈረሱ ፡ አህያው ፡ ግመ
ልና ፡ በቅሎ ፡ ሁሉም ፡ ግዙፍ ፡ ሆነው !
የቅንድ ፡ ከብቶቹ ፡ ታርደው ፡ ለመበላት ፡
ሲመከርባቸው !
አህያው ፡ ግመሉ ፡ ተጭነው ፡ ለመሄድ ፡
ሲመጡ ፡ ተስበው !



ጉልበት ፡ ሳይንሳቸው ፡ ባያስቡኮ ፡ ነው !
ግዙፍዋን ፡ ላም ፡ እያት ፡ ጥጃዋን ፡ እያየች ፡
ባጠባኋት ፡ ስትል ፡
ታልባ ፡ ታጠጣለች ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ ሳትል።

ግሩም ፡ ነው !

ሰነፍም ፡ ወግ ፡ አለው ፡ በታሪክ ፡ ይነሣል ፡
ጎበዝም ፡ ወግ ፡ አለው ፡ በታሪክ ፡ ይወሣል ፡
ሞኝ ፡ ሲበረክት ፡ አዋቂው ፡ ይረሣል ።

ሰማህ ፡ ሞኞ !

ቂል ፡ ሆነህ ፡ እንድትቀር ፡ ይሰባብኩሀል !
ጭፍራችን ፡ እያሉ ፡ አታስብ ፡ ይሉሀል !
ምነው ፡ ይግባህ ፡ እንጂ ! ዓምላክ ፡ የሰጠህን ፡
እንዴት ፡ ይነሱሃል ?

መድሃኒት ፡ የለውም ፡ እንዳንተ ፡ ላለ ፡ ሰው ፤
የሰውን ፡ ቅርጽ ፡ ይዞ ፡ ከከብት ፡ ያልተለየው፡
ቢነግሩት ፡ ቢመክሩት ፡ አይሰማም ፡ ያው ፡
ያው ፡ ነው ፤
ምን ፡ ይደረግ ፡ ብሎ ፡ ጣል ፡ እርጎ ፡ መተው ፡
ነው ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፡

መ ! ! ጭ ! ! !
ጭ ! ! ! ል ! ! ! ! ጥ ! !
አይ ፡ ጉድ ! ለካስ ፡ መሞትም ፡ አለ ?

ኤፍሬም ፤

አሁንስ ፡ ጨነቀኝ ፡ ታዲያ ፡ የቱን ፡ ልምረጥ ?
ኧረ ፡ እስኪ ፡ ንገሩኝ !

ወይም ፡ ገለል ፡ ልበል ፡ አትሰልቹኝ ፡ ገላግሉኝ ፤
ከአቅሜ ፡ በላይ ፡ ነው ፡ ታገለው ፡ አትበሉኝ ።
ካንተ ፡ አላንስም ፡ ይላል ፡ ወደሉ ፡ አህያ ፡
እንዴት ፡ ነው ፡ ነገሩ ?
ሣር ፡ በልቶ ፡ መደሰት ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ሚስ
ጢሩ ?
ሌላውም ፡ ብጠይቅ ፡ ቀውላላው ፡ ፈረሱ ፡
እንዲሁም ፡ ባዝራ !
እየዳኸች ፡ መጥታ ፡ ካንተ ፡ አላንስም ! አለች ፡
እግዜርን ፡ አትፈራ ።
እምቧ ፡ ባዮች ፡ ደግሞ ፡ እንበሬው ፡ ሁሉ ፤
ምንም ፡ አይከፉም ፡ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ ያምራሉ ፡
ሰው ፡ አስቦላቸው ፡ በልተው ፡ ይኖራሉ ።
የኔ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እየከፋ ፡ ሄዶአል ፤
ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ በክንክን ፡ ብሎአል ።
አንጎሌ ፡ ዞሮአል !
ሽማግሌን ፡ ጠርቶ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፡ መላ
ቀቅ ፡ ይሻላል ።
እነ ፡ አቶ ፡ ታሪኩን ፡ ሄጄ ፡ ላማክራቸው ፡
ይገላገሉኛል ፡ አዋቂዎች ፡ ናቸው ።
ሽማግሌ ፡ ይስማው ፡ ወሬውም ፡ ይዞራ !
በደሌ ፡ ይገለጽ ፡ ይታወቅ ፡ ይጣራ !
በሰው ፡ ዘንድ ፡ ይወራ ፡ ችግሬን ፡ ሰው ፡ ይየው
ከተሸፋፈነ ፡ ኑሮ ፡ ምን ፡ መላ ፡ አለው ?



## ምዕራፍ ፡ ፬ ፡

### ሁለተኛ ፡ ትይንት ።

እንደልቡ ፤

ለምን ፡ ጠራችሁን ፡ ኧረ ፡ እስኪ ፡ ንገሩን !
ምን ፡ አገናኛችሁ ? በሉ ፡ ግለጹልን !

ኤፍሬም ፤

ጌታዬ ! ሳላውቀው ፤ ሳያውቀኝ ፡ ልጠጋህ ፡
ይለኛል !
ጤና ፡ ይነሳኛል !
በነፍስ ፡ በሥጋዬ ፡ ይቀልድብኛል ፤
ጭፍሮቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ይዶልትብኛል !
በህልሜም ፡ በውኔ ፡ ምኞት ፡ ያሰክረኛል ።
በውኔ ፡ የማየው ፡ ባህሪውን ፡ ሳይለቅ !
ዓይኖቼ ፡ እያዩ ፡ ይሰውረኝና ፡ ሰውነቴን ፡
ማድቀቅ ።
በህልም ፡ የምበላው ፡ ከቶም ፡ ላያፋፋኝ !
መጠጡ ፡ መብሉ ፡ ጋጋታው ፡ ገደለኝ ፤
ከእንቅልፌ ፡ ስነቃ ፡ አልለውጥም ፡ ያው ፡ ነኝ !
ሳልቀምስ ፡ እስከራለሁ ፡ አንጎሌ ፡ ይቃዣል ፡
ምን ፡ እንደማይ ፡ አላውቅ ፡ አፍጥቼ ፡ እያየሁ ፡
ታዲያ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ?

ምናልባት ፡ ዓይኖቼ ፡ ሰው ፡ እንዲያስፈኝ ፡
ለጌጥ ፡ ተፈጥረዋል !
ጆሮኤም ፡ ይሰማል ፤
ልቤ ፡ ተቀብሎ ፡ ከበሮን ፡ ይመታል !
ሰውነቴ ፡ ሁሉ ፡ ሲጨነቅ ፡ ይታያል ።

እግዜር ፡ ያሳያችሁ ፡ አንድ ፡ ምስኪን ፡ ደሀ ፡
ምናምን ፡ የሌለኝ ፡
አያገባው ፡ ገብቶ ፡ ለምን ፡ ይበጥብጠኝ ?

ወይ ፡ ሳይፈጥረኝ ፡ ብቀር ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡
ባላይ !
በማይገባኝ ፡ ሚስጢር ፡ እንዲህ ፡ ከምሰቃይ ።
አላስቸግራችሁ ፡ ነገሬን ፡ ላሳጥር ፡
ድሮም ፡ ለችግር ፡ ነው ፡ አምላክ ፡ እኔን ፡
መፍጠር ፤

ወይ ፡ ጉድ ! አይ ፡ ዘንድሮ !

ላቤ ፡ እንደወሀ ፡ የሚንቆረቆረው !
ፊቴ ፡ ደም ፡ የሚለብስ ፡ የሚቀያየረው !
ስሬ ፡ ተገታትሮ ፡ አጥንቴም ፡ ሚታየው !
ሊረዳኝ ፡ በማይችል ፡ ባሳብ ፡ ተይዤ ፡ ነው ።

እንደዚህ ፡ መጨነቅ ፡ እንዲህ ፡ መንገላታት ፡
ተሳሳቁሎ ፡ መኖር ፡ ኋላ ፡ ለመረታት ፡
ገላጋይ ፡ ሞት ፡ ሊሆን ፡ ይግባኝ ፡ የሌለበት ።

በዕውነቱ ፡

ጌትነት ፡ በምኞት ፡ የሚገኝ ፡ አይደለም ፡
ካልሠሩ ፡ በተቀር ፡ በልቶ ፡ ማደር ፡ የለም ።



አየሁ !

ራዲዮው ፡ ጋዜጣው ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ነው ፡
አስተሳሰባችሁ ፡ መስመሩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፤

ሳይሠሩ ፡ ጌትነት ፡
ሳይበሉ ፡ ደም ፡ ግባት ፡
እንዲገኝ ፡ መመኘት ፤

ሊያቃዥ ፡ ይችላል !
እንዳልከው ፡ ይሆናል ፤
ሥራ ፡ ፊት ፡ መሆን ፡ ለወሬ ፡ ያዝናናል ።

መሣይ ፤

የኛ ፡ ትችት ፡ ይቆይ ፡ የነሱ ፡ ይሰማ ፤
ፈርደን ፡ እንዳንገኝ ፡ ጉዳዩን ፡ ሳንሰማ ።

አቶ ፡ አሳብ ፡ መልስ ፡ ስጥ ፡ ለተነገረው ፡ ቃል ፤
በጣም ፡ አታስረዝም ፡ አጭር ፡ ቃል ፡ ይበቃል ፤
ዕውነት ፡ ከሆነማ ፡ ነገሩ ፡ ይደንቃል !
ሰው ፡ ከፋት ፡ ሳይኖረው ፡ ለምን ፡ እረፍት ፡
ያጣል ?
አንተስ ፡ የሱን ፡ ጥቃት ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል ?

አሳብ ፤

የዓምላክ ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ አሳብ ፡ የሚባለው ፤
ቀንም ፡ ይሁን ፡ ለሊት ፡ አብሮት ፡ የሚኖረው ፤
ሌላ ፡ መቼ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ የሚያስኘው ?
ሰው ፡ ማለት ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ካሳብ ፡ ከተለየ ?
አስቦ ፡ ካልሰራ ፡ ከእእምሮው ፡ ጋራ ፡ እየተወያየ ።

እንዳሳማ ፡ ለቅሞ ፡ በልቶ ፡ ከተኛማ !
መወለድ ፡ ብቻውን ፡ ሰው ፡ አያሰኝማ ።

ይነሱ ፤

እረ ፡ ጉደኛ ፡ ነህ ፡ በጣም ፡ ትገርማለህ !
ይህን ፡ ምስኪን ፡ ደሀ ፡ ባትጫወትበት ፡ እስኪ
ምን ፡ ቸገረህ ?
አሳብ ፡ የተባልከው ፡ አንተ ፡ የማን ፡ ሰው ፡
ነህ ?

አሳብ ፤

ከሁሉም ፡ ጋር ፡ አለሁ ፡ ብቻ ፡ በመጠኑ ፡
ቁጣው ፡ ሳይረዱት ፡ ጌታዬ ፡ ምን ፡ ሆኑ !
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ምነው ፡ ባይሰማ ?
የኋሊት ፡ መሄድ ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ ከሆነማ ።

መሣይ ፤

ከሁሉም ፡ ጋር ፡ አለሁ !
ምን ፡ ማለትህ ፡ ይሆን ፡ ነገሩ ፡ ያሰጋል ፤
ጊዜ ፡ ፈጥሮብን ፡ ነው ፡ መቼስ ፡ ምን ፡ ይሆ
ናል !
ለብቻው ፡ ተፈጥሮ ፡ የአዳም ፡ ልጅ ፡ በሙሉ ፡
አሁን ፡ ከአሳብ ፡ ጋር ፡ ድርብ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።
ብዙ ፡ መስማት ፡ አለ ፡ ጊዜ ፡ ለሰጠው ፡ ሰው፡
አታላይ ፡ ሞልቶአል ፡ አቅም ፡ ካላነሰው ።

በዕውነቱ ፤

ምንም ፡ ላትግባቡ ፡ ብቻ ፡ ከንቱ ፡ ልፋት ፡



ሰው ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ይገባዋል ፡ መስ
ማት ፡
ወሬ ፡ ቢደራረብ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ከሌለው ፤
ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ማዳመጥ ፡ ጊዜን ፡ ማባከን ፡ ነው ።
ምነው ፡ ብትተዉት ፡ ጊዜን ፡ ባናጠፋ ?
ጭቅጭቅ ፡ መች ፡ ሆነ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ተስፋ !
ግራ ፡ ቀኝ ፡ ብላችሁ ፡ ሁሉንም ፡ ብታዩት ፡
ዓምላክ ፡ ከፈጠረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረት ፤
ሰውኮ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ምነው ፡ አትረዱት ?

ዘመቻ ፡ ሙሉዓለም ፡

መ ! ! ! ጭ ! ! እ ! ! ል !
! ! ም ! ! ! ጭ ! ! ! ል ! ! ጥ
አቤት ፡ ተነሳሁኝ ፡
ባየር ፡ ላይ ፡ ለመብረር ፡ ቲኬት ፡ አገኘሁኝ ፡
መ ! ! ጭ ! ! ጭ ! ! ል ! ! ጥ ! !

ይነሱ ፤

ጊዜው ፡ ተለወጠ ፤ እየከፋ ፡ ሄደ ፡ ጉዳዩ ፡
ያሰጋል ፤
ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ ነው ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡
አብድዋል ፤
ሰለጠንኩ ፡ እያለ ፡ ፈጣሪውን ፡ ክዶአል ።
እርፎ ፡ እንደ ፡ መብላት ፡ ተመስገን ፡ እያለ ፤
ሰይጣን ፡ አደረበት ፡ ሁሉም ፡ ተታለለ ፤
ይህ ፡ ስምንተኛው ፡ ሺህ ፡ ክፋቱ ፡ አየለ ።

ወጥንቅጡ ፡ በዝቶ ፡ ግራ ፡ ገባንኮ ፡
ቀስ ፡ በቀስ ፡ ለወጠው ፡ የፊቱን ፡ አምልኮ ።

ኤፍሬም ፤

ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይኸው ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ እወ
ቁት ፡
ብልሃት ፡ ቢገኝልኝ ፡ እንዳልንከራተት ፡
ያለ ፡ ፍላጐቴ ፡ እንዳልወተወት ፡ ይተወኝ ፡
ለምኑት ።

አሳብ ፤

አንተን ፡ የራዳሁኝ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ ምንም ፡ የለኝ ፤
ተኅልተህ ፡ ዶልት ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ቸገረኝ !

የማይገባው ፡ ድንጋይ ፡ ቢመክሩት ፡ ቢነግሩት ፤
ወደኋላ ፡ የሚል ፡ ወደፊት ፡ ሂድ ፡ ሲሉት ፤
እንዳንተ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ የመሻሻል ፡ ጠላት ።

ካሳብ ፡ ልለይ ፡ የሚል ፡ ገራገር ፡ ደንቆሮ ፡
ይህ ፡ ቢሉት ፡ ያ ፡ ሲሉት ፡ ማይገባው ፡ ተመ
ክሮ ፤ ባገር ፡ ውስጥ ፡ ተፈጥሮ !
የት ፡ ሊገኝ ፡ ይቻላል ፡ የመሻሻል ፡ ኑሮ ?

ያም ፡ መጥቶ ፡ ሲነግረው ፡ ጎሽ ፡ እሰይ ፡ እያለ
ያንንም ፡ ሲሰማ ፡ ጐሽ ፡ እሰይ ፡ እያለ !
በራሱ ፡ የማይቆም ፡ ሲዋልል ፡ የሚኖር ፡ በቁ
ጥር ፡ አየለ ።
በጣም ፡ የሚገርመው ፡ የሚያሳስበው ፤



አእምሮን ፡ የሚያዞር ፡ የሚያሳዝነው ፤
ብልሁ ፡ አዋቂው ፡ ስልጡኑ ፡ መርማሪው ፤
በልቶ ፡ ተደሳቹ ፡ ሰነፍ ፡ ጦም ፡ አዳሪው !
ዘራፊው ፡ ቀጣፊው ፡ ዓይን ፡ ባይን ፡ ነጣቂው !
ከንቱ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በምኞት ፡ አዳሪው ፤

ሳይለይ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል !
የወል ፡ ስም ፡ ነውና ፡ ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ።

እንደዚሁም ፡ አንተ ፡ ከብጤዎችህ ፡ ጋር ፡
ምንም ፡ የማይገባህ ፡ ጨርሶ ፡ ገራገር ፤

ባስረዳህ ! ብመክርህ ! አልተቀበልከኝም ፡
ስለማትረባ ፤
እንግዲህ ፡ ስለቸኝ ፡ ይኸው ፡ ገደል ፡ ግባ !

ታሪኩ ፤

ምነው ፡ አቶ ፡ አሳብ ፡ ነገርህ ፡ ከረረ ፡ አስተያ
የት ፡ አጣ !

አሳብ ፤

ምን ! ይኸው ፡ ውሎ ፡ አድሮ ፡ ከበድ ፡ ያለው ፡
መጣ !

ይነሱ ፤

ምን ፡ ዓይነት ፡ ድፍረት ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ?
ስድብ ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ቁጣ !
መጥፎ ፡ ዛር ፡ ይመስል ፡ አልላቀቅ ፡ ብለህ ፡
ራስህ ፡ ተሳስተህ ፡ ሰውን ፡ ትጐዳለህ ፤ ገደል ፡
ታገባለህ ፤

አስበህ ፡ አስተውለህ ፡ አውጥተህ ፡ አውር
ደህ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ አገኘህ ?
ሰነፉ ፡ አታስብ ፡ ተኛልኝ ፡ የሚለው ፡
አንተም ፡ በበኩልህ ፡ የምታቃጥለው ፤
በከንቱ ፡ አይደለም ፡ ላንድ ፡ ነገርህ ፡ ነው ፤
ይኽ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይሁን ? የዚህም ፡ ዓለም ፡
ነገር ፡ ፈላጊው ፡ ብዙ ፡ ነው ።

አሁን ፡ ተመልከተው ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ አል
ፎታል ፤

በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ካሳብ ፡ ጋር ፡ ኖሮአል ፤
ለብሰዋል ፡ አጊጦአል ፡ ወፍሮም ፡ ታይቶአል ፤
ብንን ፡ ሲል ፡ ያው ፡ ነው ፡ መቼ ፡ ለውጦአል !

አሁን ፡ ልገላገል ፡ ብሎ ፡ ሲለምንህ ፤
ስንቱን ፡ ያልሆነውን ፡ ትደረደራለህ ?
ለጥቅም ፡ ከሆነ ፡ ለሱም ፡ አስብለት ፡
እንዳሻው ፡ ይጉለት ፤
አይብላ ፡ ይመንምን ፡ አይልበስ ፡ ይራቆት !
ጨርሶ ፡ አይሥራ ፡ ወሬውን ፡ ይዶልት ፤
ለመኖር ፡ ከቻለ ፡ በራሱ ፡ ፍላጐት ።

በዕውነቱ ፤

አዬ ! አለማወቅ ፡ አለመመራመር ፤
አይ ፡ጉድ ! አለመብሰል ፡ ሞኝ ፡ መሆን ፡
ገራገር ፤
ወሬ ፡ ከተባለ ፡ ሁሉም ፡ ይደመጣል !
ሰነፍ ፡ አርም ፡ ሲሉት ፡ ሲመክሩት ፡ ይቆጣል ፤



አዋቂ ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ ቢክቡት ፡ ይመርጣል ፤
የሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ ይገርማል ፡ ይደንቃል ።

የዱር ፡ አራዊት !
ላላምድህ ፡ ቢሉት !
እየለቃቀሙ ፡ ቢያባብሉት !
ያሳዩትን ፡ ይሠራል ፤
ፊትን ፡ አይቶ ፡ ይመራል ፤

ሰማችሁ !

ደግ ፡ ሳይታወቅ ፡ ዘላለም ፡ ይኖራል ፤
በሳቅ ፡ በጨዋታ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ይቀራል ።
የሰነፍም ፡ ወሬ ፡ ጊዜን ፡ ያባክናል ፤
የናንተ ፡ ክርክር ፡ ለሰሚ ፡ ይደንቃል ፡ እጅግ፡
ያሳዝናል ።
ሕጻንን ፡ መደለል ፡ በቀላሉ ፡ ሲቻል ፤
በስኳር ፡ በዳቦ ፡ ወይም ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፤

ቁጣን ፡ ለማይወደው !
በዕድሜ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡
በስኳር ፡ በዳቦ ፡ የማይደለለው ?
አልመች ፡ የሚለው ፡ የአዋቂ ፡ ሕጻን ፡ ነው።
እንግዲህ ፡ ይኽ ፡ ሰው ፡ ብልሃቱ ፡ ምንድር ፡ ነው?

ሰማችሁ !

በድን ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ ይጠቅም ፡ መሰሎአችሁ ፤
ያለ ፡ አሳብ ፡ መኖር ፡ እንዴት ፡ መረጣችሁ ?
ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ወሰን ፡ ሲበጅለት ፤
ምድር ፡ ላይ ፡ ሲስፋፋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍጥረት ፤

የማሰብ ፡ ችሎታ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ተሰጠ ፣
ውለታው ፡ ቀረና ፡ አላስብም ፡ የሚል ፡ ካሳ
ቢው ፡ በለጠ ።

ግን !

ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ እንዲመራመር ፡ ነው!
ተሻሽሎ ፡ መገኘት ፡ የመኖር ፡ ትርጉም ፡ ነው ፣
ሳይሻሻል ፡ ቢቀር ፡ እዳው ፡ የራሱ ፡ ነው ።
መጠየቅ ፡ ያሻዋል ፡ አውቆ ፡ የማይሠራ ፣
የሚዳ ፡ ኅርፍ ፡ መስሎ ፡ የትም ፡ ከሚመራ ።

እንደልቡ ፣

ካሳብ ፡ ካልተደረብን ፡ መኖር ፡ አንችልም ፡
ብለህ ፡ ስታወራ !
ካፈር ፡ የሠራህን ፡ ዓምላክን ፡ አትፍራ !

እግዚአብሔር ፡ መሆኑን ፡ የሚያስብልህ ፣
ስሉሱ ፡ ርቆህ ፡ ሳትረዳው ፡ ቀርተህ ፣
ይህ ፡ ቢሆን ፡ ያ ! እያልክ ፡ ታሳስተናለህ ።

ሰይጣን ፡ አንተን ፡ መስሎ ፡ ሄዋንን ፡ ሲያስት!
ይህንን ፡ ከበላሽ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትልቅ
ትሆኛለሽ ፡ ብሏት ፣
አትንኪ ፡ ያላትን ፡ ሄዳ ፡ በላችና ፡
እንደምታዩት ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ፈተና ።
ምን ፡ አለ ፡ ጊዜው ፡ ነው ፡ ጨርሰህ ፡ አጥፋና !

በዕውነቱ ፣

ሄዋንን ፡ ያሳተ ፡ አለማሰብዋ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡
መቼ ፡ ሆነ !



እርግጥ ፡ በውጤቱ ፡ ሰዉ ፡ ተኰነነ ።
ባለማሰብዋ ፡ ነው ፡ ብትሆን ፡ ገራገር ፣
አስባ ፡ ብትሠራ ፡ አትሞኝም ፡ ነበር ።

የዚሁ ፡ ብጤ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ያደከመን ፡
ተመልሰን ፡ ያው ፡ ነን ፡ እንደሄዋን ፡ ዘመን ።

ዘመቻ ፡ሙሉ ፡ ዓለም ፡

! ! ! ! ጭልጥ ! ! ! እ ! ! ል ፡ ም ፡
ይኸው ፡ ተነሳሁኝ !
የምታየው ፡ ነገር ፡ በህይወትህ ፡ ሙሉ ፡
አዝእርቱ ፡ አትክልቱ ፡ ሣርና ፡ ቅጠሉ ።

ሁሉም ፡ በየመልኩ ፡ እንደየጠባዩ ፣
ባህር ፡ ውቅያኖሱ ፡ መሬቱ ፡ ድንጋዩ ፣

የቤት ፡ እንስሳቱ ፡ የዱር ፡ አራዊቱ ፣
ትላትሉ ፡ ሁሉ ፡ በራሪ ፡ አዕዋፍቱ ፣
ዝንቡ ፡ ሸረሪቱ ፡ ሁሉም ፡ በያይነቱ ፡

ቁንጫው ፡ ትኋኑ ፡ መዥገሩ ፡ ቅማሉ ፣
ትንኙ ፡ ቅጫሙ ፡ ተባዮች ፡ በሙሉ ፣
ሌላም ፡ እንደዚሁ ፡ የማናውቀው ፡ ሁሉ ፣
በድምር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ምድርን ፡ ያጌጣሉ !
ጥቂት ፡ ይኖሩና ፡ ጠፍተው ፡ ይቀራሉ ።

ለዚህ ፡ አጭር ፡ ኑሮ ፡ መጭ ፡ ይላል ፡ አሳቤ !
ሞት ፡ እንደሆን ፡ አይቀር ፡ ተሞልቶአል ፡
መዝገቤ ።

ታሪኩ ፤

በል ፡ ወንድሜ ፡ ተወን ፡ በጣም ፡ አደከምከን ፤
እንዳሻህ ፡ አድርገው ፡ መቼስ ፡ ካልሰማኸን ፤
እንለየዋለን ፡ አምላክ ፡ ይርዳህ ፡ ብለን ።

ኤፍሬም ፤

ምነው ፡ ግራ ፡ ገባኝ ፡ ምነው ፡ ተበጠበጥኩ !
የምመርጠው ፡ አጣሁ ፡ በከንቱ ፡ ተቸገርኩ ።
አሳቤ ፡ መጭ ፡ ይላል ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያለ ፡
አትርፎ ፡ ላይመጣ ፤
ትርጉሙን ፡ አጣሁት ፡ ወይኔ ፡ የኔ ፡ ጣጣ ።
አሁንስ ፡ ይበቃል ፡ አንተ ፡ አሳብ ፡ ተለመን ፤
አመንምኖኝ ፡ ቀረ ፡ የኑሮ ፡ ሰቀቀን ።
መባከን ፡ በዛብኝ ፡ ከንቱ ፡ መዘላበድ ፡
የሚገላግለኝ ፡ ምነው ፡ አጣሁ ፡ ዘመድ ?

አሳብ ፤

አስቦ ፡ ለመኖር ፡ አስቦ ፡ ለመሥራት ፤
አግኝቶ ፡ ለመኩራት ፡ በልቶ ፡ ለመደሰት ፤
አልፈልግም ፡ ልራቅ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ !
ሥርቼ ፡ አልበላም ፡ የመደሰት ፡ ኑሮ ፡ ካፍን
ጫፍ ፡ ይውጣ ፤
ባዮች ፡ በርክተዋል ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ ነገሩ !
ሊገባኝ ፡ አልቻለም ፡ ሃያል ፡ ነው ፡ ሚስጢሩ ።

አየህ ፤

የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አይደል ፡
በመመኘት ፡ ብቻ ፡ ኑሮ ፡ አይደለል ፤



አስብ ፤ እወቅ ፡ ሲሉት ፡ እምብዮ ፡ አላውቅም !
ወይም ፡ ጠይቅ ፡ ሲሉት ፡ የለም ፡ አልጠይቅም ፤
ክፍሉ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ልዩነት ፡ የለውም ።

ወይ ፡ ጉድ !

ጥሬው ፡ ብዙ ፡ ነበር ፡ ቁም ፡ ነገሩ ፡ አነሰ ፡
እንክርዳዱ ፡ ሁሉ ፡ እየተቀነሰ ።

ምን ፡ ያደርጋል !
መጮህ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ አንዴ ፡ ተይዞአል !
እንግዲህ ፡ ላይገባው ፡ መድከም ፡ ምን ፡ ያደር
ጋል ።

አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሄጄ ፡ ልለምነው ፤
ካልሆነም ፡ ይቀራል ፡ ዘፋኞች ፡ እንዳሉት ፡ ነገሩ
ያው ! ያው ፡ ነው ።

ኤፍሬም ፡

ምን ፡ አለ ፡ ልሞክር ፡ ካልሆነም ፡ ይቀራል !
ሰውን ፡ ለማስደሰት ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ይመራል ፤
የራሱን ፡ ይተዋል ።

መሣይ ፤

ሰማህ ፡ አቶ ፡ በዕውነቱ !

እየከፋ ፡ ሄደ ፡ ኤፍሬም ፡ ተቸገረ ፤
በሃሳብ ፡ ምክንያት ፡ በጣም ፡ ተማረረ ።
ምንም ፡ ሳያርፍ ፡ ያድራል ፡ በመገለባበጥ ፤
ሲባንን ፡ ይታያል ፡ በጣም ፡ ሲቅበጠበጥ ።

ምነው ፡ ተው ፡ ብትለው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔ
ሔር ፡ ብለህ !
አሁን ፡ ይኸ ፡ ደህ ፡ ምን ፡ ይሁን ፡ ትላለህ ?

በዕውነቱ ፤

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ያስቸገረው ፣
ለፍጥረት ፡ መሻሻል ፡ እንቅፋት ፡ የሆነው ፣
ለሰው ፡ የማያስብ ፤ ራሱን ፡ የሚወድ ፡ በር
ከት ፡ ስላለ ፡ ነው ።
ለማን ፡ ብለህ ፡ ይሆን ፡ ታጥቀህ ፡ የማጣኸው ?
አዎ ! ግራ ፡ ቀኝ ፡ በማለት ፡ ጥቅምን ፡ ፍለጋ ፡
ነው ።

ሰማህ ! ለጥቅሙ ፡ ካልሆነ ፡ ለሰው ፡ ደግ ፡
የሠራ ፡ ወይም ፡ የተመኘ ፡
ዕውነተኛ ፡ ጻኛ ፡ መች ፡ በብዛት ፡ ተገኘ ?

እንዳንተ ፡ መሳዩ ፡ ራሱን ፡ የሚወድ ፣
እየፈጣጠረ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፤

ለድሎቱ ፡ ብቻ ፡ ዘወትር ፡ የሚጥር ፣
የሰውን ፡ እጅ ፡ አይቶ ፡ በልቶ ፡ የሚያድር ፤

እየበዛ ፡ ሄደ ፡ ቁጥሩ ፡ በረከተ ፣
ማሰብን ፡ በመጥላት ፡ ቁም ፡ ነገርን ፡ ሳተ ።

ሰማህ ፡ ኤሬፍም !

እወቅ ፡ አለህ ፡ እንጂ ፡ አሳብ ፡ መቼ ፡ ጎዳህ !
ተኝቼ ፡ በህልሜ ፡ መጣብኝ ፡ ትላለህ ፤



አሳብ ፡ ሲደግፍህ ፡ አትሳሳት ፡ ብሎ ፤
ሰነፉም ፡ ይመጣል ፡ ከንፈሩን ፡ አሹሎ ፤
የተቆረቆረ ፡ ያዘነልህ ፡ መስሎ ።

መቼም ፡ ተነግሮሃል ፡ ቢገባህ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፤
አንተን ፡ የመሰለ ፡ ሙሉ ፡ የሆነ ፡ ሰው !
ምን ፡ እንደሚበጀው ፡ ማወቅ ፡ ሲያቅተው !
በጤናው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አጠራጠሪ ፡ ነው ።

ለሥራ ፡ ፊት ፡ ሲሳይ ፡ ሆነህ ፡ እንዳትቀር ፡
አሁንም ፡ ብትነቃ ፡ መተኛትህ ፡ ቢቀር ።

ኤፍሬም ፤

አይ ፡ጉድ ! ይደንቃል !
በየተራ ፡ መጥተው ፡ አታስብ ፡ እያሉኝ ፤
ግጠው ፡ እንዲበሉኝ ፡ በዘዴ ፡ አሞኙኝ ።
ዓምላክ ፡ ነው ፡ አሳቢው ፡ ምንም ፡ አትጨነቅ!
ፈጥሮ ፡ አይተውህም ፡ ከአሳብ ፡ ተላቀቅ ፡
ብለው ፡ በመደለል ፡ ሲያጠቁኝ ፡ ኖሩ ፤
ከቶም ፡ ሳልረዳው ፡ ሳላውቀው ፡ ሚስጢሩ ።
አሁን ፡ ገለጽክልኝ ፡ እንዲያ ፡ ስትጨነቅ !
እንዲያ ፡ ስትጉላላ ፡
ለመጭው ፡ ኑሮዬ ፡ ተገኘለት ፡ መላ ።

እንግዲህ ፡ ተመስገን ፡ እኔነቴን ፡ አወቅሁ ፡
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ሰው ፡ መሆንን ፡ ጀመርሁ ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለም ፡

መ ! ! ! ! ! ጭ ! ! !

አሳቤ ፡ እ ! ! ል ! ! ም ! ! አለ ፤

ጉ ! ! ዞ ! ውን ! ቀጠለ ፤ እ ! ል ! ! ም ! !

በዕውነቱ ፤

ፍጥረት ፡ ካላሰበ ፡ ካላሰላሰለ ፤
ሰው ፡ መስሎ ፡ ካልታየ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ ካልዋለ ፤
በየምክንያቱ ፡ ከተጨናነቀ ፤
ሰው ፡ ከሚያሰኘው ፡ ከሃሳብ ፡ ከራቀ ፤

እንስሳን ፡ ይመስላል ፡ በመልኩ ፡ ቢለይም ፡
ሰው ፡ እየተባለ ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ ቢታይም ።
ተኝቶ ፡ በከንቱ ፡ ብስጭት ፡ አያሻም ፤
ካልሠሩ ፡ በስተቀር ፡ ኑሮ ፡ አይሟላም ።

አሳብ ፤

እንዲህ ፡ ነው ! ከተመለስክማ ፡ ልቦና ፡ ከሰጠህ ፤
የመኖር ፡ ትርጉሙን ፡ አሁን ፡ ትረዳለህ ።
ከጠዋት ፡ ጀምረህ !

ቀውለል ፡ ስትል ፡ ውለህ ፡ ማታ ፡ ትገባና ፡
ቢኖር ፡ ትበላና !
ድሪቶህን ፡ ለብሰህ ፡ ጋደም ፡ ትልና !

በቅማል ፡ በትኋን ፡ አጥንትህ ፡ ይጋጣል ፤
መርጠህ ፡ አትለብስም ፡ ሠርተህ ፡ ካላተረ
ፍክ ፡ ከወዴት ፡ ይመጣል ?
አሁን ፡ ግን ፡ ተመስገን ፡ ነገሩ ፡ ገብቶሃል ፡
ለሥራ ፡ ከታጠቅህ ፡ ዓምላክ ፡ ይረዳሃል ፤
የሰውን ፡ እጅ ፡ ሳታይ ፡ በልተህ ፡ ትኖራለህ ፡
ለብሰህ ፡ ታጌጣለህ ፡
ከቁንጫ ፡ ስቃይ ፡ ትገላገላለህ ።



ኤፍሬም ፤

በቃ ፡ ቆርጫለሁ ፡ ነገሩ ፡ ገብቶኛል ፡
የቀድሞ ፡ ጥፋቴ ፡ አንጀቴን ፡ በልቶኛል ።
ካሁን ፡ ወዲያ ፡ በቃኝ ፡ ከንቱ ፡ መበለጡ !
ጉድለቴ ፡ ኃያል ፡ ነው ፡ ገብቶኛ ፡ በቅጡ ።

ካልሠሩ ፡ ማግኘት !
ካልበሉ ፡ መጠርቃት !
ካልተቀበ ፡ መውዛት ፤
ምኞት ፡ ስለሆነ ፡ ፍሬው ፡ አይታይም ፤
ቀን ፡ እየተወራ ፡ በሕልም ፡ ቢታይም ።

ታሪኩ ፤

ኤፍሬምን ፡ ለወጠው ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ሰባኪ !
እየደረደረ ፡ የአስት ፡ ትርኪ ፡ ምርኪ ፤
መሃረነ ፡ ክርስቶስ ፡ ዓምላክ ፡ ተለመነን !
ከችግር ፡ አድነን ፡ በሰላም ፡ አኑረን ፤

ኤፍሬም ፤

እናንተን ፡ አምኜ ፡ ሁሉንም ፡ ጠረጠርኩ !
ለኔ ፡ የማይበጀኝ ፡ ጠላቴ ፡ ነው ፡ እያልኩ ፤
አሳብን ፡ በመሸሽ ፡ እስህተት ፡ ላይ ፡ ወደቅኩ ።

አሁን ፡ ግን ፡ አያሻም ፡ መበለጥ ፡ ይበቃል !
ከአሳብ ፡ ልለይ ፡ ማለት ፡ ከመስመር ፡ ያወጣል ።
ማሰብ ፡ የሚጎዳኝ ፡ መስሎኝ ፡ እኖር ፡ ነበር ፡
ነገር ፡ ግን ፡ አይደለም !
ካለማወቅ ፡ ሌላ ፡ የሰው ፡ ጠላት ፡ የለም ።

ሰዎች ፡ ይባላሉ ፡ ሰነፎች ፡ በሙሉ ፣
ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያሉ ፡ እያውደለደሉ ።
እኔንም ፡ ጐተቱኝ ፡
አታስብ ፡ እያሉኝ ፤
የሥራ ፡ ጊዜዬ ፡ በወሬ ፡ አሰጣሉኝ ።
ዕድሜዬ ፡ አዘገመ ፡ ምንም ፡ ሳልሠራበት ፤
አንጐሌ ፡ አይበቀል ፡ ጊዜ ፡ አለፈበት ፤
ዕድሜ ፡ አይመለስ ፡ እንደጐርፍ ፡ ይጠፋል !
ምንም ፡ ሳይታወቅ ፡ ሽርተት ፡ ብሎ ፡ ያልፋል።
ሊጨበጥ ፡ አይችልም ፡ በኋላ ፡ ቢሮጡ !
ያለንበት ፡ ዓለም ፡ ልጅነት ፡ ነው ፡ ጌጡ ።
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቢገባኝ ፡ ባሁኑ ፡ እድሜዬ ፤
ከመቆጨት ፡ በቀር ፡ ሊጠቅመኝ ፡ አይችልም ፡
  አለቀ ፡ ጊዜዬ ።
የሰውን ፡ እጅ ፡ አይቶ ፡ መኖር ፡ ብቻ ፡ ቀረኝ ፤
ከልመና ፡ ኑሮ ፡ አቤቱ ፡ ገላግለኝ ።

በዕውነቱ ፤

ምን ፡ ያደርጋልሃል ፡ ላለፈው ፡ ብታለቅስ ?
ከቶም ፡ ላታገኘው !
ለመጭው ፡ ማሰብ ፡ ነው ፡ ያለፈውን ፡ ተወው ።
ዓምላክ ፡ ነው ፡ አሳቢው ፡ የሚለውን ፡ ይዘህ !
በመዶለት ፡ ብቻ ፡ ያለፍሬ ፡ ቀረህ ።
ዕድሜህ ፡ ገፋ ፡ ብሎአል ፡ አሰት ፡ አይባልም ፤
ከእንግዲህ ፡ ሩጠህ ፡ ብዙ ፡ አታተርፍም ፤



ዕድሜ ፡ አይመለስ ፡ መድኃኒት ፡ የለውም ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢሆንም ፡ ባለህ ፡ ቀሪ ፡ ጊዜ ፡ ጀም
ረህ ፡ ካሁኑ !
ከሥራ ፡ በስተቀር ፡ አንጉልህ ፡ አይያዝ ፡ በም
  ንም ፡ በምኑ ፤

ሰማህ !

ጐርፍ ፡ የወሰደውን ፡ ጐርፍ ፡ አይመልሰውም ፡
ያሁኑ ፡ ቁጭትህ ፡ ጊዜ ፡ አልፎበታል ፡ ትር
ጉምም ፡ የለውም ።
ላገርህ ፡ ልፋለት ፡ እንዲሁም ፡ ለግልህ
ይኸው ፡ ነው ፡ ይበቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይር
  ዳህ ።

ዘመቻ ፡ ሙሉዓለም ፡

መ ! ! ! ! ጭ ! ! ! !
ጭ ! ! ! ! ል ! ! ጥ ! ! ! እልም ! ! !
(መጋረጃ) ፤


ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ አለም ፤ ኤፍሬም ፡ አሳብ ፡ ታሪኩና ፡ መሳይ ፡ አብረው ፡ ይቀመጣሉ ።

ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ አለም ፡

መ ! ! ጭ ! ! ! ! !
እ ! ! ! ል ! ! ም ! ! ተነሳሁኝ !
ገንዘብ ፡ ሳላወጣ ፡ ቲኬት ፡ አገኘሁኝ ፤
ይሄ ፡ ነው ፡ ! ! !

አሳብ ፡ ቀልቤ ፡ ነው ፡ ምን ፡ ምግብ ፡ ያሻኛል!
መ ! ! ጭ ! ጭ ! ል ! !ዊ ! ! ደከምኩ ፡ ይበ
በቃኛል ።
ሰላም ፡ አጥቻለሁ ፡ እንዲሁም ፡ ጸጥታ !
መንፈሴ ፡ ታወከ ፡ ሥጋዬም ፡ አለቀ ፡ አድም
ጡኝ ፡ በርጋታ ።
ብ ! ! ው ! ! ይኸው ፡ መጣ ! አቤት ፡ ስ
ዞር ! አቤት ፡ ስንቀዋለል !
እዩኝ ፡ ተመልከቱኝ ፡ ካሳብ ፡ ጋር ፡ ስታገል ።





መ ጣ ሁ ! መ ----ጣ----ሁ !

ብ ! ! ብ ! ! ው ! እልም ፡ አልፈልግም ፡ ልጥፋ!
ከንቱ ፡ ለምን ፡ ልልፋ ?

ሥጋዬ ፡ ተኝቶ ! አሳቤ ፡ እልም ፡ አለ ፡ በረር
ርኩኝ ፡ ባየር ፡ ላይ !

በቃኝ ፡ አልመኝም ፡ የምድሩን ፡ ሲሳይ ።

በቃኝ ! በቃኝ ! ሄድኩላችሁ !

መመለስ ፡ ቀርቶአል ፡ ምድሩ ፡ ይስፋላችሁ።

እ ! ል ! ም ! ያውላችሁ ፡ ብክንክን ፡ ብያለሁ፡

ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ እርሜን ፡ አውጥቻለሁ!

ባሕር ፡ ሳያስፈልግ ፡ ባየር ፡ ላይ ፡ መዋኘት !
ድንበር ፡ አለፍክ ፡ ተብሎ ፡ ጭቅጭቅ ፡ የለ
በት ።

በሮ ፡ መመለስ ፡ ነው ፡ መቼ ፡ በግር ፡ መሄድ !
ምንም ፡ ጊዜ ፡ አይወስድ ፡ ፍጥነቱ ፡ በሴኮንድ !

መቀመጥ ፡ በፎቴ ፡ በማይቆረቁረው !

እድሜ ፡ ለምኞቴ ፡ ሳልሠራ ፡ መብላ ፡ ነው ።

ጭልጥ ፡ ! ! ! በየስፍራው ፡ በቃ ፡ አልመለስም!
እዚያው ፡ ይሻለኛል ፤
መጉለት ፡ መቀመጥ ፡ በጣም ፡ ሰልችቶኛል ።



ፍዋ ! ! ፍዋ ! ! ባየር ፡ በረርኩ ፡ ተሰናበትኳ
ችሁ ፡ ዕድሜ ፡ ለምኞቴ !

ተመስገን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሞላ ፡ ፍላጐቴ ።

ጉድ ፡ ነው ! !

የዚህ ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ውዝግቡ ፡ ብዙ ፡
አሳብ ! ስቃይ ! ረሃብ ! ችግር ! አቤት ፡ አበዛዙ !

ጣጣው ፡ መበርከቱ ፡ እረ ፡ ለምንድር ፡ ነው ?
ነገ ፡ ሞት ፡ እያለ ፡ ዋዜማው ፡ ለምን ፡ ነው ?

አሳብ ፤

መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ አንተም ፡ ተይዘሃል ፡
አዋቂዎች ፡ አንሰው ፡ ቂላ ፡ ቂሉ ፡ በዝቶአል ።

ጓደኛህ ፡ ያውልህ ፡ አብራችሁ ፡ ታጎሩ ፤
ምንም ፡ ሳታስቡ ፡ ለመኖር ፡ ሞክሩ ።
በናንተ ፡ ዘንድ ፡ እኮ ፡ ማሰብ ፡ ነው ፡ ችግሩ !

ዘመቻ ፡ ሙሉዓለም ፡

እግዚአብሔር ፡ አለልን ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ተወን፡
ከኛ ፡ ጋር ፡ ተጣብቀህ ፡ ምንም ፡ አልጠቀምከን፤

እንዳፈጣጠሬ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ ስራመድ ፤
የምን ፡ ልዩ ፡ ልማድ ? የምን ፡ ልዩ ፡ መንገድ ?

ምድር ፡ እሳት ፡ ቢነድ ፡ ሰማይን ፡ አይፈጅም ፡
ሌላው ፡ የሰራውን ፡ መከጀል ፡ አይበጅም !

አሳብ ፤

ጊዜ ፡ የወለዳቸው ፡ ጥርቅምቅሞች ፡ ሁሉ ፤
ምነው ፡ ያለ ፡ ገመድ ፡ የትም ፡ ይሳባሉ ?

ዘመቻ ፣ ሙሉዓለም

ኧረ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ አሳቤን ፡ ልግለጸው ?
አምላክ ፡ የፈጠረን ፡ ሊረዳንኮ ፡ ነው ፤
የእለት ፡ እንጀራችን ፡ ስጠን ፡ የምንለው !
ኪርያ ፡ ላይሰን ፡ እያልን ፡ ጠዋትና ፡ ማታ ፡
የምንጸልየው !
እንጀራን ፡ ካልሰጠን ፡ ታዲያ ፡ ለምኑ ፡ ነው ?

አሳብ ፤

አይ ፡ ጉድ ፡ ትገርማለህ ፡ የማይገባህ ፡ ድፍን !
እንዳንተ ፡ ያሉትን ፡ አግበስብሶ ፡ ማፈን ፤
ፍጥረት ፡ ቢበረክት ፡ ቁጥሩ ፡ ቢንዛዛ ፤
ቁም ፡ ነገር ፡ ሳይሠራ ፡ ከተንሸራተተ ፡ እንደ
ጠዋት ፡ ጤዛ ፤

የሀገር ፡ ሸክም ፡ ነው !
ኑሮው ፡ መላ ፡ የለው !
በመወለዱ ፡ ግን ፡ ቁጥሩ ፡
ከሰው ፡ ጋር ፡ ነው ።
እሱም ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ መላሱን ፡ አሹሎ ፡
በወዲህ ፡ በማፍሰስ ፡ በዚያ ፡ ተቀብሎ ።

አምላክ ! አምላክ ፡ ብለህ ፡ ጸሎት ፡ ብታደርግም
ኪርያ ፡ ላይሰን ፡ ብትል !
ስትጮህ ፡ ብትውል !
ካልሠራህ ፡ በተቀር ፡ ምንም ፡ አይረዳህም ።
እኔን ፡ ይብላኝ ፡ ይላል ፡ አልቃሽ ፡ ሳይቸግረው ፤



ጭራሽ ፡ ላላወቀው ፡ ዘመዱ ፡ ላልሆነው ፤
ከሥራ ፡ ለመራቅ ፡ ያቀደው ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

ዘ. ሙ. ዓ.

በፍካሬ ፡ ኢየሱስ ፡ የተወራው ፡ ሁሉ ፤
ሲከበር ፡ የኖረው ፡ አድባሩ ፡ ባህሉ ፤
ስለጠንን ፡ ባዮች ፡ ሊሽሩት ፡ ነው ፡ አሉ ፤
ገደል ፡ ሊሰዱን ፡ ነው ፡ ሰዎች ፡ ቸል ፡ አትበሉ !
«እመኑት ፡ ለምኑት ፡ አቤት ! አቤት ! በሉት ፤
ኑሩ ፡ በተጋድሎ ፡ በጾምና ፡ ጸሎት !
እንዲሰውራችሁ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ክፋት »፤
ብሎ ፡ ሲያስጠና ፡ ሲያስተምር ፡ ኑሮ !
እንደዚያው ፡ እያለ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ፤
ምነው ፡ ተንጠራራ ፡ ድፍረትን ፡ አበዛ ?
የእግዚአብሔር ፡ ሚስጢር ፡ ላይገኝ ፡ በዋዛ !
ዓምላክ ፡ የሚሳነው ፡ የማይችል ፡ ይመስል !
በተንኮል ፡ ተመርቶ ፡ ደካማን ፡ ማስመሰል ፤
ይልቅስ ፡ ዓምላክን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ በለው ፤
ከመስመር ፡ አትውጣ ፡ መደለሉን ፡ ተወው ።

አሳብ ፤

አንተን ፡ ትቼሃለሁ ፡ አልበሰልክምና ፡
ማሰብ ፡ መመራመር ፡ መስሎሃል ፡ ፈተና ።

ኤፍሬም ፤

አስብ ! አላስብም ! በሚለው ፡ ክርክር ፡ እስካ
ሁን ፡ ቆይቼ ።

ምንም ፡ ሳላፈራ ፡ አእምሮዬ ፡ ዞረ ፡ በቁመና፡
ሞቼ ፤
ከንፈሬን ፡ ብነክሰው ፡ አሁን ፡ ምን ፡ ያደርጋል !
የሌሎቹ ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ ሰዓት ፡ አልቆአል ።
እንዲያው ፡ በድን ፡ ሆኜ ፡ ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡
መለስ ፡ ብዬ ፡ ሳየው ፤
እንዲሁ ፡ በእንደዲሁ ፡ በከንቱ ፡ ላለፈው ፡
በቁሜ ፡ ሞቻለሁ ፡ እየዬ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
አሁን ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፡ ምርር ፡ ብዬ ፡
ማልቀስ ?
ላሳለፍኩት ፡ ጊዜ ፡ ከንቱ ፡ ስልፈሰፈስ !
አዎ ! ኧረ ፡ አዎ !
ዋይ ! ዋይ ! ብሎ ፡ ማልቀስ ፡ እኔን ፡ ለመሰለው !
አንጀቱ ፡ ላረረ ፡ በቁሙ ፡ ላለው ፡ ነው ።

ዘ. ሙ. ዓ ፡

አይ ፡ጉድ ! ለካስ ፡ ሞትም ፡ አለ !
እንዴ ! እንዴ !
ሰው ፡ ለምን ፡ ይሞታል ? የምን ፡ ጨዋታ ፡ ነው ?
ሳይፈልግ ፡ ተፈጥሮ ፡ ኋላ ፡ ዓለም ፡ ሲጥመው ?
በመሃል ፡ መጥፋቱ ፡ ትርጉሙ ፡ ምንድነው ?

እንዴ !

ወጥመዱን ፡ ያበጀው ፡ አምላክ ፡ ለምን ፡ ይሆን ?
አይመረመርም ፡ ሥልጣኑ ፡ እንደሆን !
ይግባኝ ፡ እንዳልሞት ! !



መፈጠሬ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ በሞት ፡ ካልተቀጣሁ !
ሳልወድ ፡ በመገደድ ፡ ካለም ፡ ገጽ ፡ ካልጠፋሁ ።
ሁሉም ፡ በየተራው ፡ በየምክንያቱ ፤
በድንገት ፡ ይጠራል ፡ ያለ ፡ ፍላጎቱ ።
ባለም ፡ ጣዕም ፡ ስደሰት ፡ ድንገት ፡ ይመጣና ፡
ሲቀጨኝ ፡ ይታያል ፡ ሥልጣኑ ፡ ሆነና ፤
ሳላስብ ፡ በድንገት ፡ መኖሪያህን ፡ ለውጥ !
በቃህ ፡ አትቀላውጥ !
ያለህበት ፡ ዓለም ፡
ለጉብኝት ፡ እንጂ ፡ መኖሪያህ ፡ አይደለም ፤
ብሎ ፡ ሲፈርድብኝ ፤
ምክንያት ፡ ሳይሰጠኝ !
መሬትዋ ፡ ተከፍታ ፡ መልሳ ፡ ልትውጠኝ ።
በላቤ ፡ ለመብላት ፡ ገና ፡ ስፍጨረጨር ፡
ከተፍ ፡ ይልብኛል ፡ ውጥኔ ፡ እንዲቀር ።
ስሜ ፡ እንዲቀበር !
ዘመድ ፡ እንዲሸበር !
በኔም ፡ የሚረዳው ፡ ተጉላልቶ ፡ እንዲቀር ፤
በሞት ፡ ይቀጣኛል !
ሳልወድ ፡ ያጠፋኛል ።
የኔ ፡ ከዚህ ፡ መጥፋት !
ላትጠቀምበት ፤
ወይ ፡ ጨዋታ ፡ ሆኖ ፡ ላትደሰትበት ፤
በዚሁ ፡ ዓለም ፡ ልኑር ፡ ይግባኝ ፡ እንዳልሞት !

ማርያም ፡ አማልጅኝ ፡ ልኑር ፡ በዚህ ፡ ዓለም!
ሚካኤል ፡ አማልደኝ ፡ ልኑር ፡ በዚህ ፡ ዓለም፡
ልታይ ፡ ለዘለዓለም !

ገብርኤልም ፡ አማልደኝ ፡ ፈጥነህ ፡ ድረስልኝ ፡
ሩፋኤልምና ፡ ጭንቄን ፡ ተረዳልኝ ፡
ነቢያት ፡ ሰማዕታት ፡ ጌታን ፡ ለምኑልኝ ፡
ጌታን ፡ ለምኑልኝ !
ድምጼን ፡ አሰሙልኝ !
ተፈጥሮ ፡ ከመጥፋት ፡ ከመሞት ፡ ያድነኝ ።

በየምክንያቱ ፡ መቀጨቴ ፡ ይቅር !

ልኑር ፡ በዚህ ፡ ዓለም !
ባላውቀው ፡ ነገር ፡ የሚደሰት ፡ የለም ።

ዓምላክ ፡ ተለመነኝ ፡
ሞትን ፡ አስቀርልኝ !
ኑሮኤ ፡ አይወሰን ፡ ልኑር ፡ ፍቀድልኝ ።

ግራ ፡ ቀኝ ፡ ልበል ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ ልደሰት !
ወይም ፡ ደሀ ፡ ልሁን ፡ ቢሻኝ ፡ ልንከራተት ፤
እኔ ፡ መሥራት ፡ ባልችል ፡ የሌላን ፡ ልመ
ልከት !
ላንተው ፡ አቤት ፡ ልበል ፡ ይግባኝ ፡ እንዳል
ሞት ።

እዚሁ ፡ ይሻለኛል ፡ ሌላው ፡ አያሻኝም !
ያለየሁት ፡ ዓለም ፡ አያስደስተኝም ፤
አዲስ ፡ ጐጆ ፡ ወጪ ፡ መሆን ፡ አያምረኝም ።



ልኑር ፡ ፍቀድልኝ !
ይግባኙን ፡ ስማልኝ ።
ውሳኔህን ፡ ለውጥ ፡ ሞትን ፡ አስቀርልኝ ።
ዓምላክ ! አንተ ፡ አምላክ ! !
ጥፋቴን ፡ አትመኝ ፡ ምን ፡ ያደርግልሃል ፡
ጠቃሚ ፡ ከሆነም ፡ ያለፈው ፡ ይበቃል ።

ኤፍሬም ፤

አይ ፡ጉድ !
አስከሬኔን ፡ ማጌጥ ፡ ኋላ ፡ ለምንድር ፡ ነው ?
በሕይወት ፡ እያለሁ ፡ አበባውን ፡ ልየው ።

ሰሚው ፡ ግራ ፡ ገባው ፡ ዘመድም ፡ ሰለቸኝ ፤
የምለውን ፡ አጣሁ ፡ ጨነቀኝ ፡ ጠበበኝ ።

ኡ ! ኡ ! ብዬ ፡ ልጮህ ፡ አንዴ ፡ እንኳን ፡ ላቅ
ልጠው ፤
አያረካምና ፡ ቁጭት ፡ በደፈናው ።

አንጐሌ ፡ አይሠራም ፡ በቅቶታል ፡ ደከመ ፤
አንጀቴም ፡ ደበነ ፤
ልቤም ፡ ተኝቶአል ፡ ሥራውን ፡ አቆመ ።
አደራ ፡ ልጆቼ ፡ በጣም ፡ ተጠንቀቁ !
ወሬን ፡ ከመዶለት ፡ ለሥራ ፡ ታጠቁ ፤
ፍሬአችሁ ፡ ታይቶ ፡ እንድትደነቁ ።

ያለሥራ ፡ ዋጋ ፡ ልባችሁ ፡ አይመኝ ፤
ምኞት ፡ አያደረጅ ፡ ብልጽግና ፡ አያስገኝ ፤
ምክር ፡ ይሆናችሁ !

ቀልድ ፡ አይምስላችሁ ! ያባታችሁ ፡ ችግር ፡
ሠርቶ ፡ ማፍራት ፡ ሲችል !
ዕድሜውን ፡ ለፈጀው ፡ ታሪኩ ፡ ሳያምር ።

አደራ ፡ በሰማይ ፡ አደራ ፡ በምድር ፡ በሥ
ራችሁ ፡ ኩሩ !
ለራሳችሁ ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ አትኑሩ !
አንዴ ፡ ካመለጠ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ችግሩ ።
የኔስ ፡ ነገር ፡ ቀረ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ፡
ብዙ ፡ ነው ፡ ምስጢሩ ።

አሳብ ፤

ያሁኑ ፡ ኡ ! ኡ ! ታህ ፡ የሰው ፡ መሳቅያ !
ለተረት ፡ ይሆናል ፡ ጊዜን ፡ ማሳለፊያ ፡

እዬየህን ፡ ትተህ ፡ አሁንም ፡ በርትተህ ፤
ባለህ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ መሯሯጥ ፡ አለብህ ።

የሚረዳ ፡ ቢሆን ፡ ጩኸትና ፡ ለቅሶ ፤
ሁሉም ፡ ለጥ ፡ ባለ ፡ እጁን ፡ አለስልሶ ።

ያለ ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ ማግኘትን ፡ መመኘት ፡
በልምምጥ ፡ ሆነ ፡ ወይ ፡ ደግሞ ፡ በጉልበት ፤

ከራስ ፡ ሊያልፍ ፡ አይችል ፡ ዋስትና ፡ የለውም !
ሊያኮራ ፡ አይችልም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አይቆይም ፤

ኤፍሬም ፤

ተወኝ ፡ ይበቃኛል ፤
አሁን ፡ የምሰማው ፡ ምን ፡ ያደርግልኛል !



ጊዜው ፡ አልፎብኛል ፡ ጉልበቴ ፡ ከድቶኛል ፤
አበባው ፡ ጊዜዬ ፡ በከንቱ ፡ ጠውልጓል ።

ለእንቆቅልሽ ፡ ሁሉ ፡ ዋጋ ፡ እየሰጠሁ ፤
ሥራን ፡ ጠልቼ ፡ ኖርኩ ፡ ተጉልቼ ፡ ቀረሁ !

ዋጋዬ ፡ ብስጭት ፡ ትርፍ ፡ የሌለው ፡ ሆነ ፡
ልጅነት ፡ መልሶ ፡ የሚገኝ ፡ በሆነ ።

የልጅነት ፡ ጊዜዬ ፡ ሸርተት ፡ ብሎ ፡ አለፈ ፡
ምንም ፡ ሳልሰራበት !
ስመከር ፡ ስነገር ፡ እንዲያው ፡ ስወተወት ።

ቀኝ ፡ ጆሮዬ ፡ ሰምቶ ፡ በግራ ፡ ስልከው ፤
ምክሩን ፡ በመተርጎም ፡ በተንኮል ፡ ስወስደው ፤
ይተናነቀኛል ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ ልግለጸው !

ያሁኑ ፡ ለቅሶዬ ፡ እንዲያው ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፤
ሠርቶ ፡ ፍሬን ፡ ያጣ ፡ አሳዛኝ ፡ ለመምሰል ።

እየሰረሰረ ፡ ከውስጥ ፡ ከሚያደብነኝ ፤
ኀዘኔ ፡ ተገልጾ ፡ ከውጭ ፡ በታየልኝ !

አዬ !

እየዬን ፡ ባበዛ ፡ እምባኤን ፡ ባጎርፈው ፤
ያለፈውን ፡ ጊዜ ፡ ከቶም ፡ ላልመልሰው ፤
በቁሜ ፡ ቅበሩኝ !
ዋይ ! ዋይ ! አትበሉ ፡ ዋጋዬ ፡ ይኸው ፡ ነው ።

አይሆንም ፡ ልሰቃይ ፡ እንባዬን ፡ ላፍሰው ፤
ፊቴ ፡ ይጨማደድ ፡ እንባው ፡ ይቦርቡረው ፤

እንባው ፡ በግልጽ ፡ ይታይ !

በሰውነቴ ፡ ላይ ፡ እንደጠበል ፡ ይረጭ ፡
ወይም ፡ ቀበራችሁኝ ፡ አዋቂ ፡ ይተካ ፡ በኔ ፡
ስፍራ ፡ ይፈንጭ !
ሠርቶ ፡ ጮማን ፡ ይብላ ፡ የማር ፡ ጠጅን ፡ ይጎ
ንጭ ።

አዬ !

በጣም ፡ የሚገርመኝ ! ሁለት ፡ ዓይንን ፡ ሰጥቶ፡
ጆሮም ፡ ሰክቶልኝ !
የጅ ፡ ጣት ፡ የግር ፡ ጣት ፡ አፍንጫና ፡ ጸጉር ፡
ስላልጎደለብኝ ፤
ሁሉም ፡ ተደምረው ፡ እኔን ፡ ሰው ፡ አሰኙኝ ፤
ይገርማል ፡ ይደንቃል ፡ ምነው ፡ ባያሞኙኝ !
ሞቶአል ፡ ይቀበር ፡ መባሉ ፡ አይቀርም ፤
በቁም ፡ መቀበሬን ፡ ሰው ፡ አልተረዳውም ።
ዘጠኝ ፡ ወር ፡ መረገዝ ፡ ተወልዶ ፡ ጡት ፡ ማለት ፤
ድሆ ፡ ተንከባልሎ ፡ ጉልበትን ፡ ማላመድ ፤
ግራ ፡ ቀኝ ፡ እያሉ ፡ ባለም ፡ ላይ ፡
መታየት ፤

ላዋቂዎች ፡ ኩራት ፡ ለሰነፍ ፡ ግን ፡ ሁከት ።
በቃኝ ! እረ ፡ እስኪ ፡ በቃኝ !
ማንንም ፡ አልወቅስም ፡ ስንፍናኤ ፡ አጠቃኝ !
መስታወቴን ፡ ልያዝ ፡ ፊቴን ፡ ልመልከተው !
ለነገሩ ፡ ያህል ፡ ግምቴን ፡ ልወቀው !
የሰው ፡ አፈጣጠር ፡ ነገሩ ፡ ረቂቅ ፡ ኑሮው ፡



ትያትር ፡ ነው ፤
ከጭቃ ፡ ተፈጥሮ ፡ ተመልሶ ፡ ያው ፡ ነው ፤
እንደምንሰማው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ።

አይ ፡ ጉድ ! አይ ፡ ጉድ ! መሮጥ ፡ ሲያቅተኝ ፡
ሲደካከም ፡ ልቤ ፡
ሰውነቴ ፡ ሲያልቅ ፡ ጠፈፍ ፡ ሲል ፡ ላቤ ፤
ማታ ፡ ተገናኘን ፡ እኔና ፡ አሳቤ ፤
እኔና ፡ አሳቤ ።

በጥያቄ ፡ ልግታ ፡ ጽሑፌን ፡ ላሳጥር ፤
ለውጥ ፡ የሌለው ፡ ችግር ፡ ቢሰሙት ፡ አያምር ።

እረ ፡ ለመሆኑ !
ባለም ፡ ላይ ፡ ያለሁት ፡ በሕልሜ ? ? ? ?
? ? ? ? ? ? ? ? በውኔ ፡ ? ? ? ? ?
? ? ? ? ይህ ፡ ሁሉ ፡ እሮሮ ፡ ለጽድቅ !
? ? ? ? ? ? ? ለኩነኔ ፡ ? ? ? ? ?

ጥያቄው ፡ ሰለቸኝ !
መፍትሔው ፡ ቸገረኝ ፤
ያሳለፍኩት ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ህልም ፡ ታየኝ ፤

ሞቼ ፡ አልተገላገልኩ ፡ እኖራለሁና ፡
አይዞህ ፡ በሉኝ ፡ ምነው ፡ ጥቂት ፡ እንድጥናና ፡

በወንድ ፡ ልጅ ፡ ዓምላክ ፡ እርዳታ ፡ አድርጉልኝ ፡
ለዚች ፡ ለድርሰቴ ፡ <u>አርእስት ፡ ስጡልኝ ፤</u>
<u>አርእስት ፡ ስጡልኝ</u> ።

## ፕሮብሌም ፤

፩. የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ባል ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ እስከሄደበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የነበረውን ፡ የቤተሰብ ፡ ሁናቴ ፡ ከ፴ ፡ መስመሮች ፡ ባልበለጠ ፡ ጽሑፍ ፡ በግጥም ፡ ግለጽ ።

፪. አቶ ፡ ወንድይፍራው ፡ ወደ ፡ ጦር ፡ ሜዳ ፡ ለመሄድ ፡ ከተነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የዓይኔ ፡ አበባ ፡ ኤፍሬምን ፡ ወደ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እስከላከችበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የነበራትን ፡ ችግር ፡ የሚገልጽ ፡ ፳፭ ፡ መስ መር ፡ ግጥም ፡ ጻፍ ።

፫. ኤፍሬም ፡ የእናቱን ፡ ሕመም ፡ ሰምቶ ፡ « ሞታ ፡ ይሆን፡ በሕይወት ፡ አገኛታለሁ» እያለ ፡ በመጨነቅ ፡ የሁለ ቱን ፡ ቀን ፡ የድንጋጤ ፡ ጉዞውና ፡ አጠገብዋ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ሲላቀሱ ፡ የነበረውን ፡ ሃዘኑን ፡ የሚገልጽ ፡ በራስህ ፡ እንደደረሰ ፡ አድርገህ ፡ በ፴፭ ፡ መስመር ፡ በግጥም ፡ ጻፍ ።

፬. የኤፍሬምን ፡ ሁናቴ ፡ ባንድ ፡ ገጽ ፡ ተኩል ፡ ለሶስተኛ፡ ሰው ፡ አስረዳ ።

፭. ዘመቻ ፡ ሙሉ ፡ ዓለምና ፡ ኤፍሬም፡ የሚመሳሰሉበት፡ መንገድ ፡ እንዳለ ፡ ባጭር ፡ ግለጽ ።



፮. ኤፍሬም ፡ መጨረሻ ፡ በተቀበለው ፡ ምክር ፡ ተጠቅ ሞበታል ? አብራርተህ ፡ ጻፍ ።

፯. ኤፍሬምን ፡ ራሱን ፡ ከሚወድ ፡ ሰው ፡ ትመድበዋለህን? ለምን ?

ተፈጸመ ።